ወለል ላይ ደረሰ ። ባሕሩ ፀጥ እያለ ማዕበሉም ቀለል ብሏል ።

ጨረቃዋ ወከክ ብላ ትታያለች ። ሌላ ከፍተኛ ፍንዳታ ተሰማ ፤ እንደገናም ተደገመ ።

መርከቢቱ የበለጠ ወደአንድ አቅጣጫ እያዘነበለች መጣች ። የኋለኛው የመርከቡ ክፍል በፍጥነት ባሕሩ ውስጥ እየሰጠመ ሄደ ። መርከበኞቹ የአደጋ ጊዜ ጀልባውን ለመጠቀም ሙከራ አድርገው ነበር ፤ ግን ሁሉም ነገር በፈጣን ሂደት ከቁጥጥር ውጪ ሆነ ። ዙሪያው በእሳት ተቀጣጥሏል ፤ ለመሆኑ ኮንስታንቲን ዴሚሪስስ ወዴት ይሆን?

ከዚያ ሪዞሊ ድምፅ ሰምቶ ቀና ሲል ከመርከቡ በላይ በአሥር ሜጋ ርቀት ሄሊኮፕተር ስታንዣብብ ተመለከተ ። በሄሊኮፕተሯ መስኮት በኩል አንድ የሚያውቀውን ፊት አየና ትኩር ብሎ ሲመለከተው ኮንስታንቲን ዴሚሪስ መሆኑን ተረዳ ። ዴሚሪስ ፈገግ ብሎ አየው ፤ በእጁም ያንን በቀላል ዋጋ የማይተመነውን ቅርስ ይዟል ። ሪዞሊ አእምሮውን ሰብስቦ አደረገና የተፈጸመውን ሁሉ እንደገና ለማስታወስ ሞከረ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በዚህ እኩለ ሌሊት እንዴት ሄሊኮፕተር ሊያገኝ ቻለ…?

ሪዞሊ ይኼኔ የተረዳው ነገር ቢኖር ውሀው እያሳሳቀው ይዞት በመሄድ ላይ መሆኑን ነው ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከእርሱ ጋር በሽርክና ለመሥራት ምንም ፍላጐት አልነበረውም ። ከመጀመሪያውኑ ችግሩን ጠንስሶ ከዚህ ደረጃ ላይ ያደረሰው ያ ኬይሲ ዴሚሪስ ነው ። ዴሚሪስ ሸሽቶ ሊያመልጥ ነው ሲል ስልክ ያስደወለው ስፒሮስ ላምብሩ ሳይሆን ራሱ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነው ። ሪዞሊ ወደመርከቡ መጥቶ ከወጥመዱ እንዲገባ ያደረገውም ዴሚሪስ ነው ።

መርከቡ በውቅያኖሱ ውስጥ እየሰጠመ ሄደ ። ውሀው በመጀመሪያ እግሩን ሲያቀዘቅዘው ከዚያ ጉልበቱን ሲነካና ወደ አናቱም ሲያሻቅብ ሪዞሊን ተሰማው ። ማንም ሰው ምን እንደተፈጸመ ሊያውቅ የማይችል ቢት አሻራ እንኳ እንዳይቀር አድርጐ ዴሚሪስ ጠላቶቹን በሙሉ ንፍሮ አደረጋቸው ።

ሪዞሊ ቀና ብሎ ወደ ሄሊኮፕተሩ እያየ ጩኸቱን ቀጠለ ። “እባክህን ተመለስ? የፈለግከውን እሰጥሃለሁ ።” ነፋሱ ጩኸቱን ጠርጐት ሄደ ።

መርከቧ ሙሉ በሙሉ ከመስጠሟና ዓይኑ በጨውማው ውሃ ከመሸፈኑ በፊት ሪዞሊ ለመጨረሻ ጊዜ ያየው ሄሊኮፕተሯ ወደ ጨረቃው ስትምዘገዘግ ነበር ።



# ምዕራፍ አሥራ ሰባት

## ቅዱስ ሞሪዝ

ካተሪን ከመጠን በላይ ደንግጣለች ። ኪርክ ሪኖልድስ መሞቱን የበረዶ መንሸራተቻው ሥፍራ የሮንዶች አዛዥ የመቶ አለቃ ሃንስ በርግማን ሲነግራት ክፍሏ ውስጥ ፎቴ ላይ ተቀምጣ ፈዝዛ ትሰማ ነበር ። ምን ይናገር እንደነበረ ግን በውል አላዳመጠችውም ፤ መርዶው አደንዝዟታል ።

‘ለኔ ወዳጅ የሚሆኑ ሁሉ ይሞታሉ’ አለች በአሳቧ ተስፋ በቆረጠ መንፈስ ። ‘በፊት ላሪ ሞተ ፤ አሁን ኪርክ ተደገመ ። ሌሎችም እንደኖኤሌ ፓጂ ፣ ናፖሊዮን ቾታስና ፍሬዴሪክ ስታቭሮስን የመሳሰሉ አልፈዋል ። ፍጻሜ የሌለው ቅዠት ።’

በአሳብ ባሕር በመዋኘት ላይ እያለች ሃንስ በርግማን ከሚወረውራቸው ቃላት መሐል አንዳንዱን ብቻ ማዳመጧን ታስታውሳለች ። “ሚሲስ ሪኖልድስ … ሚስተር ሪኖልድስ …”

ቀና አለችና በድካም አነጋገር “እኔ ሚስስ ሪኖልድስ አይደለሁም” አለች ። “ስሜ ካተሪን አሌክሳንደር ይባላል ። እኔና ኪርክ … ጓደኛሞቾች ነበርን ።”

“ገባኝ ።”

ካተሪን በኃይል ወደ ውስጥ ተነፈሰች ። “እንዴት … እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ? ኪርክ እንኳ ጎበዝ የበረዶ ላይ ተንሸራታች ነበር ።”

“እኔም ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ እዚህ ሸርተቴ ሲጫወት አይቼዋለሁ” በማለት ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። “ሚስስ አሌክሳንደር ፣ እውነቱን ለመናገር የተፈጸመው ነገር እኔንም አስገርሞኛል ። ሬሳውን ያገኘነው ቁልቁልት በመናዱ ባለፈው ሳምንት ተዘግቶ በነበረው የላጋልፕ የሸርተቴ መጫወቻ ሥፍራ ነው ። የተናደው በነፋስ ኃይልም ሊሆን ይችላል ። ግን በጣም አዝናለሁ ።”

'እዝናለሁ የሚል ቃል እንዴት ደካማና አስቀያሚ ቃል ነው' አለች በልቧ ።

"ሚስስ አሌክሳንደር ቀብሩን በምን ዓይነት ሁኔታ እንድናካሄድ ልሽ ነው የምትፈልጊው?"

ሞትኮ ለሰው ልጅ የመጨረሻው አይደለም ። ከሞትም በኋላ የሚከናወኑ ሥነ ሥርአቶች አሉ ። የመቃብር ቦታ መምረጥና ማዘጋጀት ፤ የሬሳ ሳጥን መግዛት ፤ አበባ መሸመት ፣ ለዘመዶች ማሳወቅ ። ካተሪን መሥሁ ቃጣት ።

"ሚስስ አሌክሳንደር?"

"የግሪክ ቤተሰቦቹ እንዲያውቁት አድርግ" አለች ካተሪን ቀና ብላ።

"አመሰግናለሁ ።"

ወደ ለንደን ስትመለስ ሐዘኗ የከፋ ነበር ። ከኪርክ ጋር ወደተራራው ስትመጣ ወደ አዲስ ሕይወት የመግቢያ በር ይሆነኛል ብላ ገምታ ነበር ።

ኪርክን በጣም ጨዋና ታጋሽ ሰው ሆኖ አግኝታዋለች ። 'አብሬው ተኝቼ ቢሆን ኖሮ ምን ነበረበት?' አለች ካተሪን በአሳቧ ። 'ግን ያም ቢሆን ምን ፋይዳ ሊኖረው ፤ ምን ዓይነት የተረገምኩ ገሬ ፍጡር ነኝ፤ ወደኔ የሚቀርቡትን ሁሉ የማጠፋ ቤት ።'

ወደ ለንደን እንደተመለሰች ልቧ በሐዘን በመነካቱ ወዲያውኑ ሥራ ለመግባት አልቻለችም ። ማንንም ሳታይና ሳታነጋግር እቤቷ ቁጭ አለች። የቤት ሠራተኛዋ አና ምግብ እያዘጋጀች ወደካተሪን መኝታ ቤት ብትወስድላትም ምግቡ ሳይነካ ነው የሚመለሰው ።

"አንድ ነገር መቅመስ አለብሽ ሚስስ አሌክሳንደር ።"

ስለምግብ ማሰቡ እራሱ ካተሪንን ያሳምማት ነበር ።

ካተሪን በሚቀጥለውም ቀን ባሰባት ። ደረቷ በብረት የታመቀ ይመስል መተንፈስ ተሳናት ።

'በእንዲህ ዓይነት ልቀጥል አልችልም' አለች ካተሪን በአሳቧ ። 'አንድ ነገር ማድረግ ይኖርብኛል ።'

ከኤቪሊን ኬይ ጋር ተወያየች ። "ለተፈጸመው ሁሉ ጥፋተኛዋ እኔ ነኝ ።"



"የምትናገሪው ስሜት አይሰጥም ካተሪን ።"

"ስሜት እንደማይሰጥ አውቃለሁ ፤ ግን ምን ላድርግ? የኀሊና ፀፀት ይሰማኛል ። ስለዚህ ጉዳይ የማነጋግረው ሰው ያስፈልገኛል ። ምናልባት የሥነ አዕምሮ ሐኪም ባገኝ ። ..."

"እኔ የማውቀው በጣም ጥሩ የሆነ ሐኪም አለ" አለች ኤቪሊን ። "ዊምም የሚመላለሰው እርሱ ዘንድ ነው ። አላን ሃሚልተን ይባላል ። ሕይወቷን ልታጠፋ የነበረች አንዲት ጓደኛዬ የዶክተር ሃሚልተንን ሕክምና ካገኘች በኋላ በደህና ሁኔታ ላይ ትገኛለች ። ሄደሽ ልታነጋግሪው ትፈልጊያለሽ?"

'እብደኛሽ ቢለኝስ? እውነት እብድ ሆኜ ከተገኘሁስ' ስትል ካሰበች በኋላ "እዎ አነጋግረው" አለቻት ለኤቪሊን በግድየለሽነት ።

"ሥራ ስለሚበዛበት እኔ ቀጠሮ እይዝልሻለሁ ።"

"አመሰግናለሁ ኤቪሊን ። ውለታ ከፋይ ያድርገኝ ።"

ካተሪን ወደዊም ቢሮ ሄደች ። 'ስለኪርክ ለማወቅ ይፈልግ ይሆናል' አለች በአሳቧ ።

"ዊም ኪርክ ሬኖልድስን ታስታውሳለህ? ከጥቂት ቀናት በፊት የበረዶ ሸርተቴ ሲጫወት አደጋ ደርሶበት ሞተ ።"

"እዎ ፣ በዌስት ሚኒስትር — ዜሮ ፣ አራት ፣ ሰባት ፣ አንድ" አላት ።

ካተሪን ዓይኗን አርገበገበችና "ምን?" አለችው ። ስታስታውሰው ለካ ዊም የሚናገረው የኪርክን መኖሪያ ቤት የስልክ ቁጥር ነው ።

በቃ ፣ ለዊም ሰው ማለት ያችን ታክል ብቻ ናት? በጥቂት ቁጥሮች መግለጽ? ለመሆኑ ለሰው ልጅ ምንም ስሜት የለውም? በእውነት ሰዎችን ለመውደድና ለመጥላት ወይም ሊራራላቸው ስሜት የሚባል ነገር በውስጡ አልተፈጠረበትም?

'ምናልባት ከእኔ ሳይሻል አይቀርም' ኣለች ካተሪን በአሳቧ ። 'ምክንያቱም እኔን ከሚያሰቃየኝ ጭንቀት እርሱ ነፃ ነው ።'

ካተሪን ዶክተር ሃሚልተንን በሚቀጥለው ዓርብ እንድታነጋግር ኤቪሊን ቀጠሮ ያዘችላት ። ኤቪሊን ያደረገችውን ለኮንስታንቲን ዴሚሪስ ለመንገር ፈልጋ ነበር ። ሆኖም ጉዳዩ አስፈላጊ ስላልሆነ ለምን እረብሸዋለሁ ብላ ተወች ።

የአላን ሃሚልተን ቢሮ የሚገኘው ከዊምፖል ጎዳና ላይ ነው ። ካተሪን በስጋትና በንዴት መንፈስ ለመጀመሪያው ቀጠሮዋ ተገኘች ። የስጋቸው ስለእኔ ምን ይል ይሆናል ብላ በማሰቧ ሲሆን ንዴቷ የመነጨው ደግሞ እራሷ በራሷ ለችግሯ መፍትሄ መሻት ሲገባት የማታውቀው ባዳ እንዲያቃልልላት በመተማመኗ ነበር ።

ከመስተዋት የተሠራ ክፍል ውስጥ የተቀመጠችዋ አስተናጋጅ "ሚስስ አሌክሳንደር ፣ ዶክተር ሃሚልተን እየጠበቀሽ ነው" አለቻት ።

'እኔስ ተዘጋጅቻለሁ?' አለች ካተሪን በአሳቧ ። መላ ሰውነቷ ተረብሿል ። 'እዚህ ምን አደርጋለሁ? እራሱን እንደ እግዜር ለሚቆጥር ተመጻዳቂ እራሴን አሳልፌ አልሰጥም ።'

ካተሪን አስተናጋጇን እንዲህ አለቻት ፦ "አሳቤን ቀይሬአለሁ ። ዶክተር ማነጋገር የሚያስፈልገኝ አይመስለኝም ። ቀጠሮ የተያዘበትን ሒሳብ ለመክፈል ፈቃደኛ ነኝ ።"

"እረ? እንዴ ቆዪኝ ።"

"ግን … "

አስተናጋጅዋ ወደዶክተሩ ቢሮ ገባች ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የቢሮው በር ተከፍቶ አላን ሃሚልተን ከውስጥ ወጣ ። ዕድሜው በመጀመሪያዎቹ አርባዎች አካባቢ ሲሆን ረዘም ያለ ወርቅማ ፀጉር ያለው የዓይኑ ብሌን ወደ ሰማያዊነት ያዘነበለና ቁመናው የማይከብድ ሰው ነው ።

ካተሪንን አያትና ፈገግ አለ ። "በቃ ቀኑ የኔ ነው በይኛ" ብሎ ተናገራት ።

ካተሪን ግንባሯን ቋጠረችና "ምን …?" ብላ ጠየቀችው ።

"ምን ያህል ጎበዝ ሐኪም እንደሆንኩ አላወቅኩም ነበር ። ገና ከማስተናበሪያ ክፍሌ ስትደርሺ በሽታሽ ይልቀቅሽ? ይህ ተመዝግቦ የሚያዝ ነው ።"

ካተሪን ላለመረታት "ይቅርታ ተሳስቼ ነው ። ዕርዳታ የሚያስፈልገኝ አይመስለኝም" ስትል መለሰች ።

"ይህንን በመስማቴ ደስ ብሎኛል" አላት አላን ሃሚልተን መልሶ ። "ሁሉም በሽተኞቼ እንዲህ በሆኑልኝ ምንኛ ደስ በተሰኘሁ ። ከመጣሽ ዘንዳ ሚስስ አሌክሳንደር ፣ ለምን ወደውስጥ ገብተሽ ለትንሽ ጊዜ አብረን ቡና አንጠጣም?"



"አመሰግናለሁ ። አይ እኔ አልጠጣም …"

"ብዙ አላቆይሽም ።"

ካተሪን አመነታችና "እሺ ፣ ለደቂቃ ያህል" ብላ ተከትላው ወደቢሮው ገባች ። ቢሮው ቀለል ያለ ገጽታ ያለው ሆኖ ከቢሮነት ይልቅ የመኖሪያ ቤት ሳሎንነት ድባብ ይታይበታል ። በግድግዳዎቹ ላይ ልብ የሚመስጡ ጥቅሶች ተሰቅለዋል ። አንዲት ቆንጆ ሴት ከሕጻን ልጇ ጋር የተነሳችው ፎቶግራፍ በጠረጴዛው ላይ ተደርጓል ።

'መልካም እንግዲህ የተዋበ ቢሮና ጥሩ ቤተሰብ አለው ። ምን ይሁን ታዲያ?' አለች በልቧ ።

"እባክሽ ቁጭ በይ" አላት ዶክተር ሃሚልተን ። "ቡናው በደቂቃ ውስጥ ይደርሳል ።"

"ዶክተር ጊዜህን ባልገድልብህ ጥሩ ይመስለኛል ። እኔ …"

"ግድየለም አትጨነቂ" ብሎ በአንድ አነስተኛ ወንበር ላይ ተቀመጠና ፊቷን ያጠና ጀመር ።

"ብዙ ችግሮች ደርሰውብሻል" አላት በሀዘኔታ ።

"ምን እንደደረሰብኝ የምታውቀው ነገር ምን አለ?" አለች ካተሪን በቁጣ ።

"ኤቬሊን በቅዱስ ሞሪዝ የሆነውን ነገር አጫውታኛለች ። በጣም አዝናለሁ ።"

'ያ የማልወደው አስጠሊ ቃል እንደገና መጣ?' አለች በልቧ ።

"እውነት አዝነሃል? ችሎታ ያለህ ሐኪም ከሆንክ እስቲ ኪርክን መልሰህ ሕይወት ዝራበት ።" ስቃይና ጭንቀቷ ፈንቅሎ መውጣት ጀምሯል ። ካተሪን እራሷን መቆጣጠር ተሳናትና እየተብረከረከች መነፍረቅ ጀመረች ።

"ተወኝ" አለች እያለቀሰች "ተወኝ ።"

አላን ሃሚልትን ሳይናገር ተቀምጦ ያያት ነበር ።

ካተሪን ልቅሶዋ እየቀነሰ ሲመጣ በሀፍረት "በጣም አዝናለሁ ፣ ይቅርታ አድርግልኝ ። አሁን መሄድ አለብኝ ።" ብላ ተነስታ ወደ ወንበሩ መራመድ ጀመረች ።

"ሚስስ አሌክሳንደር ፣ ልረዳሽ እንደምችል እርግጠኝ አይደለሁም፣ ግን ልሞክር እፈልጋለሁ ። ደግሞ የማደርገው ማንኛውም ነገር ጨርሶ የማይጎዳሽ መሆኑን ቃል እገባልሻለሁ ።"

ካተሪን እያመነታች በሩ አጠገብ ቆመች ። ዓይኗ እንባ እንዳቀረረ ዞር ብላ አየችውና “ምን እንደነካኝ አላውቅም” አለች በማንሾካሾክ ። “ጨርሶ የጠፋሁ ይመስለኛል ።”

አላን ሃሚልተን ከተቀመጠበት ተነሳና ወደቆመችበት ሄደ ። “ታዲያ ከጠፋሽበት ልናገኝሽ ለምን አንሞክርም? ይህንን ለማሳካት ደግሞ አብረን ጥረት እናድርግ ። እስቲ ቁጭ በዩና ቡናውም ደርሶ እንደሆነ ልጠይቅ ።”

ከክፍሉ ከወጣ አምስት ደቂቃ አልፎታል ። ካተሪን እዚያው በተቀመጠችበት ሆና እንዴት አድርጎ አቀዝቅዞ እንድትቆይ እንዳደረጋት ገረማት ። ሰዎችን የማብረድ ጥበብ አለው ። የማረጋጋት ችሎታ እንዳለው ከሁኔታው ያስታውቃል ።

‘ሊረዳኝ ይችል ይሆናል’ አለች ካተሪን በአሳቧ ።

አላን ሃሚልተን ሁለት ፊንጃል ቡና ይዞ ወደቢሮው ተመለሰ ። “ወተትና ስኳር ይደረግበት?”

“የለም አመሰግናለሁ ።”

ከፊት ለፊቷ ባለው ወንበር ላይ ተቀመጠ ። “ጓደኛሽ የበረዶ ላይ ሸርተቴ ሲጫወት አደጋ ደርሶበት የሞተ መሰለኝ” አላት ።

ስለዚያ አንስቶ መናገር ይዘገንናታል ። “አዎ ፣ ተንዶ ከአገልግሎት ውጪ በሆነ መንሸራተቻ ሥፍራ ነው ሞቶ የተገኘው ። ኃይለኛ ንፋስ መሰለኝ የናደው ።”

“በጣም የሚቀርብሽ ሰው በሞት ሲለይሽ ይህ የመጀመሪያ ጊዜሽ ነው?”

ይህንን ጥያቄ እንዴት አድርጋ ትመልስ? አይደለም ባለቤቴና ዕቁባቱ ሊገድሉኝ በመሞከራቸው ተረሽነዋል ። እኔን የቀረበ ሁሉ ይሞታል ብላ ትንገረው? በጣም ይሰቀጥጣል ። ሐኪሙ ከፊት ለፊቷ ተቀምጦ ለጥያቄዋ የሚያረካው መልስ ግን የላትም ። ‘ደግሞ በሕይወቴ ምን አገባው? አሁንስ ጠላሁት’ አለች በልቧ ።

አላን ሃሚልተን ከፊቷ ላይ ከፍተኛ ንዴት አነበበ ። ርዕስ ለመለወጥ ያህል “ቪም እንዴት ነው?” ብሎ ጠየቃት ።

ጥያቄው ካተሪን የነበረችበትን ሁኔታ ከመቅጽበት እንድትረሳው አደረጋት ። “ቪም? ደህና ነው ። የአንተ በሽተኛ እንደሆነ ኤቬሊን ነገረችኝ ።”



“አዎ”

“ባሕሪው በምን ምክንያት እንዲህ እንደሆነ ልትገልጥልኝ ትችላለህ?”

“ቪም በመጀመሪያ ወደእኔ የመጣው በየጊዜው ከሥራ በመባረሩ ነበር ። ሰውዬው የተለየ ባሕሪ ነው ያለው ። በሰው ልጅ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ አለው ። ለምን እንዲህ ሊሆን እንደቻለ ለጊዜው ለማወቅ አልቻልኩም ። ግን ሰዎችን ይጠላል ። ከሰው ጋር ለመቀራረብ ችግር አለበት ።”

ካተሪን ኤቬሊን የነገረቻትን አስታወሰች ። ‘ሰውዬው ስሜት የሚባል ነገር አልተፈጠረበትም ። ከማንም ጋር ሊቀራረብ አይችልም ።’

“ግን ቪም በሒሳብ በጣም ጎበዝ ነው” አለ አላን ሃሚልተን። ንግግሩን በመቀጠል “አሁን የሚሠራው ይህን ችሎታውን ሊጠቀምበት በሚችልበት ሥፍራ ነው ።”

ካተሪን ጭንቅላቷን ነቀነቀች ። “እንደርሱ ዓይነት ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም ።”

አላን ሃሚልተን ቀና አለና “ሚስስ አሌክሳንደር” አላት ። “ጎሊና የሚያቆስል ነገር እንዳጋጠመሽ አውቃለሁ ። ችግሩን ላቃልልሽ ብሞክርስ?”

“እ… እንጃ” አለች ካተሪን ። “ተስፋ የሌለው ነገር ይመስለኛል።”

“እንዲህ የምታስቢ ከሆነማ የትም ለመድረስ አንችልም ።” አላት አላን ሃሚልተን ። ልብ በሚሰርቅ ፈገግታ “ለምን ሌላ ቀጠሮ አንይዝም? ያኔ በውይይታችን ማብቂያ ላይ የምትጠዪኝ ከሆነ መገናኘታችንን እናቆማለን ።”

“ያን ያህል አልጠላህም” አለችው ካተሪን በይቅርታ ስሜት።

አላን ሃሚልተን ተነስቶ ወደጠረጴዛው ሄደና የቀጠሮ መስጫ አጀንዳውን ተመለከተ ። አጀንዳው ሙሉ ነው ።

“የሚቀጥለው ሰኞ ቢሆንስ?” አለና ጠየቃት ። “ከቀኑ በሰባት ሰዓት ።” ሰባት ሰዓት የምሳ መመገቢያ ጊዜው ሲሆን ያን ዕለት ምሳውን ሊተወው ፈልጓል ።

ካተሪን አሌክሳንደርን ካደረባት ከፍተኛ ጭንቀት ሊያላቅቃት አቅሙ የሚችለውን ሁሉ ለማድረግ ፈቃደኛ ሆኗል ።

ካተሪን ለረዥም ጊዜ ቀና ብላ አየችው “እሺ ።”

“መልካም ፣ እንግዲህ በቀጠሮው ዕለት እንገናኛለን” አለና

አድራሻው ያለበትን ካርድ ሰጣት ። "ከዚያ ወዲህ ልታገኝኝ ከፈለግሽ የቢሮዬና የቤቴ ስልክ ቁጥር ካርዱ ላይ አለልሽ ። እንቅልፋም ብሆንም መቀስቀሱን አትስጊ ።"

"አመሰግናለሁ ።" አለችው ካተሪን ። "ሰኞ እመጣለሁ ።"

ካተሪን ከቢሮው ስትወጣ ዶክተር አላን ሃሚልተን ዝም ብሎ እያትና በአሳቡ 'ሁሉ ነገሯ ተሰባሪ ይመስላል ፤ ውብ ናት ። ስለዚህ ጥንቃቄ ላደርግ ይገባኛል' አለ ። ጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን ፎቶግራፍ እያየ 'አንጂላ ምን ታስብ ይሆን' አለ በልቡ ።

እኩለ ሌሊት ላይ የኮንስታንቲን ዴሚሪስ ስልክ ጠራ ። ስልኩን አንስቶ እንደሰማ በመገረም ተመላ ።

"ቲኤሌ ሰመጠች ነው የምትለኝ፣ እኔ አላምንም ።"

"አዎ ሚስተር ዴሚሪስ የባሕር ጠረፍ ጠባቂው ጥቂት ስብርባሪ ነገሮችን ብቻ ነው ያገኘው ።"

"በሕይወት የተረፉ ሰዎች አሉ?"

"ማንም አልተረፈም ጌታዬ ። ሁሉም ሰጥመዋል ።"

"በጣም አሰቃቂ ነገር ። እንዴት ሊሆን እንደቻለ የሚያውቅ ሰው አለ?"

"ማንም የሚያውቅ አይመስለኝም ጌታዬ ። መረጃ ሁሉ አብሮ ከባሕሩ ሰምጧል ።"

"ባሕሩ" አለ ዴሚሪስ በማጉመትመት "ምህረት የለሹ ጨካኝ ባሕር እነዚያ ሁሉ ጉብዛዝት እንዴት ሕይወታቸውን እንዳጡ ማሰቡ እራሴ ይሰቀጥጣል በሉ አደጋውን ለኢንሹራንስና ለሌሎችም ለሚመለከታቸው አሳውቁ ።"

ታሪካዊውን ቅርስ በግል የቅርስ መሰብሰቢያ ክፍሉ ውስጥ አኖረው ። አሁን እንግዲህ ዋርሳው የሚቀጣበትም ጊዜ ነው ።



# ምዕራፍ አሥራ ስምንት

ስፒሮስ ላምብሩ የኮንስታንቲን ዴሚሪስን መታሰር ለመስማት በጉጉት ይቅበጠበጣል ። ሬዲዮውን ከቢሮው ውስጥ ከፍቶን ትቶ ሲያዳምጥ ይውላል ። በየዕለቱ የወጡትን ጋዜጦች በሙሉ አስመጥቶ አንብቧቸዋል። 'እስካሁን አንድ ነገር መስማት ነበረብኝ' አለ ላምብሩ በአሳቡ ። እስካሁን ፖሊሶች ዴሚሪስን ማሰር ነበረባቸው ። አደንዛዥ ዕፁን ዴሚሪስ እንደሚያጓጉዝለት ቶኒ ሪዞሊ ለስፒሮስ ነግሮት ፣ ስፒሮስም ስሙን ደብቆ ለአሜሪካ ጉምሩክ ነገሩን አስታውቋል ።

'እስካሁን ሳይዙት አልቀሩም ። ታዲያ ጋዜጦቹ ዜናውን ለምን ሳያወጡት ቀሩ?'

ኢንተርኮሙ የደወል ጥሪ አሰማ ።

"ሚስተር ዴሚሪስ በሁለተኛው መሥመር ላይ ሊያነጋግርህ ይፈልጋል ።"

"ሚስተር ዴሚሪስን የሚፈልግ ሰው ነው የደወለው?"

"አይደለም ሚስተር ላምብሩ ። ስልኩን የደወለው እራሱ ሚስተር ዴሚሪስ ነው ።" ፀሐፊዋ የተናገረቻቸው ቃላት በሰውነቱ ውስጥ የትካዜ ስሜት ረጨ ።

'ሊሆን አይችልም!' ላምብሩ በብስጭት የስልኩን እጀታ አነሳ ። "ኮስታ ነህ?"

"ስፒሮስ ። እንዴት ነህ ጃል?" የዴሚሪስ ድምፅ ደስተኛ ይመስል ነበር ። "ደህና ፣ ደህና ። የት የነው ያለኸው?"

"እዚሁ አቴንስ ውስጥ ነኝ ። ዛሬ ምሳ እንዴት ነው? ጊዜ ይኖርሃል?"

ላምብሩ የማይቀርበት የምሳ ቀጠሮ ነበረው ፤ ግን "አዎ ይቻላል" ሲል መለሰለት ። "ጥሩ በስምንት ሰዓት ክበቡ ውስጥ እንገናኝ ።"

ላምብሩ እጁ እየተንቀጠቀጠ የስልኩን እጀታ መልሶ አስቀመጠው። 'ስለ እግዜር የተሳሳትነው የቱጋ ይሆን?' እንግዲህ የተፈጸመውን ሁሉ በቅርብ ጊዜ ሊያውቀው ነው ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ሰላሳ ደቂቃዎች ያህል ስፒሮስን አስጠበቀው ። ዘግይቶ እንደመጣ "በመዘግየቴ ይቅርታ!" አለው ።

"ግድ የለም ።"

የሰሞኑ ሁኔታ በዴሚሪስ ላይ ያስከተለው ለውጥ ካለ ብሎ ስፒሮስ ላምብሩ በጥሞና አጠናው ። ምንም ለውጥ አይታይበትም ።

"ርቦኛል" አለ ዴሚሪስ በፈገግታ ። "አንተስ? እስቲ የዕለቱን የምግብ ዝርዝር እንመልከት" አለና ዝርዝሩን በዓይኑ ቃኘው ።

"እሃ ፡ ስትሪዳ ። ስፒሮስ በዓሣ እንጀምር?"

"የለም አይመስለኝም" አለ ። አሁንም ምንም ምግብ አላሰኘውም። ዴሚሪስ ተደሳች ለመምሰል ሲሞክር ላምብሩን ግን ቀፎታል ።

ምግብ ካዘዙ በኋላ "ላመሰግንህ እወዳለሁ ስፒሮስ" አለ ዴሚሪስ።

ስፒሮስ ትኩር ብሎ አየው ። "ስለምን?"

"ስለምን? ሚስተር ሪዞሊ የተባለውን ጥሩ ደንበኛ ስለላክልኝ ።"

ላምብሩ በምላሱ ከንፈሩን ጠረገ ። "ተ…ተገናኝታችሁ ነበር?"

"ታዲያስ ወደፊት ብዙ የንግድ ሥራ አብረን ለመሥራት ተዋውለናል" አለና ዴሚሪስ ሳቀ ። "ምን ያደርጋል ታዲያ የሚስተር ሪዞሊ ጉዳይ አበቃለት ።" ስፒሮስ ደንገጥ አለ ። "ምን ማለትህ ነው?" የኮንስታንቲን ዴሚሪስ ድምፅ ጠንከር እያለ መጣ ። "ቶኒ ሪዞሊ ሞቷል ማለቴ ነው።"

"እንዴት … ምን ሆነና?"

"አደጋ አጋጠመው ስፒሮስ" ብሎ የዋርሳውን ዓይን ትኩር ብሎ ይመለከት ነበር ። "እኔ ላይ ሸርና ደባ ለመፈጸም የሚጥር ሁሉ እንደሚደርስበት አደጋ ዓይነት ።"

"እኔ ምንም … እኔን ምንም አልገባኝም ። አንተ …"

"አልገባህም? አንተ ልታጠፋኝ ሞክረህ ነበር ግን አልተሳካልህም ፡ ሙከራው ቢሳካልህ ምንኛ በታደልክ ነበር?"

"ስለ … ስለምን እንደምታወራ አልገባኝም ።"

"አልገባህም ስፒሮስ?" አለና ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ፈገግ አለ ።

"በቅርቡ ይገባሃል ። መጀመሪያ ግን የማጠፋው እህትህን ነው ።"

"ዓሣው ቀረበ ።"

"እሃ!" አለ ዴሚሪስ ። "በጣም ይጣፍጣል ፡ በል ብላ ።"

እንደተለያዩ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከላምብሩ ጋር ባደረገው ግንኙ



ነት ከፍተኛ እርካታ ተሰማው ። የስፒሮስ ላምብሩ ሞራል ደግሞ በጣም አድርጐ ተነክቷል ። ዴሚሪስ ፡ ላምብሩ እህቱን ምን ያህል በጣም አድርጐ እንደሚወዳት ስለሚያውቅ ሁለቱንም በጋራ ለማጥቃት ቆርጦ ተነስቷል።

ግን በቅድሚያ የሚፈጸመው ጉዳይ አለ ። የካተሪን አሌክሳንደር ጉዳይ። ከኪርክ ሞት በኋላ የተሰማትን ጭንቀት ደውላ ነግራው ነበር ።

"ነገሩ … ነገሩ በጣም ያንገበግባል ።"

"በጣም አዝናለሁ ካተሪን ኪርክን ምን ያህል ትወጂው እንደነበር ይገባኛል ። አደጋው ሁለታችንንም ጥሩ ወዳጅ አሳጥቶናል ።" 'ስልቴን መቀየር አለብኝ ።' አለ ዴሚሪስ በአሳቡ ። 'ለራፈና ምንም ጊዜ አይኖረኝም ። በጣም መጥፎ ነገር ።' በናኤሌ ፓጂና በላሪ ዶግላስ ላይ ከተፈጸመው ጋር ልታነካካው የምትችልና አሁን በሕይወቷ የተረችው ካተሪን ብቻ ናት ። ይህን ያህል ጊዜ በሕይወት እንድትቆይ ማድረጉም ስሕተት ነው ። እርሷ በሕይወት እስከቆየች ድረስ ዴሚሪስ የፈጸመውን ወንጀል ለማረጋገጥ ለሚፈልግ ማስረጃ ትሆነዋለች ። ከሞተች ግን ከአደጋ ነፃ ይሆናል ።

ዴሚሪስ ከጠረጴዛው ላይ ያለውን ስልክ አንሳና የሆነ ቁጥር ደወለ። ተቀባይ እንዳገኘ "በሚመጣው ሰኞ ኮውሉን ውስጥ ስለምሆን እዚያው ተገኝ" አለና ስልኩን መልሶ ዘጋው ።

በግንብ በታጠረችው ከተማ ውስጥ በምትገኘው የዴሚሪስ የግል ቤት ውስጥ ሁለቱ ሰዎች ተገናኙ ። "በድንገት የደረሰ አደጋ መምሰል አለበት ፡ እንዲህ ለማድረግ ይከብድሃል?" ሲል ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ጠየቀ ።

ተጠያቂው ጥያቄውን እንደስድብ ነው የቆጠረው ። ደሙ ፈላ ። መንገደኛ እንጂ በሙስኩ የተካነ ሰው እንዲህ ዓይነት ጥያቄ አይጠየቅም ። በአሽሙር እንዲህ ብሎ ሊመልስለት ፈልጐ ነበር ። 'የሚከብደኝ አይመስለኝም ። ከረጅም የፎቅ ደረጃ ላይ ወድቃ አንገቷን የተቀጨች ለማስመሰልም አይሳነኝም ። ማርሴሊስ ባለው ደናሽ አማካይነት ወይንም ሰክራ ፡ በገላ መታጠቢያ ገንዳዋ ውስጥ ሰጥማ እንደሞተች ለማስመሰል እችላለሁ ። በማስታድ ፡ በወራጂ አማካኝነት ፡ ወይንም ሄሮይን ከመጠን

በላይ ወስዳ እንደሞተች ። ሦስቱ የተቀነባበሩ ዘዴዎች እነኚሁ ሲሆኑ ፣ ሲጋራዋን ሳታጠፋ እንቅልፍ እንደወሰዳትም ለማስመሰል ይቻላል ።' ፓሪስ ውስጥ በኤል ሆቴል ያለውን ስዊድናዊ የመረጃ ሰው አስታወሰ ። 'ከቤት ውጭ ቢሆን አይሻልም? በመኪና ወይንም በአይሮፕላን አደጋ እንድትሞት ወይንም በባሕር ውስጥ እንድትሰጥም ለማድረግ እችላለሁ።' ሆኖም ግን ከፊት ለፊቱ የተቀመጠውን ሰው በመፍራት ይህንን አሳቡን አውጥቶ ሊናገር አልቻለም ። የዚህን ሰው ብዙ አስደንጋጭ ታሪኮች ሰምቷል ። የሰማቸውን ሊያምን የቻለባቸው በርካታ ምክንያቶችም ነበሩት ።

ስለዚህ "አዎ ጌታዬ ማንም ሊደርስበት የማይችል ድንገተኛ አደጋ ላቀናብር እችላለሁ" ብቻ ነበር ያለው ። ይህንን ሲናገር እንኳን 'እኔ ራሴ ምስጢሩን እንደማውቅ መቼም ይረዳል' ሲል ደንግጧል ። ከዚያ ፀጥታ ሰፈነ ። በግንብ በተከበበችው ከተማ ውስጥ ያሉት ነዋሪዎች የተዘበራረቀ ውካታ በመስኮት እየገባ ይሰማዋል ።

ዴሚሪስ ትኩር ብሎ በዓይኑ መረመረው ።

"በጣም ጥሩ ፣ እንግዲህ የዘዴውን ጉዳይ ላንተ እተዋለሁ ።"

"እሺ ጌታዬ ። ለመሆኑ ዒላማዋ እዚህ ኩውሉን ነው ያለችው?"

"ለንደን ነው ፤ ካተሪን ትባላለች ። ካተሪን አሌክሳንደር ። ለንደን ባለው ቢሮዬ ውስጥ ነው የምትሰራው ።"

"ብተዋወቃት ለሥራዬ ይረዳኛል ። ውስጡን ለማወቅ ።"

ዴሚሪስ ጥቂት ካሰበ በኋላ "አንድ የሥራ አስኪያጅ ቡድን በሚቀጥለው ሳምንት ወደለንደን ልልክ ነው ። አንተም ከእነርሱ አንዱ እንድትሆን አደርጋለሁ" አለው ። ወደሱ ቀረብ ብሎ "ተጨማሪ ነገር" ብሎ ተናገረ ።

"እሺ ጌታዬ ምን ነበር?"

"ማንም ሬሳዋን ለይቶ እንዲያውቅ አልፈልግም ።"



# ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ስልክ ደወለ ። "እንደምን አደርሽ ካተሪን ። ዛሬ እንዴት ነሽ?"

"ደህና ፣ አመሰግናለሁ ፣ ኮስታ ።"

"ትንሽ ተሽሎሻል?"

"አዎ"

"ጥሩ ። ይህንን በመስማቴ በጣም ደስ ብሎኛል ። የኩባንያችን የሥራ አስኪያጆች ቡድንን ለንደን ያለው ሥራችን እንዴት እንደሚካሄድ ጥናት እንዲያደርጉ ወደዚያው ልኬአቸዋለሁ ። በደንብ ተቀብለሽያቸው ብታስተናግጂአቸው ደስ ይለኛል ።"

"በጣም ደስ ይለኛል ። የሚመጡት መቼ ነው?"

"ነገ ጠዋት ።"

"የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ ።"

"እንደምታደርጊ እተማመንብሻለሁ ። አመሰግናለሁ ካተሪን ።"

"ግድ የለም ።"

"ደህና ሁኚ ካተሪን ።"

ስልኩ ተቋረጠ ።

'አዎ እንግዲህ ተጠናቋል' አለ ዴሚሪስ በአሳቡ ወንበሩ ላይ እንደተቀመጠ ወደኋላው እየተደገፈ ። ካተሪን አሌክሳንደር ከተወገደች የሚያሰጋው ምንም ነገር አይኖርም ። ከዚያ በኋላ ትኩረቱን ሙሉ በሙሉ በሚስቱና በዋርሳው ላይ ያደርጋል ።

"ዛሬ ማታ ከዋናው መሥሪያ ቤት የተላኩ ከፍተኛ እንግዶች ስለሚመጡ በደንብ እንድታስተናግጂአቸው እፈልጋለሁ ።"

የባለቤቷን እንግዶች ካስተናገደች ብዙ ጊዜ ሆኗታል ። ነገሩ

ሚሊናን በጣም አስፈንድቋታል ። ምናልባት ይህ ሁኔታዎችን ይለውጥ ይሆናል ።

የዚያን ዕለቱ የእራት ግብዣ ግን ያስከተለው ለውጥ የለም ። ሰዎቹ መጡ ፤ እራታቸውን በሉ ፣ ተመልሰው ሄዱ ። ግብዣው የተዘቀዘ ነበር ።

ዴሚሪስ ሚሊናን እንደነገሩ ከእንግዶቹ ጋር አስተዋውቆ እርሱ ሲያወጋና ሲሳሳቅ እርሷ ሳትተነፍስ ቁጭ ብላ ታያቸው ነበር ። ኮስታ ምን ያህል ተጫዋች ሰው እንደሆነ ረስታለች ። ደስ የሚሉ ቀልዶችና ተረቶችን እየነገራቸው አልፎ አልፎም ያሞግሳቸዋል ። እንግዶቹ በዚህ ተደስተዋል ። ከአጠገባቸው የተቀመጠውን ሰው ክቡርነት መረዳታቸውን በሚገባ አሳይተዋል ። ሚሊና የመናገር እድል አልነበራትም ። ስትጀምር ኮስታ ያቋርጣታል ። ስለዚህ ማዳመጥን መረጠች ።

'ታዲያ እዚህ ከሱ ጋር እንድገኝ ለምን ፈለገ?' አለች ሚሊና በአሳቧ። ጊዜው መሽቶ ሰዎቹ ሊሄዱ ሲሉ ዴሚሪስ "ነገ በማለዳ ወደለንደን ትበሪያለሽ ። መጠናቀቅ የሚገባቸውን ጉዳዮች ደህና አድርገሽ እንደምታከናውኚ እርግጠኛ ነኝ" አላት ።

ሰዎቹም ሄዱ ።

በሚቀጥለው ቀን የልዑካኑ ቡድን ለንደን ገባ ። ሦስቱ የቡድን አባላት የተውጣጡት ከሦስት የተለያዩ አገሮች ነው ።

ጂሪ ሃሌይ ረዥምና ደልዳላ ቁመና ያለው ፣ ተግባቢ አሜሪካዊ ነው። ፀጉሩን በመጠኑ ሽበት የጀማመረው ሲሆን ፊቱም ፈካ ያለ ነው ። የእጁ ስፋት ካተሪንን እጅግ አስገርሟታል ። እስከዛሬ ካየቻቸው እጆች በጣም ግዙፍ የሆኑና አንድ ነገር ለመሥራት የጓጉ ይመስል የሚቅበጠበጡ እጆች ናቸው ያሉት ።

ፈረንሳዊው ዩቬ ሬናድ በጣም ብልህ ሰው ነው ። አጠር ብሎ ፈርጠም ያለ ቆፍጣናና ተጠራጣሪ ይመስላል ። ሁሌ በአሳብ የተዋጠ መስሎ ይታያል ። 'ጠንቃቃነት' የሚለው ቃል ካተሪን አእምሮ ውስጥ ብልጭ አለ ። 'ግን ከምንድነው የሚጠነቀቀው?' ስትል ካተሪን በሃሳቧ ተደነቀች።



ሦስተኛው የልዑካኑ ቡድን አባል ኢጣሊያዊው ዲኖ ማቱሲ ነው። በቀላሉ የሚግባባ ተጫዋችና ቀልደኛ ሰው ነው ።

"ሚስተር ዴሚሪስ ስለአንቺ በጣም ይጨነቃል" አለ ማቱሲ ።

"በጣም የተቆሻበድኩ መስሎ ይሰማኛል ።"

"በለንደን ቆይታችን የምትንከባከቢን አንቺ መሆንሽን ገልጦልናል ። እዩ ፣ ትንሽ ስጦታ አምጥቼልሻለሁ ።" አንድ የተጠቀለለ ፓኮ ለካተሪን ሰጣት ። ከውስጡ ያለው ከሐር የተሠራ የአንገት ፎጣ ነበር ።

"በጣም አመሰግናለሁ" አለች ካተሪን ።

ወደሌሎቹም ዞር ብላ "ቢሮአችሁን ላሳያችሁ" አለቻቸው ።

ከኋላቸው የዕቃ መውደቅ ድምፅ ሰሙና ዞር አሉ ። አንድ የአሥራ አምስት ዓመት ትንሽ ልጅ ከእጁ ያመለጠው ዕቃ እያሳሰበው ዝም ብሎ ቆሟል ። ሦስት ሻንጣዎችን ይዟል ። ከርደድ ያለ ቡናማ ፀጉርና አረንጓዴ ብሌን ያላቸው ብሩህ ዓይኖች አሉት ።

"ስለክርስቶስ ብለህ" አለ ሬናድ ። "እነኚያን ዕቃዎች በጥንቃቄ ያዛቸው ።"

"ይቅርታ" አለ ልጁ በመርበትበት ። "ይቅርታ አድርጉልኝ ። ሻንጣዎቹን የት ላኑራቸው?"

ሬናድ በችኮላ "ዞር አድርገህ አስቀምጣቸው ፤ በኋላ እናስገባቸዋለን" አለው ።

ካተሪን ልጁን ትኩር ብላ ስትመለከት ኤቨሊን "በአቴንስ የቢሮ ተላላኪ ሆኖ ይሠራ ነበር ፤ አቋረጠና እዚህ አዛወርነው" አለቻት ።

"ስምህ ማነው?" ስትል ካተሪን ጠየቀች ።

"አታናስ ስታቪች ነው እመቤቴ ።" ሊያለቅስ የደረሰ ይመስል ነበር።

"ደህና አታናስ ለሻንጣዎቹ ማስቀመጫ ክፍል ከበስተጓር አለ ። እኔ አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግላቸው አደርጋለሁ ።"

"አመሰግናለሁ እመቤቴ ።"

ካተሪን ወደሰዎቹ ዞር አለች ። "እዚህ ያለውን የሥራችንን ሁኔታ እንደምታጠኑ ሚስተር ዴሚሪስ ገልጦልኛል ። በሚቻለኝ ሁሉ አስፈላጊውን ትብብር አደርግላችኋለሁ ። የሚያስፈልጋችሁ ነገርም ካለ እንዲቀርብላችሁ አደርጋለሁ ። አሁን ጌቶቼ አብራችሁኝ ኑና ከቢሮና ከሌሎች የቢሮው ሠራተኞች ጋር ላስተዋውቃችሁ ።" በኮሪደሩ ላይ ሲጓዙ ካተሪን

ቆም እያለች ከሠራተኞቹ ጋር ታስታዋውቃቸው ነበር ። በመጨረሻ ከዊም ቢሮ ደረሱ ።

“ዊም ፣ እነኚህ ከሚስተር ዴሚሪስ የተላኩ ልዑካን ናቸው ። ዪቪ ሬናድ ፣ ዲኖ ማቱቺና ጄሪ ሃሌይ ይባላሉ ። ከግሪክ የመጡት ገና አሁን ነው ።”

ዊም ገልመጥ ብሎ አያቸው ። “የግሪክ ሕዝብ ብዛት ሰባት ሚሊዮን፣ ስድስት መቶ ሰላሣ ሺህ ብቻ ነው ።” ሰዎቹ ተገርመው እርስ በእርስ ተያዩ ።

ካተሪን ፈገግ አለች ። ለመጀመሪያ ጊዜ ስትተዋወቀው በነበራት ዓይነት መደነቅ ሰዎቹ እንደተደነቁ አየች ።

“ቢሮአችሁ እንዲዘጋጅላችሁ አድርጌአለሁ” አለቻቸው ካተሪን እንግዶቹን ። “አብራችሁኝ ልትመጡ ትችላላችሁ?”

ከዊም ቢሮ ወጥተው በኮሪደሩ ላይ ሲጓዙ ጄሪ ሃሌይ እንዲህ ብሎ ጠየቃት ። “ምን ዓይነት ጉደኛ ሰው ነው? በጣም ጠቃሚ ሠራተኛ ነው ብሎ ሰው የነገረኝ መሰለኝ ።”

“እዎ ነው ” አለችና ካተሪን አባባሉን አረጋገጠችለት ። “ዊም የልዩ ልዩ መምሪያዎችን ሒሣብ በቃሉ አስልቶ ይዟል ።”

“እንዲህ ያለውን ሰው የድመቴ ጠባቂ አድርጌ እንኳን አልቀጥረውም ።” አለ ሃሌይ በንቀት ።

“ምናልባት ወደፊት የበለጠ ስታውቀው ...”

“ከዚህ በላይ ላውቀው አልፈልግም” አለ ፈረንሳዊው በቁጣ ።

“ማረፊያ ሆቴልም አዘጋጅቼላችኋለሁ” አለቻቸው ካተሪን ለልዑካኑ ። “እያንዳንዳችሁ በተለያዩ ሆቴሎች ማረፊያ እንዲያዝላችሁ የምትፈልጉ መሆኑንም ተገንዝቤአለሁ ።”

“እዎ” አለ ማቱሲ ሲመልስ ።

ካተሪን በዚህ ላይ አስተያየት ለመስጠት ፈልጋ መልሳ ተወችው ። በተለያዩ ሆቴሎች ለማረፍ መፈለጋቸውም የእርሷ ጭንቀት አይደለም ።

እያሰበ ካተሪንን በትኩረት ይመለከታታል ። ‘ከገመትኩት በላይ በጣም ቆንጆ ነች ። ይህም መሆኑ ጉዳዩን የበለጠ ያሳምረዋል ። ከዓይኗ ላይ እንደማነበው ብዙ ስቃይ የደረሰባት ትመስላለች ።’



ካተሪን ለእንግዶቹ ቢሮአቸውን አሳየቻቸው ። እንደተረጋጉ ወደቢሮዋ ተመለሰች ። በመተላለፊያው ላይ ፈረንሳዊው ልዑክ በወጣቱ ላይ ሲጮህበት ሰማች ።

“ይህ የኔ ሻንጣ አይደለም ። ደደብ ፣ የእራሴ ሻንጣ ቡናማ ነው ። ቡናማ ነው የምልህ! እንግሊዝኛ ይገባሃል?”

“እዎ ጌታዬ ። ይቅርታ ጌታዬ ።” ድምፁ በፍርሃትና በድንጋጤ ይንቀጠቀጣል ።

‘ስለዚህ ጉዳይ አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ’ አለች ካተሪን በአሳቧ።

ኤቨሊን ኬይ “ለልዑካኑ እንዲደረግላቸው የምትፈልጊው ነገር ካለ ለኔ ንገሪኝ ።” አለቻት ።

“ስለ ትብብርሽ አመሰግናለሁ ኤቬሊን ። ሲያስፈልግ እነግርሻለሁ።”

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አታናስ ስታቪች በካተሪን ቢሮ በኩል ሲያልፍ ካተሪን “እስቲ አንዴ ና!” አለችው ።

ልጁ ሲገረፍ እንደተጠራ ሰው እየተርበተበተ “እሺ እመቤቴ” ብሎ ወደውስጥ ገባ ።

“በሩን ዝጋው ።”

“እሺ እመቤቴ ።”

“ተቀመጥ አታናስ ስምህ አታናስ ነው አይደል ?”

“እዎ እመቤቴ ።”

እንዳይፈራ ሞክራ አልሆነላትም ።

“አይዞህ አትፍራ ።”

“አልፈራሁም እመቤቴ ።”

እንዲህ በፍርሃት የሚያርደው ምን ይሆን ስትል ካተሪን አሰበች ። ስላለፈው ሕይወቱ ለማጥናትም ወሰነች ።

“አታናስ ፣ እዚህ ማንም ችግር ቢፈጥርብህ ወይም ሊፈጥርብህ ቢሞክር ወደ እኔ መጥተህ እንድትነግረኝ ፤ እሺ ?”

ምራቁን ዋጠ ። “እሺ እመቤቴ ።”

ከዚህ በፊት ሰው ቅስሙን የሰበረበት መስሎ ተሰማት ። ችግር ቢያጋጥመው ወደ እርሷ መጥቶ የመናገር ድፍረቱንም ተጠራጠረች ።

“በኋላ እንነጋገራለን” አለች ካተሪን ።

ልውካ ብኮንስታንቲን ዴሚሪስ የተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ለረ ዥም ዓመታት የሰሩ መሆናቸው ስለድርጅቱ አሠራር በሰፊ እንዲያውቁ ረድቷቸዋል ። ካተሪንን ያስደነቃት የተወዳጁ ኢጣሊያዊ የዲኖ ማቴሲ ሁኔታ ነው ። እራሱ መልሱን ማወቅ የሚሻባቸውን ጥያቄዎች ካተሪንን ደጋግሞ ይጠይቃል ። ስለ ለንደኑ ቢሮ አሠራር ለማወቅ የፈለገም አይመስልም ። በእርግጥ ለመናገር ከኩባንያው አሠራር ይልቅ ስለካተሪን የግል ሕይወት ለማወቅ የሚሻ ይመስላል ።

"ባል አለሽ ?" ሲል ማቴሲ ጠየቃት ።

"የለኝም ።"

"ድሮስ አግብተሽ ነበር ?"

"አዎ ።"

"ተፋትተሽ ነው ?"

ውይይቱን በዚሁ ለመግታት "ባሌ ሞቶብኛል" አለች ።

ማቴሲ ሳቅ አለ ። "መቼም እስካሁን አፍቃሪ ጓደኛ ሳይኖርሽ የሚቀር አይመስለኝም ። ምን ማለቴ እንደሆነ ገባሽ ?"

"ምን ለማለት እንደፈለግክ ገብቶኛል" ካለች በኋላ በሃሳቧ 'አንተን ምንም የሚያገባህ ነገር የለም' አለች ። መለሰችና "አንተስ አግብተሃል ?" ስትል ጠየቀችው ።

"ሲ ፡ ሲ ፡ ሚስትና አራት ቆንጆ ልጆች አሉኝ ። እንግዲህ ለሥራ ስለያቸው በጣም ቅር ይላቸዋል ።"

"ለሥራ ወደ ውጭ ብዙ ትዟዟራለህ ሚስተር ማቴሲ ?"

ትንሽ ቅር ተሰኘ ። "ዲኖ በይኝ ዲኖ ፡ ማቴሲ የአባቴ ስም ነው ። አዎ ለሥራ ወደውጭ ብዙ እዟዟራለሁ ።" ፈገግ አለና ድምጹን ቀነሰ ። "አንዳንዴኮ ከቦታ ቦታ መጓዝ ተጨማሪ ደስታን ያስገኛል ። ምን ማለቴ እንደሆነ ግልጽ ሆነልሽ ?"

ካተሪን በፈገግታ "አልገባኝም አለች ።"

ያን ዕለት በስድስት ሰዓት ከሩብ ላይ ካተሪን ወደ ዶክተር ሃሚልተን በቀጠሮዋ ሄደች ። የሚገርመው በተጠሮዋ ቦታ ለመገኘት ያለወትሮዋ በጣም ጓጉታለች ። ባለፈው ጊዜ ልታነጋግረው በመጣችበት ወቅት ምን ያህል ተበሳጭታ እንደነበር አስታወሰች ። አሁን ግን ለችግሯ መፍትሔ



እንደምታገኝ በመተማመን ቢሮውን ከፍታ ገባች ። እስተናጋጅዋ ለምሳ ስለወጣች ወደ ዶክተሩ ቢሮ የሚያስገባው ክፍል ክፍት ነበር ። አላን ሃሚልተን ለቀጠሮው ሲጠብቃት ደረሰች ።

"ነይ ግቢ" አለና ሰላምታ አቀረበላት ።

ካተሪን ወደቢሮው ስትገባ እንድትቀመጥ ወንበር አሳያት ።

"መልካም ፡ ሳምንቱ እንዴት አለፈ ? በጥሩ አሳለፍሺው ?"

የኪርክ ሬኖልድስ እሚሚት ከአዕምሮዋ ውስጥ ጨርሶ ሊጠፋ አልቻለም ። "አዎ ደህና ነበር ያሳለፍኩት ፡ ሥራ በዝቶብኝ ነው የሰነበትኩት" አለች ።

"ይሄማ ላንቺ ጥሩ ነው ። ከኮንስታንቲን ዴሚሪስ ጋር ምን ያህል ጊዜ ሰርተሻል ?"

"አራት ወር ።"

"ሥራሽን ትወጂዋለሽ ?"

"እእምሮዬን ሁልጊዜ ስለሚጠምድልኝና … ስለሌላ ነገር እንዳላስብ ስለሚረዳኝ እወደዋለሁ ። ሚስተር ዴሚሪስ ትልቅ ባለውለታዬ ነው። ምን ያህል እንደረዳኝ በቃላት ልገልጽ አልችል" በማለት ካተሪን ፈገግ አለች ። "ውለታውን እንዴት አድርጌ እንደምከፍለው እኔ እንጃ ። ግን እከፍለዋለሁ ።"

አላን ሃሚልተን ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "ልትነግሪኝ የምትፈልጊውን ብቻ እየመረጥሽ ንገሪኝ ።"

ፀጥታ ሰፈነ ። ጭርታውን ሰብራ "ባለቤቴ የሚስተር ዴሚሪስ አውሮፕላን ነጂ ነበር ። የ… የጀልባ አደጋ ደርሶብኝ ምንም ማስታወስ ከማልችልበት ደረጃ ደረስኩ ። የማስታወስ ችሎታዬ ቀስ በቀስ ሲመለስ ሚስተር ዴሚሪስ ይህንን ሥራ ሰጠኝ" አለችው ።

በሃሳቧም 'የደረሰብኝን ስቃይና ሽብር እርግፍ አድርጌ እየተናገርኩ ነው ። ግን ባለቤቱ ሊገድለኝ እንደነበረ ልገልጽለት ለምን አፈርኩ ? ምናልባት የማልረባ አድርጎ ይገምተኛል በሚል ሥጋት ይሆን ?'

"ለማንኛችንም ቢሆን ስላለፈው ሕይወታችን አንስቶ ማውራት ይከብዳል ።"

ካተሪን ፀጥ ብላ በትኩረት ተመለከተችው ።

"የማስታወስ ችሎታዬ ጠፍቶ ነበር ነው ያልሺው ?"

"አዎ ።"

“የጂልባ አደጋ ደርሶብኝ ነበር ?”

“አዎ ።” ብዙ ነገር ልትነግረው ያልፈለገች ይመስላል ፤ ከንፈሮቿ እንደኩበት ደርቀዋል ። ልንገረው አልንገረው ስትል አመነታች ። በመጨረሻም አፍረጥርጣ ነግራው እርዳታውን ለማግኘት ፈለገች ። በሌላ በኩል ደግሞ አትናገሪ የሚላት ነገር ከውስጧ አለ ።

አላን ሃሚልተን ትኩር ብሎ ስለሁኔታዋ አጠና ። “ከባልሽ ተፋትተሻል ?”

በሀሳቧ ‘አዎ ፤ ተረሽኖ ነው የሞተው’ ካለች በኋላ “ባ… ባሌ … ሞቷል ።” ስትል ተነፈሰች ።

“ሚስስ አሌክሳንደር …” ንግግሩን ለመቀጠል አመነታና “ካተ ሪን ብዬ ብጠራሽ ቅር ትሰኚያለሽ ?”

“አልሰኝም ።”

“እኔንም አላን ብለሽ ጥሪኝ ካተሪን ። ታዲያ የሚያስፈራሽ ምን ነገር አለ ?”

“እንደፈራሁ በምን ገመትክ ?”

“አልፈራሽም ?”

“አልፈራሁም ።” ረዘም ላለ ጊዜ ፀጥታ ሰፈነ ።

እውነቱን ይፋ ለማውጣት በልቦናዋ አምቃ የያዘችውን በቃላት መንዘራ ለመናገረ ፈርታለች ። “ወዳጅ የሚሆኑኝ ሰዎች .. የሚሞቱ ይመስሉኛል ።”

አለመደነቁን ለማሳየት እየሞከረ “ለእነርሱ ሞት ምክንያት እኔ ነኝ ብለሽ ትገምቺያለሽ ?”

“ነኝም — አይደለሁምም ለማለት እችላለሁ ። ብቻ እኔ እንጃ ። ግ… ግራ ገብቶኛል ።”

“በሌሎች ሰዎች ላይ ስለደረሰው ነገር በከንቱ እራሳችንን እንደጥፋ ተኛ እንቆጥራለን ። ባልና ሚስት የተፋቱ እንደሆነ እኛ ነን ምክንያቱ ብለው ልጆቻቸው ይገምታሉ ። አንድ ሰው ሌላውን ተራግሞ በአጋጣሚ ተረጋሚው ኅልፈተ ሕይወት ቢደርስበት ረጋሚው ለዚህ ምክንያቱ እኔ ነኝ ብሎ ያስባል ። እንዲህ ዓይነቱ እምነትና አስተሳሰብ ደግሞ ያልተለመደ አይደለም እና አንቺ …“

“ነገሩ ከዚህም የከበደ ነው ።”

“ነው ?” አለና መልሳ እንድትናገር በጉጉት ጠበቃት ።



ቃላቶቹ ተሸጉጉደጉዱ ። “ባሌ ተገደለ ። እና የእርሱም … እቁባቱ ተገደለች ። ጥብቅና የቆመለት ሁለቱ የሕግ ባለሙያዎችም ሞቱ ። እና አሁን ደግሞ …” ድምጿ እየሰለለ መጣ ። “ኪርክ ሞተ ።”

“ለእነኚህ ሁሉ አሟሟት ምክንያቷ እኔ ነኝ ብለሽ ትገምቺያለሽ ? ይህማ ልትሸከሚው ከሚገባሽ በላይ እራስሽን መጫንሽ ነው ፤ አይመስል ሽም ?”

“… ገፌ የሆንኩ እየመሰለኝ ነው ። ስለዚህም ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት ለመፍጠር አስፈርቶኛል ። ልቋቋም የምችል አይመስለኝም ። አንድ ነገር …”

“ካተሪን ፤ ኃላፊነት ያለብሽ ለማን ሕይወት እንደሆነ ታውቂያለሽ? ለእራስሽ ብቻ ። ለሌላ ለማንም ሊሆን አይችልም ። የሌላውን ሰው ሕይወት ለመቆጣጠርም ሆነ አሟሟቱን ለማስቆም ጨርሶ አትቺይም ፤ የዋህ ነሽና ። ከእነርሱ ሞት ጋር አንቺን የሚያገናኝሽ ምንም ነገር የለም ። ይህ በደንብ ሊገባሽ ይገባል ።”

‘የዋህ ነሽና ። ከእነርሱ ሞት ጋር አንቺን የሚያገናኝሽ ምንም ነገር የለም ።’ ካተሪን ቁጭ ብላ እነኚህን ቃላት በአእምሮዋ ውስጥ አመላለ ሰች ። አባባሎቹን ሙሉ በሙሉ አምና ልትቀበላቸው ፈልጋለች ። ሰዎች የሞቱት በእራሳቸው ምክንያት እንጂ ሰበቧ እርሷ አይደለችም ። የኪርክም ቢሆን ድንገተኛ አደጋ ነው ።

አላን ሃሚልተን ዝም ብሎ ተቀምጦ ይመለከታታል ። ካተሪን ጣራ ጣራውን እየቸና በአሳቧ ‘ደግ ሰው ነው ምነው ቀደም ብዬ ባወቅሁት ኖሮ’ አለች እራሷን እንደ ወንጀለኛ የቆጠረችው ካተሪን ። ጠረጴዛው ላይ ያለውን የአላን ሚስትና የልጁን ፎቶግራፍ ተመለከተች ።

“አመሰግናለሁ” አለች ካተሪን ። “የመከርከኝን ለመቀበል ጥረት አደርጋለሁ ። ከምክርህም ራሴን ለማዋሃድ እሞክራለሁ ።”

አላን ሃሚልተን ፈገግ አለ ። “አብረን እንሞክራለን ። ተመልሰሽ ትመጫያለሽ አይደል ?”

“ምን ?”

“ይህ ሙከራ ነው ፤ ታስታውሺ የለ ? ያኔ እኔ ዘንድ ለመምጣት ስታመነቺ የነበረውን ?”

ካተሪን ወዲያው “አዎ ተመልሼ እመጣለሁ አላን” አለችው ።

እንደወጣች አላን ሃሚልተን እዚያችው ቁጭ ብሎ ስለእርሷ

ማሰቡን ቀጠለ ። በሥራው ላይ በቆየባቸው ባለፉት ዓመታት በርካታ የሆኑ ውብ ሴት ሕመምተኞችን አክሟል ፤ አንዳንዶቹም ሊያሽኮረምሙት ሙከራ ቢያደርጉም ሳይደለል በጠንካራ የሥነ አእምሮ ሐኪምነቱ ቆይቷል ። እንዲህ ዓይነት ንኪኪ ከሕሙማን ጋር መፍጠር ክብር የሆነ ሙያዬን ያዋርዳል ብሎ ያምናል ። እንደዚያ ማድረጉ ለሙያው ግዴታማኝ አለመሆን ነው ይላል ።

የዶክተር አላን ሃሚልተን ወላጆችም በሕክምና ሥራ ውስጥ የነበሩናቸው ። የቀዶ ጥገና ሐኪም የነበረው አባቱ አብራው ትሠራ የነበረችውን ነርስ አግብቶ ነው ሐሚልተን የተወለደው ። አያቱም ቢሆን የታወቀ የልብ ሐኪም እንደነበር ይነገራል ። አላን ገና በልጅነት ዕድሜው ነበር ሐኪም የመሆን ፍላጐት ያደረበት ። ጉጉቱም እንደአባቱ የቀዶ ጥገና ሐኪም ለመሆን ነበር ። በኪንግ ኮሌጅ ውስጥ በሚገኘው የሕክምና ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት አጠናቆ ከተመረቀ በኋላ የቀዶ ጥገና ሕክምና ማጥናት ቀጠለ ።

ወጣቱ በትምህርት ከሚገኝ ዕውቀት ባሻገር የተፈጥሮ ችሎታም ነበረው ። በዚህ መሐል ሰፕቴምበር 1 ቀን 1939 የሂትለር ወታደሮች ፖላንድን ወረሩና ፈረንሳይና ብሪታንያ ወደ ጦርነቱ መግባታቸውን በይፋ አስታወቁ ። የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተጀመረ ።

አላን ሃሚልተን በቀዶ ጥገና ሐኪምነት ተመዘገበ ።

ጁን 22 ቀን 1940 ፣ ለጦርነቱ ግንባር የፈጠሩት አገሮች ማለትም ጀርመንና ኢጣሊያ ፣ ፖላንድ ፣ ኖርዌይና በአካባቢው የሚገኙ አገሮችን ከወረሩ በኋላ ፈረንሳይም በጀርመን እጅ ወደቀች ። ስለዚህ ጀርመንን የመቋቋም ተግባር በብሪታንያ ጫንቃ ላይ ብቻ ወደቀ ።

በመጀመሪያ በቀን ከመቶ የማያንሱ አውሮፕላኖች ተሰልፈው በብሪታንያ ከተሞች ላይ ቦንብ አዘነቡ ። ብዙ ሳይቆይ የቦንብ ጣይ አውሮፕላኖች ቁጥር ሁለት መቶ ደረሰ ። ቀጥሎም ወደ አንድ ሺህ ከፍ አለ ። በዚሁ ሳቢያ የደረሰው እልቂት በአሀዝ ተገልጾ የሚቻል አልሆነም። የቆሰሉትና የሞቱት ሰዎች በየቦታው ወድቀው ይታያሉ ። ከተማዋ በእሳት ጋየች ። ሆኖም ሂትለር ስለእንግሊዞች የነበረው ግምት በጣም የተሳሳተ ነበር ። በቦንብ ድብደባ ጭካኔው እንግሊዞች የበላይነትን



እንዲያገኙ ረድቷቸዋል ። ድብደባው እንግሊዞችን ይበልጥ ያነሳሳቸው ሲሆን ለነፃነቱ ለመሞት እያንዳንዱ የአገሪቱ ዜጋ ዝግጁ ነበረ ።

ቀንም ሆነ ሌሊት እረፍት የሚባል ነገር አልነበረም ። አላን ሃሚልተን አንዳንዴ ያለእንቅልፍ በተከታታይ ለሰልሳ ሰዓታት የሚሰራባቸው ጊዜያት ነበሩ ። የሚያክምበት ድንገተኛ ክፍል በቦንብ ሲደበደብ በሽተኞቹን ወደ ሆስፒታሉ መጋዘን አጓጉዞ ሥራውን ቀጠለ ። በጣም አስቸጋሪ በሆነው ሁኔታ ውስጥ አቅሙ የቻለውን ሁሉ እየሠራ የብዙ በሽተኞችን ሕይወት አተረፈ ።

በኦክቶበር የቦንብ ድብደባው እየባሰበት መጥቶ ነበር ። በአንድ ወቅት የአደጋ ጊዜ ጥሪው ተሰምቶ ሕዝቡ ሁሉ ሮጦ ወደየቀበሮ ጉድጓድ ሲገባ አላን የኦፕራሲዮን ሥራ ያካሄድ ነበር ። ሥራውን አቋርጦ እንዲሸሽ ቢሞከርም በሽተኛዬን ጥዬ አልሄድም ብሎ የቀዶ ጥገናውን ሥራ ቀጠለ። ቦምቡ በአጠገቡ ፈነዳና ከአላን ጋር ይሠራ የነበረ ሐኪም “እባክህ ከዚህ እንውጣ” ብሎ ጠይቆት ነበር ።

“ቆይ አንድ ደቂቃ” አለና የቀደደውን የበሽተኛ ደረት ቀድዶ መጐርጐር ጀመረ ።

“አላን !”

ሥራውን አቁሞ ሊሄድ አልቻለም ። በአካባቢው ፈንጂ እንደበረዶ ሲዘንብ ደንታ ሳይሰጠው በኦፕራሲዮኑ ላይ ብቻ ተመስጧል ። ሕንጻው ላይ የወደቀውን ቦምብ ድምፅ እንኳ አልሰማም ነበር ።

ለስድስት ቀናት ያህል ሕሊናውን ስቶ ሲነቃ በሌላው አካሉ ላይ ከደረሱት ጉዳቶች በተጨማሪ የቀኝ እጁ አጥንቶች መድቀቃቸውን ተረዳ። አጥንቶቹ ተጠግነው የዳነ ቢመስልም ከእንግዲህ የቀዶ ጥገና ሥራ ሊሰራ አይችልም ።

የወደፊቱ ሕይወቱ መበላሸቱን ሲያሰላስል የተነካው አእምሮው መልሶ ለመዳን የዓመት ያህል ጊዜ ፈጅቶበታል ። አንድ የማይረባ የሥነ አእምሮ ሐኪም “ስላለፈው ማዘኑን ትተህ ስለወደፊቱ ሕይወትህ ማሰብ የሚገባህ ከአሁኑ ጀምሮ ነው” አለው ።

"እኮ ምን ዓይነት ሥራ ልሥራ?" ሲል አላን ምርር ብሎ ጠየቀው ።
"እስካሁን የምትሠራውን ሥራ ዓይነት ለየት ባለ ሁኔታ ።"
"አልገባኝም ።"

"አንተ ፈውስ ሰጪ ነህ አላን ። የሰዎችን አካል ታድናለህ ። በርግጥ ከእንግዲህ እንደዚያ ያለ ሥራ ለመሥራት አትችልም ። የሰዎችን አዕምሮ ማዳንም የዚያኑ ያህል በጣም ተፈላጊ ተግባር ነው ። ጥሩ የሥነ አዕምሮ ሐኪም መሆን ትችላለህ ። ብሩህ አእምሮ አለህ ። ለሰዎች አዛኝ ነህ ። እስቲ አስብበት ።"

አላን በሕይወቱ ውስጥ ከወሰናቸው ጠቃሚ ውሳኔዎች ይሄኛው ዋነኛው ነው ። በአዲሱ ሥራው በጣም ተደስቷል ። አሳዛኝ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተስፋ የቆረጡ በሽተኞችን አክሞ መልሰው ጤነኛ አእምሮ እንዲኖራቸው ማድረግ ቀድሞ ከነበረው የበለጠ የመንፈስ እርካታ እየሰጠው ነው ። ስሙ ገንኖ ታዋቂነትንም በማግኘቱ ካለቋሚ ሕመምተኞቹ በስተቀር ለሦስት ዓመት ሌላ አዲስ በሽተኛ ለመቀበል አልቻለም ። ካተሪንን የተቀበላትም ለሌላ ሐኪም ሊያስተላልፋት ሲል ነበር ። ሆኖም የእርሷን ነገር ችላ ሊለው አልቻለም 'ልረዳት ይገባኛል' አለ በአሳቡ ።

ካተሪን ከአላን ሃሚልተን ጋር ከተወያየች በኋላ ወደቢሮዋ ስትመለስ ዊምን ልታነጋግር ሄደች ።

"ዛሬ ዶክተር ሃሚልተንን አነጋገርኩት" አለችው ።

"በእውነት ? ከሥነ አእምሮ ታካሚዎች በቁጥር ደረጃ ስናስቀምጥ መቶዎቹ ባል ወይም ሚስት የሞተባቸው ፤ 73ቱ በልዩ ልዩ ምክንያት የተፋቱ ፤ 65ቱ በእሥር ፤ 63 የቅርብ ዘመድ የሞተባቸው ፤ 63 ልዩ ልዩ አደጋ ወይም ሕመም የደረሰባቸው ፤ 53ቱ በትዳር ፤ 50ዎቹ ከሥራ በመባረራቸው ፤ 47ቱ ..."

ዊም የሚናገረውን ካተሪን ዝም ብላ ቆማ አዳመጠች ። በአሳቧ 'ሁሉንም ከቁጥር አንፃር ብቻ ማየቱ ምን ይመስል ይሆን ? ሰውን እንደሰው አለመቁጠርስ ? እውነተኛ ጓደኛ አለመፍጠርስ ? እኔማ አዲስ ጓደኛ አገኘሁ ። ለመሆኑ አዲሱ ጓደኛዬ ካገባ ምን ያህል ጊዜ ይሆነው ?' አለች ።



# ምዕራፍ ሃያ

## አቴንስ

'ልታጠፋኝ ሞክረህ ነበር ግን አልተሳካልህም ። ግን ሙከራው ቢሳካልህ ምንኛ ይሻልህ ነበር?'

እነኚህ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የተናገራቸው ቃላት አሁንም ከስፓሮስ ላምብሩ ጆሮዎች ውስጥ ያንቃጭላሉ ። ዴሚሪስ ፋክራውን ከግቡ ለማድረስ ወደኋላ እንደማይል ላምብሩ ጠንቅቆ ያውቃል ። 'አምላኬ ፤ የሪዞሊ ስሕተት ምኑ ላይ ይሆን ? ሁሉም በጥንቃቄ ታቅዶ ነበር ።' ከእንግዲህ ስህተቱ ምን እንደነበረ ለማጤን ጊዜ የለም ፤ አስፈላጊው እህቱን ማስጠንቀቁ ላይ ነው ።

የላምብሩ ፀሐፊ ወደቢሮው ገባች ። "የአራት ሰዓት ቀጠሮህ እንደተጠበቀ ነው ። መልእክቱን...?"

"የለም ፤ ቀጠሮዎቹን ሁሉ ሰርዢያቸው ዛሬ ጠዋት ተመልሼ የምመጣ አይመስለኝም ።"

በስልኩ ካነጋገራት ከአምስት ደቂቃ በኋላ ወደሜሊና ገሰገሰ ።

በቪላው አትክልት ውስጥ ሆና ትጠብቀው ነበር ። "ስፒሮስ ፤ በስልኩ ውስጥ ትንሽ የተበሳጨህ ትመስል ነበር ። ምን ችግር ተፈጠረ?"

"መነጋገር አለብን" አላትና በወይን ቅጠል ወደተከበበው አግዳሚ ወንበር ይዟት ሄደ ። ተቀምጦ ዓይን ዓይኗን እያየ 'እንዴት ደስ የምትል ሴት ናት ። ለቀረቧት ሁሉ ደስታን አጎናፅፋለች ። የምትቀጣው ምንም ወንጀል ሳትፈጽም ነው' ሲል አሰበ ።

"ምን ችግር እንዳጋጠመህ ለምን አትነግረኝም?"

ላምብሩ አየር ወደ ውስጥ በኃይል ሳበ ። "የምነግርሽ ነገር ሕመም የሚለቅብሽ ነው የኔ ፍቅር" አላት ።

"ማስጠንቀቂያ ነው?"

“እውነቱን ነው የምነግርሽ ። ሕይወትሽ አደጋ ላይ ነው ።”

“ምን? ማነው አደጋ የሚያደርስብኝ?”

የሚናገራቸውን ቃላት በጥንቃቄ መምረጥ ጀመረ ። “ኮስታ ሊገድልሽ ሳይሞክር የሚቀር አይመስለኝም ።”

ሜሊና አፏን ከፍታ እንደፈዘዘች ቀረች ። “ትቀልዳለህ መሰል ።”

“የምሬን ነው ሜሊና”

“የኔ ፍቅር ፡ ኮስታ ብዙ ብዙ ሊሆን ቢችልም ነፍሰ ገዳይ አይደለም። በፍፁም በፍፁም…”

“ተሳስተሻል ። ከዚህ በፊት ግድያ ፈጽሟል ።”

ፊቷ እየገረጣ መጣ ። “ምንድነው የምትለው?”

“እርሱማ ግድያውን በገዛ እጆቹ አይፈጽምም ። ሰዎችን እየቀጠረ ነው የልቡን የሚያደርሰው ። ማን…”

“ላምንህ አልችልም ።”

“ካተሪን ዶግላስ የተባለችዋን ታስታውሺያለሽ?”

“ያቺ የተገደለችዋ ሴት…”

“አልተገደለችም ። አሁንም በሕይወት ትገኛለች ።”

ሜሊና ጭንቅላቷን ነቀነቀች ። “እንግዲህ የምናገረው ስለሷ አይደለም ማለት ነው ። እኔ የማውቃትን… የገደሏት ሰዎች ተረሽነዋል ።”

ላምብሩ የእህቱን እጅ ሳብ አድርጎ ያዘ ። “ሜሊና አይምሰልሽ ፤ ላሪ ዶግላስና ኖኤሌ ፓጂ ካተሪንን አልገደሏትም ። ፍርድ ቤት በቀረቡበት ወቅት እንኳን ዴሚሪስ ደብቆ አስቀምጧት ነበር ።”

ሜሊና በተቀመጠችበት ድርቃ ቀረች ። በፊት ሰሞን እቤቷ ውስጥ በጨረፍታ ያየቻት ሴት ትዝ አለቻት ።

ምልልሱን አስታወሰች ። ‘በሳሎኑ ውስጥ ያየኋት ሴት ማን ናት’ ስትለው…

‘የአንድ ሸሪኬ ሚስት ናት ። ለንደን በሚገኘው ቢሮዬ ተቀጥራ ልትሠራ መሄዷ ነው’ ሲላት…

በጨረፍታ አይቻታለሁ ። እንዳየቻት አንድ ሰው ትዝ አላት ። ‘የአውሮፕላንህ ነጂ ሚስት ትመስላለች’ ስትለው ‘ከቶ ሊሆን አይችልም እሷንማ ገለዋታል’ ብሎ መለሰላት ።



እንደምንም ታግላ መናገር ጀመረች ። “እቤታችን ውስጥ አይቻት ነበር ስፒሮስ ። ኮስታ ስለእርሷ የነገረኝ ውሸት ነበር ።”

“ሰውዬው ንክ ነው ። ቶሎ ብለሽ ዕቃሽን ሰባስበሽ ከዚህ ሥፍራ እንድትለቂ እፈልጋለሁ ።”

አየችውና ዝቅ ባለ ድምፅ “አይሆንም ይህማ የገዛ ቤቴን ትቼ ?” አለችው ።

“ሜሊና ፣ አንድ ነገር ስትሆኚ ሐዘኑን ልቋቋመው አልችልም ።”

ድምጿ ጉርነን አለ ። “አታስብ ምንም አልሆንም ። ኮስታ ሞኝ አይደለም ፤ አንድ ነገር ቢያደርገኝ አሳር ፍዳውን እንደሚያይ ደህና አድርጎ ያውቃል ።”

“ባልሽ ቢሆንም ደህና አድርገሽ ያወቅሺው አይመስለኝም ። በጣም ፈርቼልሻለሁ ።”

“ሰውዬውን እንዴት አድርጌ እንደምይዘው አውቃለሁ ስፒሮስ ።”

ትኩር ብሎ እንዳያት አሳቧን ሊያስቀይር እንደማይችል ተረዳ ። “የምትሄጂ ከሆነ እንግዲህ በማንኛውም ጊዜ ከሱ ጋር ለብቻችሁ እንዳትሆኑ ቃል ግቢልኝ ።”

የወንድሟን ጉንጭ መታ አደረገችና “ቃል ገብቼልሃለሁ” አለችው።

ሜሊና ለወንድሟ የገባችውን ቃል ለመጠበቅ ሃሣብ አልነበራትም።

ያን ዕለት ምሽት ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከቤት እንደደረሰ ሜሊና ስትጠብቀው አገኘት ። ሲያያት በጭንቅላቱ ብቻ ሰላምታ ሰጣትና አልፏት ወደመኝታ ቤቱ ገባ ። ሜሊናም ተከተለችው ።

“መነጋገር ያለብን ይመስለኛል” አለች ሜሊና ።

ዴሚሪስ ሰዓቱን አየና “የሚኖረኝ ጥቂት ደቂቃ ብቻ ነው ፣ ቀጠሮ አለኝ” አላት ።

“እለህ ? ዛሬ ማታ ደግሞ ልትገድለው ያቀድከው ሰው አለ?”

ፊቱን ወደእርሷ ዞር አደረገ ። “ምንድነው የምትቀባጥሪው ?”

“ዛሬ ጠዋት ስፒሮስ መጥቶ ነበር ።”

“ወንድምሽ እቤቴ እንዳይደርስ ማስጠንቀቂያ ልሰጠው ነው ።”

“ቤቱኮ የእኔም ጭምር ነው” አለች ሜሊና በልበ ሙሉነት ። “ ከእርሱ ጋር ትልቅ ቁምነገር ተወያይተናል ።”

“እውነትሽን ነው? ስለምን ጉዳይ ይሆን?”

“ስለአንተ ፣ ስለካተሪን ዶግላስና ስለኖኤሌ ፓጂ ።”

በትኩረት አዳመጣት ። “ያን ያረጀ ያፈጀ ጥንታዊ ታሪክ!”

“ይመስልሃል? ሁለት ንጹሀን ሰዎችን እንዳስገደልክ ስፒሮስ ነግሮኛል ።”

“ስፒሮስ ሞኝ ነው”

“ሲትዮዋን እኔም እራሴ እዚህ ቤት ውስጥ አይቻታለሁ ።”

“የፈለግሺውን ብታወሪ ማንም ሊያምንሽ አይችልም ። ደግሞ ከእንግዲህ አታዩአትም ። የሚያጠፉትን ሰዎች አሰማርቻለሁ ።”

ለእራት ተገኝተው የነበሩትን ሦስቱን ሰዎች ከመቅጽበት አስታወሰች ። ‘ነገ በማለዳ ወደለንደን ትበሪያለሽ ። መጠናቀቅ የሚገባቸውን ጉዳዮች ደህና አድርገሽ እንደምታከናውኚ እርግጠኛ ነኝ ‘ሲል የተናገራትትዝ አላት ።

ወደሜሊና በጣም ተጠጋና በለስላሳ አነጋገር “መቼም ታውቂያለሽ፣ የአንቺና የወንድምሽ ነገር እጅ እጅ ብሎኛል” አላት ። እጇን ያዘና በኃይል ጠመዘዛት ። “ስፒሮስ ሊያጠፋኝ ሞክሮ ነበር ፣ ቢገድለኝ ይሻለው ነበር ።” አላትና በይበልጥ እጇን ጠመዘዘ ። “ምነው ሞቶ በሆነ ብላችሁ ሁለታችሁም የምትመኙበት ጊዜ ሊመጣ ነው ።”

“ተው እያሳመምከኝ ነው እኮ ።”

“ውድ ባለቤቴ ሆይ እስካሁን የህመምን ምንነት ያወቅሽ ስላልመሰለኝ ለወደፊቱ በደንብ እንድትረጂው አደርጋለሁ ። ” አላትና እጇን ለቀቀው ።

“እፈታሻለሁ ። ደንበኛዋን እንስት ነው ያሰኘኝ ። እንዲህም ሲባል ከሕይወትሽ ውጭ የምሆን አይምሰልሽ ። ለአንቺና ለውድ ወንድምሽ ያሰብኩት ጥሩ እቅድ አለ ። አዎ ፣ በመጠኑም ቢሆን የተነጋገርን መሰለኝ። ይቅርታ አድርጊልኝና ወደውስጥ ገብቼ ልብሴን ልቀይር ። የቀጠርኳትን ሴት ብዙ ማስጠበቅ ተገቢ አይመስለኝም ።”

ዞር አለና ወደልብስ መቀየሪያ ክፍሉ ገባ ። የልብ ትርታዋ የጨመረው ሜሊና እዚያው ቆማ ቀረች ። ‘ስፒሮስ ለካ እውነቱን ነበር ። ሰውዬው እብድ ነው ።’

ተስፋ ብትቆርጥም ለገዛ ሕይወቷ ግድ አልነበራትም ። ‘የምኖረው ለምንድን ነው?’ አለች በአሳቧ ምርር ብሏት ። ባሏ አዋርዷታል ።



በአደባባይ ሳይቀር እየተሳደበ የፈጸመባትን ወራዳ ተግባር ሁሉ አስታወሰች ። በዚህም የተነሳ በጓደኞችዋ ዘንድ መሳቂያና መሳለቂያ ሆናለች ። ከእንግዲህ ለእራሷ መጨነቅን ትታለች ። ‘ለመሞት ዝግጁ ነኝ’ አለች በልቧ ። ‘ስፒሮስ ላይ ጉዳት ሲያደርስ ግን ዝም ብዬ አልመለከትም ።’ ከዚህ ተግባሩ ግን እንዴት አድርጋ ልታድነው ትችላለች ? ስፒሮስ ኃያል ቢሆንም ባለቤቷ ደግሞ ከእርሱ የበለጠ ኃያል ነው ። ሜሊና ዝም ካለችው ባለቤቷ ያሰበውን ነገር ከማድረግ ወደኋላ እንደማይል በሚገባ አውቃለች ። ‘ያም ሆነ ይህ ልገታው ይገባኛል ። ግን እንዴት አድርጌ?…’

# ምዕራፍ ሃያ አንድ

ከአቴንስ የመጡት ልዑካን ካተሪንን በሥራ ወጥረዋታል ። ከሌሎች ኩባንያ ሥራ አስኪያጆች ጋር እንዲወያዩና በለንደኑ ቢሮ የሚከናውነውን ተግባር እየተዘዋወሩ እንዲመለከቱ አድርጋለች ። ሰዎቹ በታታሪነቷና በብቃቷ በጣም ተደንቀዋል ። ስለማንኛውም የሥራ ዘርፍ ጠንቅቃ ማወቋ እርካታን ሰጥቷቸዋል ።

ካተሪን በየዕለቱ በሥራ መጠመዷ ስለችግሯ እንዳታስብ ረድቷታል ። እንግዶቹንም እያወቀቻቸው መጣች ።

ጀሪ ሃሌይ ከቤተሰቡ ውስጥ በጣም የተረገመ ልጅ ነው ። አባቱ የታወቀ የነዳጅ ዘይት ከበርቴ ሲሆን እያቱም ዳኛ ነበሩ ። ጀሪ ሃሌይ ዕድሜው ሃያ አንድ እንደሞላ የሰው ግቢ ሰብሮ በመግባት አውቶሞቢል ሰርቆና የልጃገረድ ክብረ ንፅሕና በጉልበት ደፍሮ በወጣት ጠባይ ማረሚያ ለሦስት ዓመት ታሥሮ ነበር ። ቤተሰቦቹ መጥፎ ባሕሪው ስላንገፈገፋቸው ወደአውሮጳ ላኩት ። "በኋላ እራሴን አርሜ ፡ እንደገና ልስተካከል ችያለሁ " ሲል ካተሪንን አጫውቷት ነበር ።

ዩቬ ሬናድ ኩስተር ያለ ሰው ነው ። ወላጆቹ በርቀት የዝምድና ሐረግ ላይ ለሚገኝ ዘመድ ሰጥተውት ነበር ያደገው ። "አሳዳጊዎቹ በቪቺ አካባቢ እርሻ ስለነበራቸው ከጠዋት ጀምሮ እስከማታ በእርሻው ላይ ያለዕረፍት እንደእህያ ያሠሩኝ ነበር ። ዕድሜዬ አሥራ አምስት ሲሞላ ከዚያ አምልጬ በመሄድ ፓሪስ ውስጥ እሠራ ነበር ።"



ሁሌ ደስተኛውና ፍልቅልቁ ኢጣሊያዊ ፡ ዲኖ ማቱሲ የተወለደው በመካከለኛው የኑሮ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ቤተሰቦች በሲሲሊ ውስጥ ነው ። "ዕድሜዬ አሥራ ስድስት ሲሞላ አሥር ዓመት ከምትበልጠኝና ባል ከነበራት ሴት ጋር በመኮብለል ስሕተት ፈጸምኩ ። ወይኔ ፡ ሴትዮዋ ቤሊሲማ ነበረች ።"

"ከዚያስ?" ስትል ካተሪን ጠየቀች ።

ሳቀ ። " መልሰው ወደቤት አመጡኝና ከሴትዮዋ ባል ቁጣ ሊሸሽጉኝ ወደሮም ላኩኝ ።"

ካተሪን ፈገግ አለች ። "አሃ! በሚስተር ዴሚሪስ ኩባንያ ውስጥ መሥራት የጀመርከው መቼ ነው?"

የማይጨበጥ መልስ ሰጣት ። "በኋላ ላይ ነው ። ቀደም ሲል የእለት ጉርሻ የሚያስገኝልኝ ምናምንቴ ሥራ ስሠራ ነበር ።"

"እና ከዚያ ሚስትህን አገኘህት?"

የካተሪንን ዓይን እያየ "ባለቤቴ እዚህ የለችም" አላት ።

ትኩር ብሎ ተመለከታት ። አነጋገራት ፡ ስትናገር ድምጿን አዳመጠ ፡ የሽቶዋን ጠረን አሸተተ ። ስለእርሷ ሁሉንም ነገር ለማወቅ ፈለገ ። በአረማመዷ እንኳ ሳይቀር ቋምጦ እራቁቷን አልጋ ውስጥ ስትገባ ምን ትመስል ይሆን ብሎ አሰላሰለ ። ምን እንደምትመስል በቅርቡ ይረዳል ። በጣም በቅርብ ጊዜ ። ሊታገስ የሚችል አይመስልም ።

ጀሪ ሃሌይ ወደካተሪን ቢሮ ገባ ። "ትያትር ትወጂያለሽ ካተሪን?"

"ለምን ፡ አዎ እኔ...."

"ፊኒአንስ ሬንቦው የተሰኘ አዲስ ሙዚቃዊ ድራማ ተከፍቷል ። ዛሬ ማታ ላየው እፈልጋለሁ ።"

"ትኬት ላዘጋጅልህ?"

"ለብቻ መግባት ደስ አይልም ። አይመስልሽም? አንቺ ምን ሥራ አለሽ?" ካተሪን አመነታችና "ምንም !" ብላ ቅብጥብጡን እጆቹን ተመለከተች ።

"በጣም ጥሩ! ከምሽቱ በአንድ ሰዓት ከሆቴል መጥተሽ ውሰጂኝ ።" እንደ ትዕዛዝ ነበር አነጋገሩ ። ወደኋላው ዞረና ከቢሮው ወጣ ።

አቀራረቡ ያልተለመደ ሆነባት ። ግልፅነትና የወዳጅነት አቀራረብ ቢያሳያትም... "እራሴን እርግአለሁ" የሚለውን የዚያን ሰውዬ እነኚያን ግዙፍ እጆች ሁኔታ ጨርሳ ልትረሳ አልቻለችም ።

ጄሪ ሃሌይ በሳቮይ ሆቴል መተላለፊያ ላይ ሆኖ ካተሪንን ጠራትና በኩባንያው ሊሞሲን ተሳፍረው ወደትያትር ቤቱ አመሩ ።

"ለንደን ታላቅ ከተማ ናት" አለ ጄሪ ሃሌይ ። "ወደዚህ በመጣሁ ቁጥር ደስ ይለኛል ። እዚህ ለብዙ ጊዜ ቆይተሻል?"

"ለጥቂት ወራት"

"ትውልድሽ አሜሪካ ነው"

"አዎ ፣ ቺካጐ"

"ቺካጐ ትልቅ ከተማ ሆኗል ። እዚያ በጣም ጥሩ ጊዜ አሳልፌአለሁ።"

'የቤቶችን ክብረ ንጽሕና መድፈር?' አለች በአሳቧ ።

ከትያትር ቤቱ ደረሱና ከተመልካቹ ጋር አብረው ተቀመጡ ። ትርዒቱ በጣም ጥሩ ቢሆንም ካተሪን አሳቧን ሰብስባ ልትከታተለው አልቻለችም ። ጄሪ ሃሌይ ጣቶቹን ከወንበሩ ፣ ከጭኑና ከጉልበቱ ጋር እያጋጨ ድምፅ በማሰማት ረብሿት ነበር ። እጆቹ አርፈው ሊቀመጡ አልቻሉም ።

ትርዒቱ ሲያልቅ ሃሌይ ወደካተሪን ዞር አለና " በጣም ጥሩ የምሽት ጊዜ ነው ያሳለፍነው ። ለምን መኪናዋን ትተን በሃይድ መናፈሻ ውስጥ በእግር አንሽራሽርም?" ሲል ጠየቃት ።

"በጠዋት ቢሮ መግባት አለብኝ" አለችው ካተሪን መልሳ ። "ሌላ ጊዜ ቢሆን ይሻላል ።"

ሃሌይ ፊቷን ትኩር ብሎ እየተመለከተ ከአንገት በላይ ፈገግታ አሳያት ። "እንዳልሽ ፤ ወደፊት ብዙ ጊዜ አለን ።"

ዩቬ ሬናድ ሙዚዬሞችን መጐብኘት ይወዳል ። ፈረንሣዊው ካተሪንን "በዓለም ውስጥ ታላቅ ሙዚዬም የሚገኘው በፓሪስ ውስጥ ነው። ሉቭሬን አይተሻል?" ሲል ጠየቃት ።



"አላየሁም" አለች ካተሪን ። "ወደፓሪስ ሄጄ አላውቅም ።"

"አትዩኝም! አንድ ቀን መሄድ ይኖርብሻል ። " እነኚህን ቃላት ሲናገር በአሳቡ ግን 'እንደማትሄጂ አውቃለሁ' አለ ። "በለንደን የሚገኙ ሙዚዬሞችን ለመጐብኘት እፈልጋለሁ ። በመጪው ቅዳሜ ጥቂቶቹን ብናያቸውስ?"

ካተሪን በሚቀጥለው ቅዳሜ የተወዘፉ የቢሮ ሥራዎችን ለማከናወን ዕቅድ ቢኖራትም ኮንስታንቲን ዴሚሪስ እንግዶቹን በደንብ እንድትንከባከባቸው መመሪያ ስለሰጣት "እሺ" አለች ። "ቅዳሜ ይመቸኛል ።"

ካተሪን ቀኑን ሙሉ ከፈረንሣዊው ጋር ለማሳለፍ አልፈለገችም ። 'ሰውዬው ፊቱ የማይፈታ ፣ መከራ ላይ ያለ ነው የሚመስለው' ስትል አሰበች ።

ቀኑ በጥሩ ሁኔታ ተጀመረ ። በመጀመሪያ ወደእንግሊዝ ሙዚዬም ሄደው ጥንታውያን ቅርሶችን እየተዘዋወሩ ጐበኙ ። በቀዳማዊት ኤልሳቤጥ የተፈረመውን የማግና ካርታ ሰነድ ተመለከቱ ። ከማግና ካርታ በፊት መቶ ዓመት አስቀድሞ የተደረጉ የጦርነት ስምምነቶችም በሙዚዬሙ ውስጥ ነበሩ ።

ካተሪንን ስለ ዩቬ ሬናድ አንድ ያሳሰባት ነገር አለ ። በሙዚዬሙ ውስጥ ለአንድ ሰዓት ያህል ከቆዩ በኋላ ነው ነገሩን ልብ ያለችው ።

በአድሚራል ሂልሰን የተጻፈው ዘገባ የተቀመጠበትን መደርደሪያ ይመለከቱ ነበር ።

"እዚህ ውስጥ ከሚገኙት ቅርሶች መካከል ይኸኛው በጣም ግሩም ይመስለኛል" አለች ካተሪን ። "ይህ የተጻፈው አድሚራል ኒልሰን ወደጦርነቱ ከመሄዱ በፊት ነው ። አይገርምህ ፣ ሥልጣን እንዳለው እንኳን ..." ዩቬ ሬናድ እንደማያዳምጣት ወዲያውኑ ተረዳች ። ስታስታውሰው በጉብኝቱ ወቅት በሙሉ ሀሣቡ በቅርሶቹ ላይ ከቶ አልነበረም ። ጉዳዩ ከጉብኝቱ አይመስልም 'ታዲያ ሙዚዬሞችን ለመጐብኘት እፈልጋለሁ ያለኝ ለምንድነው?' አለችና በልቧ ተደነቀች ።

ወደቪክቶሪያና አልቤርት ሙዚዬም ሄደው እዚህም ተመሳሳይ ሁኔታ ተደገመ ። ካተሪን ሁኔታውን በደንብ መከታተል ጀመረች ። ዪቬ ሬናድ ከክፍል ወደክፍል እየተዘዋወረ እንደረካ አልፎ አልፎ ቢናገርም ትኩረቱ በሚያየው ላይ ሳይሆን ውጭ እንደሆነ ይታወቅበታል ። ለማ

ጉብኝታቸውን ሲጨርሱ ካተሪን "ዌስት ሚኒስተር አቤይን የት ትፈልጋለህ?" ብላ ጠየቀችው ።

ዪቬ ሬናድ ጭንቅላቱን እወዛወዘና "እንዴታ በደንብ እፈልጋለሁ" ብሎ መለሰላት ።

ወደታላቁ አቤይ ሲጓዙ እግረ መንገዳቸውን በእንግሊዝ ታሪክ ውስጥ የታወቁ ባለቅኔዎች ፣ የአገሪቱ መሪዎችና ነገሥታት አፅም ያረፈበትን ከድንጋይ የታነፀ የመቃብር ሥፍራ ተመለከቱ ።

"ተመልከት" አለች ካተሪን ። "ይህ የብራውኒንግ መቃብር ነው።"

ሬናድ ዞሮ ተመለከተና "አሃ ፣ ብራውኒንግ!" ብሎ ጉዞውን ቀጠለ ።

ካተሪን በጥሞና ትመለከተው ነበር ። 'የሚፈልገው ምንድን ነው? ለምን ቀኑን እንዲሁ ያቃጥላል?' አለች በአሳቧ ።

ወደሆቴላቸው ለመመለስ ጉዞ እንደጀመሩ ዪቬ ሬናድ እንዲህ አላት፦ "አመሰግናለሁ ሚስስ አሌክሳንደር ። በጉብኝቱ በጣም ተደስቻለሁ ።"

'ውሸቱን ነው' አለች ካተሪን በአሳቧ ። 'ግን ለምን?'

"ስቶንሄንግ የተባለው በጣም አስደሳች ሥፍራ ከሳልስበሪ ሜዳ አጠገብ ይገኛል ሲሉ ሰምቻለሁ ።"

"አዎ" አለች ካተሪን ።

"ታዲያ ቢቻል ለምን በሚቀጥለው ቅዳሜ አንጎበኘውም?"

'ስቶንሄንግ ከሙዚዬሙ ይልቅ ሊያስደስተው ?' ስትል አባባሉን ለመቀበል ተጠራጠረች።

ሆኖም "እሺ ጥሩ ነው" ብላ መለሰች ካተሪን ።

ዲኖ ማቱሲ ምግብና መጠጥ ማማረጥ ይወዳል ። በከተማ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ ሥፍራዎችን የሚጠቁም አነስተኛ መጽሐፍ ይዞ



ወደካተሪን ቢሮ ገባ ። "በለንደን ውስጥ የታወቁ ምግብ ቤቶች ዝርዝር ይዣለሁ ፤ ለመጋበዝ ትፈልጊያለሽ?"

"መልካም ፣ እኔ ..."

"ጥሩ! ዛሬ ማታ ወደኮናውት እንሄድና እራት አብረን እንበላለን ።" ካተሪን "ዛሬ ማታ እኔ..." አለችው ።

"ምክንያት አልቀበልም ። ከምሽቱ በሁለት ሰዓት መጥቼ እውስድሻለሁ ።"

ካተሪን ካመነታች በኋላ "እሺ ደህና ።" ብላ መለሰች ።

የማቱሲ ፊት ፈካ ። "በቤኔ!" አለና ቀና ብሎ ተቀመጠ ። "ለብቻ ልደሰት ቢባል አይሆንም ። አይመስልሽም?" 'አባባሉማ ትክክል ነበር ። ሲያዩትም አደገኛ ሰው አይመስልም ።' ስትል አሰበች ።

በኮናውት የበሉት እራት በጣም ጣፋጭ ነበር ። የተጠበሰ የስኮትላንድ ዓሣና ጥብስ ሥጋ ፤ በፉርኖ ዱቄትና በሥጋ የተጠበሰ እንቁላል ቀርቦላቸው ተመገቡ ።

ቀጥሎ ሰላጣና አትክልት እንደቀረበላቸው ዲኖ ማቱሲ "ካተሪን ፣ ደስ የምትዪኮ ነሽ ። አሜሪካውያን ሴቶችን እወዳለሁ" አላት ።

"አሃ ፣ ባለቤትህ አሜሪካዊት ናት ?" ስትል ካተሪን በየዋህነት ጠየቀችው ። ማቱሲ ትከሻውን ነቀነቀ ። "የለም ፤ ጣሊያዊ ናት ። ቢሆንም ይህን ያህል ችግር የምትፈጥርብኝ ሴት አይደለችም ።"

"ይህማ ላንተ ጥሩ ነው" አለች ካተሪን ።

ፈገግ አለና "በጣም ጥሩ ነው እንጂ" ሲል መለሰ ።

በመጨረሻም ፍራፍሬ እንደቀረበላቸው ዲኖ ማቱሲ እንዲህ አላት፦ " ከከተማ ወጣ ማለቱ አያስደስትሽም? መኪና ያለው ጓደኛ ስላለኝ ለሽርሽር ወጣ ብንልስ?"

ካተሪን እምቢ ልትል ስትል ከመቅጽበት ዊም ታሰባት ። ብቸኛ ስለሆነ ወደገጠር እንሽራሸር ቢባል ደስ ሳይለው አይቀርም ። "ደስ ይለኛል" አለች ካተሪን ።

"በጣም እንደሚያስደስትሽ ቃል እገባልሻለሁ ።"

"ዊም አብሮን ቢሄድ ደስ ይለኛል ።"

ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "መኪናዋ አነስተኛ ናት ። እስቲ እንድትዘጋጅ አደርጋለሁ ።"

ከአቴንስ የመጡት ጐብኝዎች ፍላጐት ብዙ በመሆኑ ካተሪን ለእራሷ ጉዳይ ጊዜው እያነሰባት መጣ ። ሃሌይ ፣ ሬናድና ማቱሲ ከዊም ቫንዲን ጋር ብዙ ጊዜ ተገናኝተው ተነጋግረዋል ። ከጊዜ በኋላ በእርሱ ላይ ያላቸውም አመለካከት እየተለወጠ መምጣቱ ካተሪንን አስደስቷታል ።

"ይህን ሁሉ ያለ ሂሣብ መሣሪያ ነው የሚሠራው?" ብሎ ተደነቀ ሃሌይ ።

"አዎ ።"

"እንዲህ ዓይነት ፍጡር አይቼ አላውቅም ።"

የአታናስ ስታቪችም ሁኔታ ካተሪንን እያስደነቃት ነው ። እንደዚህ ወጣት ያለ ጠንካራ ሠራተኛ አይታ አታውቅም ። ጠዋት ካተሪን ወደቢሮ ስትገባ ሁልጊዜ ቀድሟት በሥራ ላይ ይገኛል ። ማታም ሁሉ ሰው ከሄደ በኋላ ዘግይቶ ይሠራል ። ሁሌ ፈንግተኛ ከመሆኑም በላይ ሰዎችንም ለማስደሰት ይጥራል ። ካተሪን ባየችው ቁጥር ተሸቀጥቋጭ ቡችላ መስሎ ይታያታል ። ባለፈው ሕይወቱ ውስጥ ሰዎች ኀሊናውን የሚያቆስል ጭቆና ያደረሱበት ይመስላል ።

ካተሪን ከእላን ሃሚልተን ጋር ስትገናኝ ስለ አታናስ ልታጫውተው ወስናለች ። 'በእራሱ እንዲተማመን አንድ ነገር መደረግ ይኖርበታል' አለች በእሳቧ ። 'አላን እንደሚረዳው እርግጠኛ ነኝ ።'

"ልጁ ከአንቺ ፍቅር እንደያዘው አታውቂም?" አለቻት ኤቪሊን አንድ ቀን ።

"ምንድነው የምትዪው?"

"ስለአታናስ ነዋ የምናገረው ። የማፍቀር ሁኔታ ከዓይኑ ውስጥ አይታይሽም ? በግ እንደጠፋበት እረኛ ዓይኑን ያንከራትታል ።"

ካተሪን ሳቀች ። "አንቺ ደግሞ የማይሆን ነገር ነው የምታስቢው ።"

ሳታውቅ አታናስን "ምሣ ልጋብዝህ" አለችው ።

"ሬ–ሬስቶራንት ውስጥ?"

ካተሪን ፈገግ አለች ። "አዎ"

ፊቱ ፈካ ። "እ–እንጃ ሚስስ አሌክሳንደር ።" ያልፀዱ ልብሶቹን ተመለከተ ። "ይህንን ለብሼ ካንቺ ጋር ስታይ በሰዎች ዘንድ ላሳፍርሽ እችላለሁ ።"



"እኔ ሰዎችን የምለካው በአለባበሳቸው አይደለም" አለች ካተሪን ቅጭም ብላ ። "ቦታ እንዲያዝልን አደርጋለሁ ።"

አታናስን በሲኖስ ኮርነር ሃውስ ምሣ ጋበዘችው ። ከፊት ለፊቷ ተቀምጦ በአካባቢው በሚታየው ሁሉ መደነቅ ጀመረ ። "እኔ– እኔ ከዚህ ቀደም እንዲህ ዓይነት ቦታ ተገኝቼ አላውቅም ። በጣም የሚያምር ነው ።"

ካተሪን በአነጋገሩ ተነካች ። "የምትፈልገውን ማንኛውንም ነገር ለማዘዝ ትችላለህ ።"

የምግቡን ዝርዝር አነበበና ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "ሁሉም በጣም ውድ ነው ።"

ካተሪን ፈገግ አለች ። "ለዋጋው አትጨነቅ ። እኔና አንተ በጣም ሀብታም የሆነ ሰው ተቀጣሪ ነን ። ደህና ምሣ እንድንመገብ የሚፈልግ ለመሆኑ እርግጠኛ ነኝ ።" የምትከፍልለት እርሷ መሆኗን ግን አልገለጸች ለትም ።

አታናስ የሽሪም ኮክቴል ፣ ሰላጣ ፣ የዶሮ ጥብስና የተጠበሰ ድንች አዘዘና ተመገበ ። በመጨረሻም እንዲመጣለት የጠየቀው የቸኮሌት ኬክና አይስ ክሬም ነበረ ።

ካተሪን ልጁ ሲመገብ በአድናቆት ትመለከተዋለች ። ሰውነቱ ቀጫጫ በመሆኑ "ይህንን ሁሉ የት ነው የምትከተው?" ስትል ካተሪን ጠየቀችው ።

አታናስ በሐፍረት "እኔ እንጃ ፣ ወፍሬ አላውቅም" አላት ።

"ለንደን ደስ ይለሃል አታናስ?"

ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "እስካሁን ባየሁት ተደስቻለሁ ።"

"አቴንስ ውስጥ የቢሮ ተላላኪ ነበርክ?"

አሁንም ጭንቅላቱን በአዎንታ አነቃነቀ ። "አዎ የሚስተር ዴሚሪስ ተላላኪ ነበርኩ" አለ ። ንዴትና ቁጭት ይታይበታል ።

"ሥራውን ትወደው ነበር?"

"ይቅርታ አድርጊልኝና ፣ ስለዚያ ጉዳይ መነጋገሪያ ሥፍራው እዚህ አይመስለኝም ። ግን ሚስተር ዴሚሪስ ጥሩ ሰው አይደለም ። እኔ …እኔ አልወደውም ።" ወጣቱ ልጅ የተናገረውን ነገር የሚሰማበት ሰው ያለ ይመስል ዙሪያውን ተገላምጦ ተመለከተ ። "እርሱ– ለሰው ግድ የለውም።"

ካተሪን ስለዚሁ ጉዳይ እንዲናገር ብዙ ላለመገፋፋት ፈለገች ።

"ለምን ወደ ለንደን ለመምጣት ፈለግህ አታናስ?"

ዝቅ ባለ ድምፅ የተናገረው ለካተሪን አልተሰማትም ።

"ምን አልከኝ? አልሰማሁህም ።"

"ዶክተር ለመሆን ስለምፈልግ ።"

በመገረም ትኩር ብላ አየችው ። "ዶክተር?"

"አዎ እመቤቴ የሞኝ አስተሳሰብ ሊመስልብኝ ይችል ይሆናል ።" ትንሽ አመነታና ንግግሩን ቀጠለ ። "ቤተሰቦቼ የመጡት ከመቅዶንያ ነው። ከልጅነት ጀምሮ ቱርኮች ወደመንደራችን እየመጡ ነዋሪውን ሲያሰቃዩና ሲገድሉ እንደነበር ተደጋግሞ ሲነገር እሰማለሁ ። በቱርኮች ግፍ የቆሰሉትን ወገኖቼን የሚረዱ ሐኪሞች አልነበሩም ። አሁን መንደሩ ተደምስሶ ነዋሪዎቹ ሁሉ ተፈናቅለዋል ። ለዚያ ብቻ ሳይሆን አሁንም በመላ ዓለም ብዙ የቆሰሉና እርዳታን የሚሹ በርካታ ሰዎች አሉ ። እነኚህኑ ለመርዳት እፈልጋለሁ ።" በሐፍረት ዓይኑን አቀረቀረ ። "በአነጋገሬ እብድ ነው ሳትዪኝ አትቀሪም ።"

"አልልም" አለች ካተሪን በለሆሳስ ። "በጣም ጥሩ አሳብ ይመስለኛል ። እና ወደ ለንደን የመጣኸው ስለሕክምና ልታጠና ነው?"

"አዎ እመቤቴ ቀን ቀን እየሠራሁ ማታ ማታ ለመማር እፈልጋለሁ። ዶክተር መሆን አለብኝ ብዬ ቆርጬ ተነስቻለሁ ።"

በአነጋገሩ ላሰበው ነገር ቆርጦ የተነሳ ይመስላል ። ካተሪን ጭንቅላቷን አወዛወዘች ። "ልታደርግ እንደምትችል እተማመናለሁ ። እኔና አንተ ስለዚሁ በሰፊው እንነጋገራለን ። ሊረዳህ የሚችልም ጓደኛ አለኝ ። አንድ የማውቀው ጥሩ ሆቴል አለ ፤ በሚቀጥለው ሳምንት እዚያ ምሣ እንበላለን ።"

እኩለ ሌሊት ላይ በስፒሮስ ላምብሩ ቪላ ቤት ውስጥ ቦንብ ፈነዳ ። ፍንዳታው የቪላውን የፊትለፊት ክፍል አፈራርሶ ሁለት ሠራተኞችን ገድሏል ። የስፒሮስ ላምብሩ መኝታ ክፍልም በፍንዳታው ተደርምሷል ። ላምብሩ ከዚህ አደጋ ሊያመልጥ የቻለው እቤት ለመቆየት የነበረውን አሳብ ቀይሮ የአቴንስ ከተማ ከንቲባ ባደረጉት የእራት ግብዣ ላይ ከባለቤቱ ጋር በመገኘቱ ነው ።

በሚቀጥለው ቀን አንድ ማስታወሻ ወደ ቢሮው ተላከ ። 'ሞት



ለካፒታሊስቶች' ይላል ። የሄሊኒክ አብዮታዊ ፓርቲ ማህተም ሰፍሮበታል ።

"እንዲህ ዓይነት ነገር ለምን ባንተ ላይ ይፈጽማሉ?" ስትል በፍርሃት የተዋጠች ሜሊና ጠየቀችው ።

"እነርሱ አይደሉም" አለ ስፒሮስ ። "ይህንን ያደረገው ኮስታ ነው።"

"እንዲህ – እንዲህ ለማለት ምን መረጃ አለህ?"

"ማስረጃ አያስፈልገኝም ። ያገባሽውን ሰው አሁንም በደንብ አላወቅሽም ማለት ነው?"

"ምን – ብቻ ፣ ምን ለማለት እንደምችል አላውቅም ።"

"ሜሊና ፣ ሰውዬው በሕይወቱ እስካለ ድረስ የሁለታችንም ሕይወት አደጋ ላይ ነው ። ካሰበው ነገር የሚገታው ምንም ነገር አይኖርም።"

"ሄደህ ጉዳዩን ለፖሊስ መንገር አትችልም ?"

"አንቺ እራስሽ ተናግረሽ ጨርሰሽዋል ። ምንም ማስረጃ የለኝም ። ፖሊሶች ሊስቁብኝም ይችላሉ ።" እጇን ሳብ አደረገና ያዛት ። "ከዚህ አካባቢ ዞር እንድትዪ እፈልጋለሁ ። እባክሽ የሚቻልሽን ያህል ርቀሽ ሂጂ ።"

ከነበረችበት ቆማ ቀረች ። በመጨረሻ ቃላት ስትወረውር ከአንድ ውሳኔ ላይ የደረሰች ትመስል ነበር ። "መልካም ስፒሮስ ፣ ማድረግ የሚገባኝን እፈጽማለሁ ።"

እቅፍ አደረጋት ። "ጥሩ ፣ ግን ብዙም አትጨነቂ ። ከዚህ አድራጐቱ የሚገታበትን ዘዴ እንፈልጋለን ።"

ሜሊና ከቀትር በኋላውን በሙሉ በመኝታ ቤቷ ውስጥ ተቀምጣ ስለተፈጸመው ነገር ስታወጣና ስታወርድ ቆየች ። እና ባለቤቷ በፎከረው መሠረት እርሷንና ወንድሟን ለማጥፋት ቆርጦ ተነስቷል ። እጁን አጣጥፋ ልታየው አትችልም ። የእነርሱ ሕይወት አደጋ ላይ እስካለ ድረስ የካተሪን ዶግላስም መኖር በአስጊ ሁኔታ ላይ ነው ለማለት ይቻላል ። 'ለንደን ውስጥ ሥራ ትሠራልናለች ። አስጠንቅቃታለሁ ።' አለች ሜሊና በአሳቧ ። 'ከዚህም የበለጠ ነገር ማድረግ ይገባኛል ። ኮስታን ማጥፋት አለብኝ ። ማንንም ሰው እንዳይጐዳ ማድረግም ይኖርብኛል ። ግን እንዴት ?' ምላሹንም ወዲያው አገኘች ። 'ልክ ነው ብቸኛው መንገድም ያ ብቻ ነው ። ግን እንዴት ቀደም ብሎ አልመጣልኝም ?'

# ምዕራፍ ሃያ ሁለት

## ምሥጢራዊ ማኅደር

### ከካተሪን ዶግላስ ጋር የተካሄደ ውይይት ዶሴ

ካተሪን ፦ በመዘግየቱ ይቅርታ አላን ፡፡ ከቢሮዬ ልወጣ ስል ስብሰባ አጋጠመኝ ፡፡

አላን ፦ ግድ የለም ፡፡ ከአቴንስ የመጡት ልዑካን አሁንም ለንደን ናቸው?

ካ ፦ አዎ ፡፡ በሚቀጥለው – በሚቀጥለው ሳምንት ተመልሰው ሊሄዱ ያስባሉ ፡፡

አ ፦ የሰለቸሽ ይመስለኛል ፡፡ በጣም አስቸግረውሽ ነበር እንዴ ?

ካ ፦ የለም ይህን ያህል እንኳን አልተቸገርኩም ፡፡ ግን…ግን የነሱ ነገር ግራ ግብት ብሎኛል ፡፡

አ ፦እንዴት?

ካ ፦ በቃላት ለመግለፅ ያስቸግረኛል ፡፡ ምናልባት ከሞኝነቴ መንጭቶ ይሆናል… ሁሉም ላይ ለየት ያለ ነገር እያለሁ ፡፡

አ ፦ እንቺን ያስቀየሙት ነገር አለ? አንቺ ላይ …

ካ ፦ የለም ፡፡ ብቻ አሣብ ውስጥ ጣሉኝ ፡፡ ትናንት ማታ እንደገና ያ አስፈሪ ቅዠት መጣብኝ ፡፡

አ ፦ ሰው ከባሕር ሊያሰምጥሽ የሚሞክርበት ሕልም?

ካ ፦ አዎ፡፡ እንደዚያ ዓይነቱን ሕልም ደግሜ ሳላይ ቆይቼ ነበር ፡፡ ያሁኑ ደግሞ ለየት ያለ ነው ፡፡

አ ፦ የሚለየው በምን ዓይነት ነው?

ካ ፦ ነገሩ የበለጠ …እውነታን ያዘለ ይመስላል ፡፡ በፊት ከቆመበት በመቀጠል ረዥም ሕልም ሆኗል ፡፡

አ ፦ ሰው ሊያሰጥምሽ ከሞከረበትም አልፎ ተጨማሪ ሕልም ታየሽ?

ካ ፦ አዎ ፡፡ ሊያሰጥሙኝ ይታገላሉ ፡፡ ወዲያው ሕይወቴ ከተረፈበት ሥፍራ እራሴን አገኘሁ ፡፡



አ ፦ በሴቶቹ ገዳም ውስጥ?

ካ ፦ እርግጠኛ አይደለሁም ፡፡ ሊሆንም ይችላል ግን የአትክልት ቦታ ውስጥ ነው ፡፡ እና አንድ ሰው ሊያነጋግረኝ መጣ ፡፡ እንደሚመስለኝ በፊትም እንደዚያ ዓይነት ሕልም አልሜአለሁ ፡፡ አሁን ግን የሰውዬውን ፊት በደንብ አይቻለሁ ፡፡

አ ፦ ሰውዬው ማን እንደሆነ አውቀሻል?

ካ ፦አዎ ፡፡ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነው ፡፡

አ ፦ እና በሕልምሽ ውስጥ…

ካ ፦ አላን ፣ ነገሩ ሕልም አይደለም ፡፡ እውነተኛው የማስታወስ ችሎታዬ ተመልሶ መምጣቱ ነው ፡፡ አሁን ያለኝን የወርቅ የደረት ጌጥ ሰጥቶኝ የነበረው ኮንስታንቲን ዴሚሪስ መሆኑን አስታውሻለሁ ፡፡

አ ፦ ውስጠ ህሊናሽ ከዚህ በፊት በእውን የተፈፀመውን ይፋ አውጥቶ እንዳሳየሽ አድርገሽ ነው የምትገምቺው? እርግጠኛ ነሽ? ያየሺው…

ካ ፦ እርግጠኛ ነኝ ያንን የደረት ጌጥ በሴቶቹ ገዳም ውስጥ የሰጠኝ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነው ፡፡

አ ፦ በባሕሩ ከመስጠም የተረፍኩት መነኮሳት ደርሰውልኝ ወደገዳሙ ስለወሰዱኝ ነው ብለሽ ታምኚያለሽ?

ካ ፦ በደንብ ፡፡

አ ፦ ካተሪን ፣ የሴቶቹ ገዳም ውስጥ እንደነበርሽ የሚያውቅ ሌላ ሰው አለ?

ካ ፦ የለም ፣ ያለ አይመስለኝም ፡፡

አ ፦ ታዲያ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ እዚያ መኖርሽን እንዴት ሊያውቅ ቻለ?

ካ ፦ እኔ–እኔ እንጃ ፡፡ የማስታውሰው ነገሩ ተፈጽሞ እንደነበረ ነው ፡፡ ከእንቅልፌ የነቃሁትም በፍርሃት ተውጬ ስለነበረ ሕልሙ እንደ ማስጠንቀቂያ ዓይነት ነገርም መስሎ ተሰምቶኛል ፡፡ አንድ አደገኛ ነገር ይፈጸምብኛል የሚል ስጋት አድሮብኛል ፡፡

አ ፦ በእርግጥ ቅዠት እንደዚያ ዓይነት ሥጋት እንዲያድርብን ያደርጋል፡፡ ቅዠት የሰው ልጅ ጠላት ነው ፡፡ ዘመኑ ያለፈበት ከንቱ እምነት እንደሚያወሳው ከሌሊቱ ከአሥር ሰዓት በኋላ ነው ሰው በቅዠት የሚጨነቀው ይባላል ፡፡

ካ ፦ ከእውነት ጋር የተያያዘ ትርጉም የላቸውም ነው የምትለው?

አ ፦ አንዳንዴ ሊኖራቸው ይችላል ። ኮለሪጅ ሲፅፍ “ሕልም ጥላ ሳይሆን የሀዘኔና የሕይወቴ ቁም ነገር ነው” ብሏል ።

ካ ፦ እንደትልቅ ቁም ነገር አጋንኜ ተርጉሜው ይሆናል ። ብቻ ከዚህ አስፈሪ ቅዠት በስተቀር ደህና ነኝ ። አሃ ፣ ስለአንድ ሰው ላነጋግርህ እፈልጋለሁ አላን ።

አ ፦ እሺ ።

ካ ፦ አታናስ ስታቪች ይባላል ። ወደለንደን የሕክምና ትምህርት ሊከታተል የመጣ ወጣት ነው ። ሕይወቱ ወጣ ገባ የበዛበት ይመስላል ። አንድ ቀን አግኝተኸው ጥሩ ምክር ብትሰጠው ይጠቅመዋል ብዬ እገምታለሁ ።

አ ፦ ደስ ይለኛል ። ግን ግንባርሽን ለምንድነው የምትቋጥሪው?

ካ ፦ አንድ ነገር ትዝ ብሎኝ ነው ።

አ ፦ ምን?

ካ ፦ የማይረባ ነገር ነው ።

አ ፦ ውስጠ ኅሊናችን ይረባል አይረባም አይልም ።

ካ ፦ በሕልሜ ሚስተር ዴሚሪስ የወርቅ የደረት ጌጡን ሲሰካልኝ…

አ ፦ እሺ?

ካ ፦ “ሊገድልሽ ነው” የሚል ድምፅ ሰማሁ ።

‘ድንገተኛ አደጋ መምሰል አለበት ። ማንም ሬሳዋን ለይቶ እንዲያውቅ አልፈልግም ።’ እርሷን ለመግደል ብዙ ዘዴዎች አሉ ። ካሁኑ ዝግጅት ማድረግ ሊኖርበት ነው ። አልጋው ላይ ተንጋሎ ስለአገዳደሏ ሲያሰላስል የወሲብ ፍላጐቱ ተቀሰቀሰበት ። የመጨረሻ ደረጃ እርካታውን የሚያስገኝለት ሞት ነው ። ይህም እንዴት እንደሚከናወን ወደኋላ ላይ ተገልጾላታል ። ቀላል ጉዳይ ነው ። ምስጢሩን ሊያውቅ የሚችል በሕይወት የተረፈ ላይገኝ ነው ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስንም በጣም ደስ ይለዋል ።



# ምዕራፍ ሃያ ሦስት

የኮንስታንቲን ዴሚሪስ መዝናኛ ቤት ከፒራኡስ ወደብ ሦስት ማይልስ ያህል ርቆ ከባሕሩ ዳርቻ ላይ ይገኛል ። ዴሚሪስ ከምሽቱ በአንድ ሰዓት ላይ እዚያ እንደደረሰ መኪናውን ከጎዳናው ጥግ አቁሞ ከፈተና ወርዶ ወደቤቱ አመራ ።

እንደደረሰ በማያውቀው ሰው በሩ ተከፈተለት ።

“እንደምን አመሸህ ሚስተር ዴሚሪስ ።” ዴሚሪስ በርካታ ፖሊሶችን እቤቱ ውስጥ አየ ።

“እንዴ! እዚህ ምን ትሠራላችሁ?” ሲል ዴሚሪስ ጠየቀ ።

“እኔ የፖሊስ መቶ አለቃ ቲዮፊሉስ ነኝ ። እኔ…”

ዴሚሪስ ወደጎን ገፈተረውና ወደሳሎኑ ገባ ። ቤቱ ተመሰቃቅሏል ። ድብልቅልቁ የወጣ ትንቅንቅና ግርግር የተካሄደበት ይመስላል ። ጠረጴዛዎችና ወንበሮች ተገለባብጠዋል ። ዴሚሪስ ፣ ተቀዶ ከወለሉ ላይ የተጣለውን የሜሊና ልብስ ትኩር ብሎ አየው ።

“ባለቤቴ የት ነው ያለችው? ከእርሷ ጋር እዚህ ለመገናኘት ቀጠሮ ነበረን ።”

መቶ አለቃው “እዚህ የለችም ። ቤቱ ውስጥና ውጪም የባሕር ዳርቻውን ዙሪያ ፈልገናት አላገኘናትም ። ቤቱ በሌባ ሳይመዘበር አልቀረም ።”

“እና ታዲያ ሜሊና የት ናት? እሷ ናት የደወለችላችሁ? እዚህ ነበረች እንዴ?”

“አዎ ፣ እዚህ የነበረች ይመስለናል ጌታዬ ።” አንድ መስታወቱ የተሰበረበት የቤት ሰዓት በእጁ ይዟል ። ሰዓቱም ልክ ዘጠኝ ላይ ቆሟል ። “ይህ የባለቤትህ ሰዓት ነበር ?”

“እዎ ይመስላል ።”

ከሰዓቱ ጀርባ ላይ “ለሚሊና ከአፍቅሮት ጋር የተሰጠ – ኮስታ” የሚል ጽሑፍ ሰፍሯል ።

“እዎ ነው ። ለልደት በዓሏ ያበረከትኩላት ስጦታ ነበር ።”

መርማሪ ቲዮፊሉስ ወደ ምንጣፉ አመለከተ ። “እነዚህ የደም ነጠብጣቦች ናቸው ። አሻራው እንዳያልፍበት ተጠንቅቆ መሬት ላይ የወደቀውን ጩቤ አነሳ ። የጩቤው ስለት በደም ተበክሏል ።

“ይህንን ጩቤ ከዚህ በፊት አይተህ ታውቃለህ ጌታዬ ?”

ዴሚሪስ ለአጭር ጊዜ ጩቤውን ተመለከተ ። “እንዴ! ሞታለች ልትለኝ ነው?”

“መሰለኝ ጌታዬ ። በእሸዋው ላይ የታየንን የደም ነጠብጣብ እየተከተልን ስንሄድ ከባሕሩ አጠገብ አደረሰን ።”

“አቤት አምላኬ !” አለ ዴሚሪስ።

“እንዳጋጣሚ በጩቤው ላይ የጣት አሻራ ቀርቶልናል ።”

ዴሚሪስ ወንበሩ ላይ ዘፍ አለ ።

“እንዲያ ከሆነ ልትይዙት ትችላላችሁ ።”

“የጣት አሻራው በማኅደራችን ውስጥ ካለው ጋር ከተመሳሰለ እንይዘዋለን ። በቤቱ ውስጥ በርካታ የጣት አሻራዎች አግኝተናል ። እና እየለየን ማገናዘብ ሊኖርብን ነው ። ሚስተር ዴሚሪስ የጣት አሻራህን ልትሰጠን ትችላለህ?”

ዴሚሪስ ካመነታ በኋላ “እሺ ምንም ችግር የለም ።”

“ለዚያኛም የሃምሣ አለቃ ስጠው ።”

ዴሚሪስ የደንብ ልብስ ለብሶ የጣት አሻራ መቀበያውን ወደያዘው ፖሊስ ሄደ ። “እባክዎ ጌታዬ ፣ ጣትዎችዎን እዚህ ላይ ያኑሩት” አለውና ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሥራው ተጠናቀቀ ። “እንዲሁ ለደንቡ ስንል ነው ።”

“ይገባኛል ።”

የመቶ አለቃ ቲዮፊሉስ ለዴሚሪስ ካርድ ሰጠው ። “ሚስተር ዴሚሪስ ፡ ስለዚህ የምታውቀው ነገር አለ ?”

ዴሚሪስ ካርዱን ሲያይ “ካቴላኖስ የምርመራ ድርጅት—የግል ተቋም” የሚል ተጽፎበታል ። ካርዱን መልሶ ለመቶ አለቃው ሰጠው ። “የማውቀው ነገር የለም ። ግን ካርዱ ከጉዳዩ ጋር የተያያዘ ነው ?”



“አላውቅም ፤ እያጣራን ነው ።”

“በጣም ጥሩ ፣ ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ማን እንደሆነ ለማረጋገጥ የሚቻልህን ሁሉ እንድታደርግ እፈልጋለሁ ። ባለቤቴ የተናገረችው ነገር ካለም ብትነግረኝ ደስ ይለኛል ።”

የመቶ አለቃ ቲዮፊሉስ እየውና በአዎንታ ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። “አታስብ ጌታዬ ሁሉንም ነገር እናደርጋለን ።”

ሚሊና ፣ ቆንጆ ፣ ብሩህና ደስ የምታሰኘዋ ወርቅ ልጅ ። ቀደም ሲል ሁሉም ነገር አስደሳች ነበር ። ከዚያ በኋላ ግን ወንድ ልጃቸውን በመግደሏ ይቅርታ የማይደረግላት ሆነ ። የጠበቃት ሞት ብቻ ነው ።

* * *

የስልክ ጥሪው የተደረገው በሚቀጥለው ቀን ስድስት ሰዓት ላይ ነበር ። ፀሐፊው የውስጥ ስልክ ጥሪ ስታደርግለት ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ስብሰባ በማካሄድ ላይ ነበረ ።

“ይቅርታ ሚስተር ዴሚሪስ ...”

“እንዳታቋርጪኝ ብዬሽ አልነበረም ?”

“ነበር ጌታዬ የፖሊስ ባልደረባው ተቆጣጣሪ ላቫኖስ በስልኩ መስመር ላይ ሆኖ ነገሩ በጣም አስቸኳይ ነው ስላለኝ ነው ። ስብሰባ ላይ ስለመሆንህ እንድነግረው ...”

“ግድ የለም አነጋግረዋለሁ ።” ዴሚሪስ በስብሰባ ጠረጴዛው ዙሪያ ወደተቀመጡት ሰዎች ዞር አለ ። “ለጥቂት ጊዜ ይቅርታ አድርጉልኝ ጌቶቼ” ብሎ የስልኩን እጀታ አንስቶ “ዴሚሪስ ነኝ” አለ ።

“ሚስተር ዴሚሪስ ፣ ከማዕከላዊ ጣቢያ ተቆጣጣሪ ላቫኖስ ነኝ ። ይጠቅምሃል ብለን የምንገምተው አንድ መረጃ አለን ። ወደፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ለመምጣት ትችላለህ ?”

“የባለቤቴን ጉዳይ ደረሳችሁበት ?”

“በስልክ ባንነጋገር አይሻልም ?”

ዴሚሪስ ትንሽ አመነታ ። “አሁኑኑ እመጣለሁ ።” ስልኩን ዘጋና

ወደ ሰዎቹ ዞር አለ ። "አንድ አስቸኳይ ጉዳይ አጋጥሞኛል ። ለምን ወደምግብ አዳራሹ ገብታችሁ ባቀረብኩት አሳብ ላይ አትወያዩም ? እኔም ተመልሼ በምሳ ላይ እንገናኛለን ።"

በአሳቡ ተስማሙ ። ከአምስት ደቂቃ በኋላ ዴሚሪስ ወደ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያው ጉዞውን ቀጠለ ።

በርካታ ሰዎች በፖሊስ ኮሚሽነሩ ቢሮ ውስጥ ይጠብቁት ነበር ። ዴሚሪስ በባሕር ዳርቻ ቤቱ ውስጥ ያያቸውን ፖሊሶች አስታወሳቸው ።
"... ይህ ዴልማ ይባላል ። ልዩ የሕግ አስከባሪ ነው ።"

ዴልማ ከቁመቱ አጠር ብሎ ደንደን ያለ ፣ ቅንድቡ ግጥም ያለ ፣ ተጠራጣሪ ዓይኖች ያሉት ፣ ራቁ ክብ የሆነ ሰው ነው ።

"እንዴት ሆነ ?" አለና ዴሚሪስ ጠየቀ ። "ስለ ባለቤቴ አወቃችሁ?"

ዋናው ተቆጣጣሪ እንዲህ አለ፦— "ሚስተር ዴሚሪስ በግልጽ ለመናገር ያህል አንድ በጣም ግራ የሚያጋባ ነገር አጋጥሞናል ። ይህን በተመለከተ እንደምትረዳን ተስፋ እናደርጋለን ።"

"ብዙም ልረዳችሁ የምችል አይመስለኝም የሚዘገንን ነገር ነው ። ..."

"ባለቤትህን ትናንት ከሰዓት በኋላ በባሕር ዳርቻው ቤትህ ልታገኛት ቀጠሮ ሰጥተሀት ነበር ?"

"ምን ? በፍጹም ። ሚስስ ዴሚሪስ ራሷ ናት ደውላ በአንድ ሰዓት እንድንገናኝ የጠየቀችኝ ።"

የሕግ አስከባሪው ዴልማ በእርጋታ "እኛንም ያምታታን ይኸው ነው። በስምንት ሰዓት ገደማ ለባለቤትህ ስልክ ደውለህ ወደባሕር ዳርቻው ቤትህ ብቻዋን ሄዳ እንድትጠብቅህ እንደነገርካት የቤት ሠራተኛህ ነግራናለች ።"

ዴሚሪስ ግንባሩን ቋጠረ ። "ተምታቶባት ነው ። ከምሽቱ በአንድ ሰዓት ቤቱ ውስጥ እንድንገናኝ ደውላ የጠየቀችኝ ባለቤቴ ናት ።"

"እሺ ። እና ሠራተኛዋ ተሳስታለች ማለት ነዋ !"

"ያለጥርጥር ።"



"ባለቤትህ ወደ ባሕር ዳርቻው ቤት እንድትመጣ አንተን የጠየቀችበት ምክንያት ምን ይመስልሃል ?"

"እንድፈታት ልትጠይቀኝ ይመስለኛል ።"

"ልትፈታት ማቀድህን ለባለቤትህ ገልጸህላት ነበር ?"

"አዎ ።"

"ሚስስ ዴሚሪስ ልትፋታ እንደምትፈልግ በስልክ ስትነግርህ መስማቷን የቤት ሠራተኛዋ ነግራናለች ።"

"ሠራተኛዋ ለምትቀባጥረው ደንታ የለኝም ። ቃሏን አምናችሁ መቀበል ይኖርባችኋል ።"

"የዋና ልብስህን በባሕር ዳርቻ ቤት ውስጥ ነው የምታኖረው ?" ሲል ዋናው ተቆጣጣሪ ጠየቀ ።

"በባሕር ዳርቻ ቤት ውስጥ ? በፍጹም በባሕር ውስጥ መዋኘት ከተውኩ ዓመት አልፎኛል ። የምዋኘው በከተማ በሚገኙት ቤቶች አካባቢ በሠራኋቸው የመዋኛ ቦታዎች ነው ።"

ዋናው ተቆጣጣሪ የጠረጴዛውን መሳቢያ ከፈተና የፕላስቲክ

ከረጢት አውጥቶ የዋና ልብሶችን እየመዘዘ ለዴሚሪስ አሳየ ።
"እነዚህ የዋና ልብሶችህ ናቸው ሚስተር ዴሚሪስ ?"

"የእኔ ሊሆኑ ይችላሉ አዎ ይመስለኛል ።"

"ስምህ በላያቸው ተጽፏል ።"

"አዎ ። አስታውሳለሁ ፤ የእኔ ናቸው ።"

"ከባሕር ዳርቻው ቤት ውስጥ ከቁም ሳጥን ሥር ነው ያገኘናቸው ።"

"እና ! ምናልባት ከረዥም ጊዜ በፊት እዚያው ተትተው ይሆናል ። ለምን ... ?"

"ልብሶቹ በውሀ ርሰዋል ። የተካሄደው ምርመራ እንደሚያመለክተው ልብሱን ያራሰው ውሀ ቤቱ ፊት ለፊት ካለው የባሕር ውሀ ጋር አንድ ዓይነት ነው ። በልብሶቹ ላይ የሚታየው ቀያይ ነገር ደም ስለመሆኑ ተረጋግጧል ።"

ክፍሉ በጣም ይሞቅ ጀመር ።

"እና ሌላ ሰው ለብሶት ነበር ማለት ነው" አለ ዴሚሪስ ቆፍጠን ብሎ ። ልዩ ሕግ አስከባሪው "ለምን ብሎ ሌላ ሰው ይለብሰዋል ? ግራ

የገባንም ይሄው ነው ሚስተር ዴሚሪስ ።”

ዋና ተቆጣጣሪው ኤንቬሎፕ ከፈተና የወርቅ አዝራር አወጣ ። “እንዱ መርማሪዬ ይህንን ከምንጣፉ ሥር አገኘው ። ይህን አይተህ ታውቃለህ ?”

“አይቼ አላውቅም ።”

“ከአንደኛው ጃኬትህ ላይ የተበጠሰ ነው ። በተሰጠን ሥልጣን መሠረት ዛሬ ጠዋት ወደ ቤትህ ሄደን ቁምሳጥኑን ስንፈትሽ የአንደኛው ጃኬትህ ቁልፍ ተበጥሶ ነው ያገኘነው ። ቁልፉ የተሰፋበትም ክር ከሌላው ጋር አንድ ነው ። ጃኬቱም ከላውንደሪ የወጣው ከሳምንት በፊት መሆኑን ተረድተናል ።”

“እኔ እንጃ …”

“ሚስተር ዴሚሪስ ፣ ባለቤትህን ልትፈታ መፈለግህን እንደነገርካትና እርሷም ስለዚሁ ልታነጋግርህ እንደምትፈልግ ገልጠህልን ነበር ።”

“ትክክል ነው ።”

ከአንድ ቀን በፊት በባሕር ዳርቻው ቤት ውስጥ ለዴሚሪስ ስለተሰጠው ካርድ ተቆጣጣሪው አነሳ ። “እንዱ ባልደረባችን ዛሬ የካቴላኖስን የምርመራ ድርጅት ጎብኝቶ ነበር ።”

“እኔኮ ነግሬሃለሁ—ስለዚህ ድርጅት ሰምቼ አላውቅም ።”

“ባለቤትህ እራሷን ለማስጠበቅ ቀጥራቸው ነበር ።”

የሰማው በጣም አስደንጋጭ ሆነበት ። “ሜሊናን ? ከምን እንዲጠብቋት ?”

“ከአንተ እንዲጠብቋት ። ባለቤትህ እፈታሃለሁ እያለች ታስፈራራህ እንደነበረ የድርጅቱ ባለቤት ገልጦልናል ። አንተም በዚህ አሳቧ የምትገፋበት ከሆነ እንደምትገላት ማስጠንቀቂያ እንደሰጠሀት ተረድተናል ። ሚስትህ ለምን ለጥበቃ ወደ ፖሊሶች ዘንድ እንደማትሄድ ቢጠይቃት ጉዳዩ በምስጢር መያዝ ስላለበት መሆኑን ነግራዋለች ። በይፋ እንዲታወቅ አልፈለገችም ነበር ።”

ዴሚሪስ ተነስቶ ቆመ ። “እኔ እዚህ ዝም ብዬ ተቀምጬ ይህን ሁሉ ውሸት ላዳምጥ አልችልም ። ምንም …”

ተቆጣጣሪው የጠረጴዛ ኪሱን ሳበና ከባሕር ዳርቻ ቤቱ ውስጥ የተገኘውንና በደም የተበከለውን ጩቤ አወጣ ።

“በባሕር ዳርቻ ቤቱ ውስጥ መኮንኑ በጠየቀህ ጊዜ ጩቤውን



አይተኸው እንደማታውቅ ገልጸህለት ነበር ።”

“ትክክል ።”

“ግን በጩቤው ላይ ያለው የጣት አሻራ ያንተ ነው ።”

ዴሚሪስ ጩቤውን አተኩሮ አየ ። “የእኔ—የእኔ የጣት አሻራ ? ተሳስታችኋል ። ግምታችሁ ትክክል አይደለም ።”

አእምሮው ተበታትኖ በአሳብ መብከንከን ጀመረ ። እስካሁን በእርሱ ላይ ስለተጠናቀሩት ማስረጃዎች ማሰላሰል ጀመረ ። ‘የቤት ሠራተኛዋ እንዳለችው በስምንት ሰዓት ለሚስቱ ደውሎ ወደባሕር ዳርቻው ቤት ብቻዋን እንድትሄድ መንገሩ … በሁለት የመዋኛ ትጥቅ ላይ የደም ነጠብጣቦች መታየታቸው … ከጃኬቱ የተበጠሰ አዝራር … የጣት አሻራው ያለበት ጩቤ ።’

“ይህ ሆን ተብሎ የተቀነባበረ ስለመሆኑ እናንተ ደደቦች አይገባችሁም ?” አለና አንቧረቀባቸው ። “ሌላ ሰው የዋና ልብሶቹንና ጩቤውን ወደ ባሕር ዳርቻ ቤቱ ወስዶ ደም ቀብቶዋቸው የጃኬቱን አዝራር ደግሞ በጥሶ …”

ልዩ ሕግ አስከባሪው አቋረጠው ። “ሚስተር ዴሚሪስ ፡ የጣት አሻራህ እንዴት በዚህ ጩቤ ላይ ሊያርፍ እንደቻለ ልታስረዳን ትችላለህ ?

“እኔ—እኔ አላውቅም … ቆዩኝ ። አዎ አሁን አስታወስኩ ። ሜሊና የተጠቀለለ ፓኮ እንድከፍትላት ይህንን ጩቤ ሰጥታኝ ነበር ። የጣት አሻራዬም በጩቤው ላይ የተገኘው ፓኮውን ስቀድበት ነው ።”

“ጥሩ ፣ በፓኮው ውስጥ ምን ነበር ?”

“እኔ … አላውቅም ።”

“በፓኮው ውስጥ ምን እንደነበረ አታውቅም ?”

“አዎ አላወቅኩም ። ፓኮው ታስሮበት የነበረውን ገመድ ብቻ በጥሼ ሰጠኋት ። እኔ ፊት አልከፈተችውም ።”

“በምንጣፉ ላይ ባሕሩ አጠገብ እስኪደርስ ድረስ በአሸዋው ላይ የተንጠባጠበውን ደም ሁኔታስ ልትገልጽልን ትችላለህ ? …”

“እርሱማ ግልጽ ነው” አለ ዴሚሪስ ። ወዲያው “ሜሊና ራሷን ትንሽ አድምታ እኔ የገደልኳት ለማስመሰል እስከባሕሩ ድረስ ደሟን እያንጠባጠበች ሄደች ። ልፈታት በማሰቤ ልትበቀለኝ ብላ ነው እንዲህ ያደረገችው። ይሄኔ የምታስሩኝ እየመሰላት አንድ ቦታ ተደብቃ እየሳቀች ነው ። ሜሊና እንደኔው በሕይወት ትገኛለች” በማለት ተናገረ ።

ልዩ የሕግ አስከባሪው ተስፋ በቆረጠ አነጋገር እንዲህ አለ፦—
“ጌታዬ እንደምትለው ቢሆን ደስ ባለን ነበር ። አስከሬኗን ዛሬ ጠዋት ነው ከባሕሩ ውስጥ ያወጣነው ። በጩቤ ተወግታ ከባሕሩ ሰምጣ ነው ያገኘናት ሚስተር ዶሚሪስ ። ባለቤትህን በመግደልህ በቁጥጥር ሥር ውለሃል ።”



# ምዕራፍ ሃያ አራት

መጀመሪያ ላይ ሜሊና እንዴት አድርጋ እንደምታከናውነው ምንም አሳብ አልመጣላትም ነበር ። የምታውቀው ነገር ቢኖር ባሏ ወንድሟን ለማጥፋት ቆርጦ መነሳቱንና ይህ እስኪሆን ደግሞ እጇን አጣጥፋ እንደማትቀመጥ ብቻ ነበር ። ያም ሆነ ይህ ኮስታ መገታት ነበረበት ። ለራሷ ሕይወት ጨርሶ አልተጨነቀችም ። ቀኑም ሆነ ሌሊቱ በስቃይና በተስፋ መቁረጥ የተመላ እየሆነባት መጣ ። ይህንን ጋብቻ እንዳትፈጽም ስፒሮስ እንዴት አስጠንቅቋት እንደነበር አስታወሰች ። ‘ዶሚሪስን ልታገቢው አትቺዪም ። ሰውዬው የለየለት አረመኔ ነው ፤ ያጠፋሻል ።’ ወንድሟ እውነቱን ነበር ። ያኔ ምክሩን እንዳትቀበል ፍቅር አሳውሮአታል ፤ አሁን ግን ባሏ መደምሰስ ይኖርበታል ። ግን እንዴት? ‘እንደኮስታ አስቢ’ የሚል ከአእምሮዋ መነጨ ። አዎ እንደሱ አሰበች ። ምን እንደምታደርግ ጠዋቱን ዝርዝር እቅድ ነድፋለች ። ከዚያ በኋላ ቀላል ነበር ።

ሜሊና ወደውስጥ ስትገባ ኮንስታንቲን ዶሚሪስ ጥናት ክፍሏ ውስጥ ተቀምጦ ይሠራ ነበር ። በጠንካራ ገመድ የታሠረ ፓኮ ታቅፋለች ። በእጇም ትልቅ ጩቤ ይዛለች ።

“ኮስታ ይህንን ገመድ ቆርጠህ ፓኮውን ልትከፍትልኝ ትችላለህ? እኔ አልቻልኩበትም ።”

ቀና ብሎ አያትና በመሰልቸት ስሜት “ድሮስ ልትችይበት ኖሯል? ጩቤን ስለቱ ላይ መያዝ አግባብ እንዳልሆነ አታውቂም?” ጩቤውን ከእጇ መንጭቆ ወሰደና ገመዱን መቁረጥ ጀመረ ።

“የቤት ሠራተኞቹ እንዲቆርጡልሽ ለምን አላደረግሺም?”

ሜሊና አልመለሰችለትም ።

ዶሚሪስ ገመዱን ቆርጦ እንዳበቃ “ይኸውልሽ!” አለና ጩቤውን አስቀመጠው ። ሜሊናም በጥንቃቄ ስለቱን በመያዝ አንስታ ወሰደችው ።

ወደ እርሱ ተመለከተችና “ኮስታ በዚህ ዓይነት መቀጠል አንች
ልም ። አሁንም ቢሆን እወድሃለሁ ። ስለእኔ ስሜት ሊኖርህ ይገባል ።
አብረን ያሳለፍናቸውን አስደሳች ጊዜያት ታስታውሳለህ? ትዝ ይልሃል?
በሜትላ ጊዜያችን ሌሊት ...”

“ስለክርስቶስ ብለሽ” አለና ዴሚሪስ አመናጨቃት ። “አይገባ
ሽም? አከተመ ። በቃሺኝ የኔና ያንቺ ነገር እዚህ ላይ አቆመ ። ውጪልኝ፤
አስጠልተሽኛል ።”

ሜሊና እዚያው ቆማ አተኩራ አየችው ። በመጨረሻም በእርጋታ
“መልካም እንዳልከው ይሁንልህ ።” ወደኋላዋ ዞራ ጩቤውን እንደያዘች
ከክፍሉ ወጥታ ሄደች ።

“ፓኮውን ረስተሻል” አለና ዴሚሪስ ጮክ ብሎ ተናገረ ።

እርሷ ሄዳለች ።

ሜሊና ወደባልዋ የልብስ መቀየሪያ ክፍል ገብታ የቁም ሳጥኑን
ከፈተችው ። በውስጡ በመቶ የሚቆጠሩ ሙሉ ልብሶች ተሰቅለዋል ።
ለጃኬቶችም መስቀያ ልዩ ሥፍራ ተሰጥቷል ። ከአንደኛው ጃኬት ላይ
አንድ ቁልፍ በጠሰችና ኪሷ ውስጥ ጨመረችው ።

ቀጥላ መሳቢያውን ከፍታ የባሏ ስም የተለጠፈበትን የዋና ልብስ
አወጣች ። ‘ቤታ ዝግጁ ነኝ’ አለች በአሳቧ ።

የካቴላኖስ የምርመራ ድርጅት የሚገኘው ከስፎክሊስ ጐዳና ጥግ
በአረጀ የሸክላ ቤት ውስጥ ነው ። ሜሊና ፣ መለጥ ብሎ ትንሽ ዲም
ወዳለው የድርጅቱ ባለቤት ወደ ሚስተር ካቴላኖስ ቢሮ እንድትገባ
ተስተናገደች ።

“እንደምን አደርሽ ሚስስ ዴሚሪስ ፣ ምን ልርዳሽ?”

“ጥበቃ እንዲደረግልኝ እፈልጋለሁ ።”

“ምን ዓይነት ጥበቃ?”

“ከባሌ ።”

ካቴላኖስ ግንባሩን ቋጠረ ። አንድ ችግር እንዳለም ተገነዘበ ።
እንዲህ ዓይነቱን ነገር አልጠበቀም ። እንደኮንስታንቲን ዴሚሪስ ያለውን



ሰው ማስቀየም ጅልነት ነው ።

“ፖሊስ ዘንድ ለመሄድ አላሰብሽም ነበር?”

“በፍፁም ነገሩ ይፋ እንዲወጣ አልፈልግም ። በምስጢር እንዲያዝ
ልኝ እፈልጋለሁ ። ልፈታው እንደምፈልግ ስለገለፅኩለት በዚህ አሳቤ
የምገፋበት ከሆነ እገልሃለሁ ብሎኛል ። ወደአንተ የመጣሁትም በዚህ
ምክንያት ነው ።”

“ገባኝ ። ታዲያ አሁን እኔ ምን እንዳደርግልሽ ነው የምትፈል
ጊው?”

“ጥበቃ የሚያደርጉልኝን ሰዎች እንድትመድብልኝ ነው ።”

ካቴላኖስ ቁጭ ብሎ አጠናት ። በሃሳቡ ‘በጣም ቆንጆ ሴት ናት ።
ንክ ስለመሆኗ ደግሞ አልጠራጠርም’ አለ ። ባለቤቷ ይጐዳታል ብሎ
ለማመን በጣም ያስቸግራል ። በቤት ውስጥ የተነሳ አነስተኛ ግጭት
ይሆናል ይህን ሁሉ ያሳሰባት ። ቢሆንም ከእርሷ ደህና ክፍያ ሊያገኝ
ይችላል ። የሚያገኘው ገንዘብ ሊደርስበት ከሚችል አደጋ ጋር ሲመጣ
ጠን ገንዘቡ የሚያጓጓ በመሆኑ ካቴላኖስ የተጠየቀውን ለማድረግ ወሰነ ።

“ጥሩ ነው” አለ ። “ጐበዝ ሰው ስላለኝ ለጥበቃሽ ልመድበው
እችላለሁ ። መቼ እንዲጀመር ነው የምትፈልጊው?”

“ሰኞ ዕለት ።”

እውነቱን ነበር ፤ ምንም የሚያስቸኩል ነገር የለም ።

ሜሊና ዴሚሪስ ተነሳች ። “ስልክ እደውልላሃለሁ ። አድራሻህ
ያለበት ካርድ አለህ?”

“አዎ ፣ አለኝ ።” ካቴላኖስ ስሙና አድራሻው የሠፈረበትን ካርድ
ሰጣትና እስከውጭ ድረስ ሸኛት ። ‘የሷ እኔ ዘንድ መምጣት ለኔ ጥሩ ነው’
አለ በአሳቡ ። ‘ስሟ ሌሎች ደንበኞቼም የበለጠ እንዲያምኑብኝ ሊያደርግ
ይችላል ።’

ሜሊና ወደቤቷ ስትመለስ ለወንድሟ ስልክ ደወለችለት ። “ስፒ
ሮስ ጥሩ ወሬ አለኝ ።” ድምጿ በደስታ የተሞላ ይመስላል ። “ኮስታ እርቅ
ይፈልጋል ።”

“ምን? እሱን አላምነውም ሜሊና ። አንድ ያሰበው ተንኮል
ይኖራል። እርሱ ...”

“አይደለም ፣ የምሩን ነው ። ሁለታችሁ በየጊዜው መፋተጋችሁ ምኝነት መሆኑን ተረድቷል ። በቤተሰቡ ውስጥ ሰላም እንዲሰፍን ይፈልጋል ።”

ፀጥታ ሰፈነ ። “እኔ እንጃ ብቻ ።”

“ትንሽ ዕድል ብትሰጠው ። ዛሬ ከሰዓት በኋላ በዘጠኝ ሰዓት በአክሮ ኮሪንዝ በሚገኘው የመዝናኛ ክበብህ ሊያገኝህ ይፈልጋል ።”

“ያ ሥፍራኮ በመኪና አራት ሰዓት ያስኬዳል ። እዚሁ ከተማ ውስጥ ለምን አንገናኝም?”

“እንግዲህ እርሱ እንዲህ አላለኝም ” ብላ ሜሊና “ግን እውነት ለሰላም ከሆነ ...”

“እሺ አደርጋለሁ ። ግን ይህንን የምፈጽመው ለአንቺ ስል ነው ።”

“ለእኛ ብለህ ነው” አለችው ሜሊና ። “ደህና ሁን ስፒሮስ ።”

“ደህና ሁኚ ።”

ሜሊና ኮንስታንቲን ቢሮ ስልክ ደወለች ። ድምፁ የቁጣ ነበር ። “ምንድን ነው? እኔ ሥራ በዝቶብኛል ።”

“ስፒሮስ አሁን ስልክ ደውሎልኝ ነው ። ከአንተ ጋር እርቅ ለማውረድ ይፈልጋል ።”

አጭር የለበጣ ሳቅ ሳቀ ። “ቢያደርግ ይሻለዋል ። ያለምኩት ሁሉ ከግቡ ሲደርስ ብቻ ነው ሰላሙን ሊያገኝ የሚችለው ።”

“ከእንግዲህ ከአንተ ጋር ለመፎካከር እንደማይፈልግ ገልጾልኛል ኮስታ ። መርከቦቹን ሁሉ ሊሸጥልህ አስቧል ።”

“ለእኔ ሊሸጥልኝ ... እርግጠኛ ነሽ?” በነገሩ እየተመሰጠ መምጣቱ ከድምፁ ይታወቃል ።

“አዎ ። እንደበቃው ተናግሯል ።”

“እሺ ። ሒሣቡን ተምኖ እንዲልክልኝ ንገሪው ። እና ...”

“አይደለም ። ዛሬ ከሰዓት በኋላ በዘጠኝ ሰዓት አክሮ – ኮሪንዝ ውስጥ ከአንተ ጋር ሊገናኝ ይፈልጋል ።”

“በመዝናኛ ክበቡ?”

“አዎ ። ሥፍራው ገለል ያለ ስለሆነ ሁለታችሁ ብቻችሁን ለመሆን አመቺ ነው ። ይህ ምስጢር ለማንም እንዲነገርበት አይፈልግም ።”

‘እንደሱ ይሻለዋል’ አለ ዴሚሪስ ኩራት እየተሰማው በአሳቡ ።



‘ምስጢሩ ቢሰማበት መሳቂያ መሳለቂያ ይሆናል ።’ “እሺ” አለ ዴሚሪስ። “በተባለው ሥፍራ እንደምገኝ ንገሪው ።”

ወደ አክሮ – ኮሪንዝ በመኪና የሚደረገው ጉዞ ረዘም ያለ ጠመዝማዛ ሲሆን በውቡ የገጠር ጐዳና ላይ የሚሸተው የግሬፕሱና የሎሚው መዓዛ ያውዳል ። ስፒሮስ ላምብሩ ከጥንታዊ ፍርስራሽ አጠገብ ሲያልፍ ከሩቁ የአምላክ ኢሊውሲስን መስዋዕት ማቅረቢያ ሥፍራ አየና ዴሚሪስ ትዝ አለው ።

ከመዝናኛ ክበቡ ቀድሞ የደረሰው ላምብሩ ነው ። ከአንድ ጐጆ ቤት ፊት ለፊት መኪናውን አቆመና ተቀምጦ ከዴሚሪስ ጋር ስለሚነጋገርበት ጉዳይ ማሰላሰል ጀመረ ። ኮንስታንቲን እውነት እርቅ እንዲወርድ ፈልጐ ይሆን ወይንስ ይህ ሌላው የማታለያ ዘዴው ነው? ድንገት አንድ አደጋ ቢደርስበት ሜሊና የት እንዳለ ታውቅለታለች ። ስፒሮስ ከመኪናው ውስጥ ወረደና ጭር ወዳለው ክበብ ገባ ። ክበቡ ከእንጨት የተሠራ ማራኪ ጥንታዊ ሕንፃ ነው ። ከፍታ ቦታ ላይ በመሠራቱ እዚያ ሆኖ ጥንታዊዋ የኮሪንዝ ከተማ በደንብ ትታያለች ። ስፒሮስ ልጅ በነበረበት ወቅት ከአባቱ ጋር ቅዳሜና እሁድ ወደዚህ ሥፍራ እየመጣ በአካባቢው ባለው ተራራ አውሬ ያድን ነበር ። አሁን ግን የሚያሳድደውና የሚያድ ነው ሌላ ነገር ነው ።

ከአሥራ አምስት ደቂቃ በኋላም ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ደረሰ ። ስፒሮስ ቀድሞት እየጠበቀው መሆኑን ሲመለከት የበለጠ ኩራት ተሰማው ። ‘አሃ ፣ ከዚህ ሁሉ ዓመት በኋላ ሰውዬው ሽንፈቱን አምኖ ሊቀበል ነው ።’ ከመኪናው ውስጥ ወረደና ወደጐጆዋ አመራ ። ሁለቱም ሰዎች ቆመው ትኩር ብለው ይተያዩ ነበር ።

“መልካም ፣ ውድ ዋርሳዬ ሆይ” አለ ዴሚሪስ ። “በመጨረሻ ከጐዳናው ፍጻሜ ላይ ደረስን አይደል?”

"ከእንግዲህ እብደታችን እዚህ ላይ እንዲያከትም እፈልጋለሁ ኮስታ ። ከሚገባው በላይ ተጉዘናል ።"

"በሀሣብህ እጅጉኑ እስማማለሁ ። ለመሆኑ ስፒሮስ ስንት መርከብ አለህ?" ላምብሩ በአድናቆት ወደእርሱ ተመለከተ ። "ምን?"

"ስንት መርከቦች ነው ያለህ? ሁሉንም እገዛቸዋለሁ ። በእርግጥ ጥሩ ቅናሽ ታደርግልኛለህ ።"

ላምብሩ "መርከቦቼን ልትገዛ?"

"ሁሉንም ልገዛቸው ፈቃደኛ ነኝ ። ይህም በዓለም ውስጥ የመርከብ ባለቤቶች ቁንጮ እንድሆን ያስችለኛል ።

"እብደሃል መሰለኝ፣ ምን ይሆን መርከቦቼን የምሸጥ መሆኔን እንድታስብ ያደረገህ?"

ምላሹን መስጠት አሁን የዴሚሪስ ተራ ነበረ ። "እዚህም የተገናኘነው ለዚሁ መሰለኝ ፤ አይደለም እንዴ?"

"እዚህ የተገናኘነው አንተ እርቅ በመጠየቅህ ነው ።"

የዴሚሪስ ፊት ጠቆረ ። "እኔ – ማን ነው እንደርሱ ያለህ?"

"ሜሊና"

ለሁለቱም እውነቱ በአንዴ ታያቸው ። "እኔ እርቅ እንደምፈልግ ነገረችህ?"

"እኔ መርከቦቼን ለመሸጥ እንደምፈልግ ነገረችህ?"

"ይህች ደደብ ውሻ" አለ ዴሚሪስ ። "ሁለታችንን በማገናኘቷ ከአንድ ስምምነት ላይ የምንደርስ መስሏት ነው ላምብሩ ፣ እርሷ ደግሞ ከአንተ የባሰች ጅል ናት ። የከሰዓት በኋላ ጊዜዬን በሙሉ ከአንተ ጋር በከንቱ አባከንኩ ።"

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ወደኋላው ዞረና በኃይል በሩን ከፍቶ ወጣ ። ስፒሮስ ላምብሩ በአሳብ ተመስጦ ዝም ብሎ ያየው ነበር ። 'ሜሊና ልትዋሸን አይገባትም ነበር ። በእኔና ባለቤቷ መካከል እርቅ ሊወርድ የሚችልበት ምንም መንገድ እንደሌለ ማወቅ ነበረባት ። አሁን አይደለም፤ ጊዜው አልፏል ፤ ሁልጊዜም እንዲሁ ነው ።'

ያን ዕለት ከሰዓት በኋላ በስምንት ሰዓት ላይ ሜሊና በደወል ጥሪ ሠራተኛዋን ጠራቻት ። "አንድሪአ ፣ ሻይ ልታመጪልኝ ትችያለሽ?"



"እሺ እመቤቴ ።" ሠራተኛዋ ወጣችና ከአሥር ደቂቃ በኋላ ሻይዋን በማቅረቢያ ላይ አስቀምጣ ይዛ ስትገባ እመቤቷ በስልክ ትነጋገር ነበር ። አነጋገሯ በንዴት የተሞላ ይመስላል ።

"አይሆንም ኮስታ ከውሳኔ ላይ ደርሻለሁ ። አንተን ልፈታህ ወስኛለሁ ። ይህንኑ ነገር የበለጠ ውስብስብና በአደባባይም የታወቀ እንዲሆን አደርገዋለሁ ።"

በሰማችው የቲደናገጠችው ሠራተኛ ማቅረቢያውን አስቀመጠችና ዞራ ለመውጣት እርምጃ ጀመረች ። ሜሊና በእጅ ምልክት እንድትቆይ ነገረቻት ።

ሜሊናን ከሌላኛው የስልክ ጫፍ የሚያነጋግራት ሰው አልነበረም ። ብቻ በስልክ መነጋገሩን ቀጠለች ። "እንደፈለግከው ልታስፈራራኝ ትችላለህ ። አሳቤን ግን አልቀይርም ... በፍጹም ... የፈለግከውን ብትናገር ግድ የለኝም ... ኮስታ አታስፈራራኝ ... አይሆንም ... ጉዳዩ ምንድን ነው? ... እሺ ወደባሕር ዳርቻው ቤት መጥቼ ላገኝህ እችላለሁ ፤ ግን ይህ ምንም ለውጥ ሊያመጣ አይችልም ። እሺ ፣ ብቻዬን እመጣለሁ ። በአንድ ሰዓት ውስጥ? ጥሩ ነው ።"

ሜሊና ቀስ ብላ ስልኩን ዘጋች ። ፊቷ ላይ ጭንቀት ይነበባል ። ወደ አንድሪያ ዞር አለችና "ከባለቤቴ ጋር ለመገናኘት ወደባሕር ዳርቻው ቤት መሄዴ ነው ። በአሥራ ሁለት ሰዓት ያልተመለስኩ እንደሆነ ለፖሊስ ስልክ እንድትደውዪ እፈልጋለሁ ።"

አንድሪያ በድንጋጤ ምራቋን ዋጠች ። "ሾፌሩ ቢያደርስሽስ?"

"የለም ፣ ሚስተር ዴሚሪስ ብቻሽን ነይ ነው ያለኝ ።"

"እሺ እመቤቴ ።"

አንድ የሚሠራ ተጨማሪ ነገር ነበረ ። የካተሪን አሌክሳንደር ሕይወት አደጋ ላይ ነው ። ለእርሷ ማስጠንቀቂያ ሊደርሳት ይገባል ። ወደቤታቸው መጥተው እራት ከበሉት ልዑካን መካከል አንዱ ሊሆን ይችላል። 'ሁለተኛ ልታገኚያት አትችዪም ። የሚያጠፉት ሰው ልኬአለሁ ።' ተብሎ የተነገራት ትዝ አላት ። ሜሊና ለንደን ወደሚገኘው የባለቤቷ መሥሪያ ቤት ስልክ ደወለች ።

"ካተሪን አሌክሳንደር የምትባል አለች?"

"አሁን ለጊዜው ቢሮ ውስጥ የለችም ። ሌላ ሰው ላቅርብልዎ?"

ሜሊና አመነታች ። ለማስተላለፍ የፈለገችው መልእክት በጣም

አስቸኳይ ቢሆንም ለሌላ ሰው ለመንገር ደግሞ ማንንም አላመነችም ። መልሳ ለመደወል ደግሞ ጊዜ የላትም ። ኮስታ በቢሮው ውስጥ ስለሚገኘው ዊም ቫንዲን ስለተሰኘው ጉበዝ ሠራተኛ ሲያወራ ሰምታለች ።

"እባክዎ ሚስተር ቫንዲንን ለማነጋገር እችላለሁ?"

"አንድ ጊዜ ይጠብቁ"

የአንድ ሰው ድምፅ ከስልኩ ውስጥ ተሰማ ። "ሄሎ"

ማንነቱ በእንዴ ገብቷታል ።

"ለካተሪን አሌክሳንደር መልእክት ነበረኝ ። በጣም ከፍተኛ ጉዳይ ነው ። እባክህ መልእክቱን ልታስተላልፍልኝ ትችላለህ?"

"ካተሪን አሌክሳንደር?"

"አዎ ። ንገራት ። ሕይወቷ በአደጋ ላይ መሆኑን ንገራት ። ሰው ሊገድላት ነው ። ከአቴንስ ወደዚያ ከመጡት ሰዎች መካከል አንዱ ይመስለኛል ።"

"አቴንስ ..."

"አዎ"

"የአቴንስ ሕዝብ ብዛት ስምንት መቶ ስድስት ሺህ ..."

ሚሊና ሰውዬው እንዲገባው ልታደርግ አልቻለችም ። ስልኩን መልሳ ዘጋችው ። የአቅሟን ሁሉ ሞክራለች ።

ዊም ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ስላደረገው የስልክ ውይይት ማሰላሰል ቀጠለ ። 'አንድ ሰው ካተሪንን ሊገድላት ይፈልጋል ። በዚህ ዓመት ውስጥ በእንግሊዝ ውስጥ አንድ መቶ አሥራ አራት ግድያዎች ተፈጽመዋል ። ካተሪን የዚህን ቁጥር ወደ አንድ መቶ አሥራ አምስት ከፍ ታደርገዋለች ። ከአቴንስ ከመጡት ሰዎች መካከል አንደኛው ጂሪ ሃሌይ ፣ ዩቪ ሬናድ ፣ ዲኖ ማቲሲ ፣ ከእነኚህ አንደኛው ካተሪንን ሊገድል ነው ።' የዊም ኮምፒዩተራዊ ጭንቅላት ስለሦስቱም ሰዎች ያለውን መረጃ አስታውሶ አሳውቆታል ። 'የትኛው እንደሆነ አውቄዋለሁ ።'

ካተሪን ተመልሳ ስትመጣ ዊም ስለስልክ ጥሪው ምንም አልነገራትም ።

ግምቱ ትክክል መሆን ያለመሆኑን ለማረጋገጥ ወንጀሉ ተፈጽሞ



ለማየት ጓጉቷል ። ካተሪን ከልዑካኑ አባላት ጋር ማታ ማታ በየተራ ትወጣለች ። በነጋታው ሥራ ስትገባ ምን እንደደረሰባት ለማየት ዊም ቀድሞ ይጠብቃታል ። ምንም አለመሆኗ ተስፋ አስቆርጦታል ።

'መቼ ይሆን የታሰበውን የሚፈጽሙባት' አለ በአሳቡ እየተገረመ ። የስልኩን መልዕክት ለእርሷ መንገር ነበረበት ። ያ ደግሞ ማታለል ነው ። የአጋጣሚን ልዩ ልዩ ድንገታዊ ክስተቶች እንዳይፈፀሙ ማገድ ተገቢ አይደለም ።

# ምዕራፍ ሃያ አምስት

ወደ ባሕር ዳርቻ ቤቱ በመኪና ያደረገው የአንድ ሰዓት ጉዞ ያለፉትን ሃያ ዓመታት ትዝታዎች በሙሉ ከፊቱ ድቅን አድርጐበታል ። ሜሊናም የምታስታውሳቸው ብዙ ነገሮች ነበሩ ፤ ብዙ ብዙ ትዝ የሚሉ ጊዜዎች ። መልከ መልካሙ ወጣት ኮስታ እንዴ 'ውበት ምን እንደሆነ ለኛ ለአላፊና ጠፊ ፍጡሮች ለማስተማር ከመንግሥተ ሰማያት የተላክሽ ነሽ ። ይህ ድለላ አይደለም ። ስላንቺ የምናገረው ማንኛውም ነገር አንቺን በትክክል ሊገልጽሽ እንደማይችል…' ያላት ፤ በግል የመንሸርሸሪያ መርከባቸው ያደርጉት የነበረው ሽርሽር ፤ በፕሳራ ያሳለፏቸው ጊዜያት … አስደሳች ስጦታዎች ይቀርቡባቸው የነበሩበት ቀናት ፤ በአልጋ ላይ ተቃቅፈው በፍቅር የተቃጠለ ወሲብ የፈጸሙባቸው ሌሊቶች ። ከዚያም ያስወረዳትና እንደአሸን የፈሉት የኮስታ ዕቁባቶች ፤ በተለይም ከኖኤል ፓጂ ጋር የነበረው ወዳጅነት ፤ የደበደባትና ያደረሰባት ውርደት። "ኮሪትሲሞን! እንጃ የምትኖሪበት ምክንያት የለም ። ለምን ሕይወትሽን አታጠፊም?" ያላት ። በመጨረሻም ስፒሮስን ለመግደል የተሰነዘረው ዛቻ ።

በተለይ ፍጻሜው ላይ ይህንን ነበር ሜሊና ልትቋቋመው ያልቻለችው።

ሜሊና ከባሕር ዳርቻው ቤት ስትደርስ ጭር ብሏል ። ሰማዩ ደመናን አዝሏል ። በጣም ቀዝቃዛ የሆነ ነፋስም ከወደ ባሕሩ ይነፍሳል ። 'መጥፎ ገድ' አለች በአሳቧ ።

ምቹ ወደሆነው አዝናኝ ቤት ገባ አለችና ለመጨረሻ ጊዜ ዙሪያውን ቃኘች ። ከዚያም ወንበሮቹን በሙሉ ገለባበጠች ፤ አምፖሎቹን ሰባበረች። የለበሰችውን ልብስ ቀዳድዳ ከወለሉ ላይ ጣለች ። ከመርማሪ ድርጅቱ የተሰጣትን አድራሻ ያለበትን ካርድ አውጥታ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠች ። ምንጣፉን ገለጠችና የወርቅ አዝራሩን ከሥር አኖረች ። ኮስታ ሰጥቷት የነበረውን የወርቅ ሰዓት ከእጇ ላይ አውጥታ ከሰከሰችው ።



ከመኖሪያ ቤቷ ያመጣችውን የባለቤቷን የዋና ልብስ ይዛው ወደባሕሩ ዳርቻ ተጓዘች ። ውሀ ውስጥ ነክራ መልሳ ወደቤቱ አመጣች ። በመጨረሻም ለማከናወን የቀራት አንድ ነገር ነበር ። 'ጊዜው አሁን ነው' አለች በአሳቧ ። በኃይል ወደ ውስጥ ተነፈሰችና እጇታው በሽንት ቤት ወረቀት የተጠቀለለውን ጩቤ አውጥታ በትኩረት አየችው። ወሳኙ ይህኛው ነው ። ሰው የገደላት ለማስመሰል እራሷን በኃይል መውጋት ይኖርባታል ። ከዚህም በተጨማሪ ቀሪውን እቅዷን ከግቡ ለማድረስም ቀሪ ጉልበት ሊኖራት ይገባል ።

ዓይኗን ጨፈነችና ጩቤውን ሰውነቷ ውስጥ በኃይል ሰካች ። ሕመሙ እየተሰማት መጣ ። ደም እንደጐርፍ ፈሰሰ ። ሜሊና የሚደማውን ሰውነቷን እርጥብ በሆነ የዋና ሙታንታ ያዘችና ሙታንታው በደሙ ሲጨማለቅ ከቁምሳጥኑ በስተጀርባ ደበቀችው ። አሁን ያዞራት ጀመር ። ካሰበችው ነገር የተረሳ አለመኖሩን ለማረጋገጥ ዙሪያውን በዓይኗ ቃኘችና እየተንገዳገደች ወደመውጫ በሩ አመራች ። ደሟን በምንጣፉ ላይ እያንጠባጠበች መጣች ።

ወደውቅያኖሱ ተጓዘች ። ደሟ በጣም ይፈሳል ። በአሳብዋ 'ካቀድኩት ግብ የምደርስ አይመስለኝም ። ኮስታ ሳያሸንፈኝ አይቀርም ። ግን መሆን የለበትም' አለች ።

ወደውቅያኖስ ያደረገችው ጉዞ በቀላሉ የሚዘለቅ አልነበረም ። 'አንድ ሌላ ርምጃ' አለች በአሳቧ ። 'አንድ ተጨማሪ ርምጃ ።' ምድር ሰማዩ እየዞረባት ጉልበት ብታጣም እንደምንም ርምጃዋን ቀጠለች ። ዓይኗም ብዥ ስላለባት ወድቃ ተምበረከከች ። 'እዚህ ላይ መቆም የለብኝም ።' ተነስታ ጉዞ ቀጠለችና የውሀው ቅዝቃዜ እግሯን ተሰማት ።

ጨውማ ውሃ ቁስሏን ሲነካው ልትቋቋም የማትችለው ከፍተኛ ሕመም ተሰማትና በኃይል ጮኸች ። 'ይህንን የማደርገው ለስፒሮስ ብዬ ነው' አለች በአሳቧ ። 'ውድ ስፒሮስ ።'

በርቀት ደመናው እየከበደ ወደ አድማስ ሲጓዝ ይታያል ። ደሟን እያዘራች ወደሱው መዋኘት ጀመረች ። ተአምር ታየ ። ደመናው ወርዶ ወደእርሷ መጣ ። ለስላሳው ደመና ሰውነቷን ሲነካ ፤ ገላዋን ሲያጥበውና ሲያንሳፍፋት ተሰማት ። አሁን ሕመሙ ጠፍቷል ። በጣም አስደሳች የሆነ ሰላማዊ ስሜት በውስጧ ሰፍኗል ።

'ወደ ቤቴ መሄዴ ነው' ስትል ሜሊና በደስታ አሰበች ። 'በመጨረሻ ወደመኖሪያ ቤቴ መሄዴ ነው ።'

# ምዕራፍ ሃያ ስድስት

“ሚስትህን በመግደልህ በቁጥጥር ሥር አውዬሃለሁ ።”

ከዚያ በኋላ ሁሉም ነገር በዝግታ እንቅስቃሴ የሚከናወን ይመስ ላል። የጣት አሻራው እንዲወሰድ ተደረገ ። ፎቶግራፍ ተነሳና ወደወህኒ ተላከ ። እንዲህ ዓይነት ነገር ይፈጸምበታል ብሎ ለማመን በጣም ያስቸግራል ።

“ፒተር ዲሞኒደስን አሁኑኑ ፈልግልኝ ። አሁኑኑ ላነጋግረው እንደምፈልግ ንገርልኝ ።”

“ሚስተር ዲሞኒደስ ከሥራው ታግዷል እየተመረመረ ነው ።”

“ስለዚህ የማነጋግረው ማንም ሰው የለም ማለት ነው ?” ‘ከዚህ ሥፍራ እወጣለሁ’ አለ በአሳቡ ። ‘እኔኮ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነኝ ።’

ልዩ ሕግ አስከባሪው እንዲመጣለት ጥያቄ አቀረበ ።

ዴልማ ከአንድ ሰዓት በኋላ ወደ እሥር ቤቱ መጣ ። “ልታነጋግረኝ ጥያቄ አቅርበህ ነበር?”

“አዎ” አለ ዴሚሪስ ። “እንደገባኝ ባለቤትህ ተገደለች ብላችሁ የመዘገባችሁት ጊዜ ዘጠኝ ሰዓት ነው ።”

“ትክክል ነው ።”

“ኋላ እራስህም ሆነ ፖሊሶች እንዳታፍሩ ፣ በተባለው ሰዓት ከባሕር ዳርቻ ቤቴ አካባቢ አለመኖሬን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አለኝ ።”

“ማረጋገጫውን ለማቅረብ ትችላለህ?”

“እንዴታ ምስክር አለኝ ።”

ከፖሊስ ኮሚሽነሩ ቢሮ ተቀምጠው እንዳለ ስፒሮስ ላምብሩ ደረሰ ። ዴሚሪስ ገና እንዳየው ፊቱ ፈካ ።

“ስፒሮስ ፣ እግዚአብሔር ነው ደህና ጊዜ አንተን ወዲህ ያመጣልኝ። እነኚህ ደደቦች ሜሊናን የገደልኩ መስሏቸዋል ። እንዳልገደልኳት ስለምታውቅ እባክህ ንገራቸው ።”

ስፒሮስ ላምብሩ ግንባሩን ቋጠረ ። “ምን ልንገራቸው?”



“ሜሊና የተገደለችው ትናንት ከሰዓት በኋላ በዘጠኝ ሰዓት ነው ። በዘጠኝ ሰዓት ደግሞ እኔና አንተ በአክሮ ኮሪንዝ የመዝናኛ ክበብህ አብረን ነበርን ። ከምሽቱ አንድ ሰዓት በፊት ከባሕር ዳርቻ ለመድረስ እንደማልችል ደግሞ ታውቃለህ ። አብረን እንደነበርን ግለጽላቸው ።”

ስፒሮስ ላምብሩ ትኩር ብሎ ተመለከተው ። “አብረን እንደነበ ርን?”

የዴሚሪስ ፊት ፍም መሰለ ። “እ … እኔና አንተ ትናንት አክሮ ኮሪንዝ በሚገኘው የመዝናኛ ክበብ ውስጥ አብረን እንደነበርን?”

“ዞሮብሃል መሰለኝ፣ ኮስታ ፣ ትናንት ከሰዓት በኋላ ብቻዬን በመኪና ከከተማ ወጥቼ ነበረ ። ውሸት ልናገርልህ አልችልም ።”

የኮንስታንቲን ዴሚሪስ ፊት በንዴት ተወጣጠረ ። “እንዴት እንዲህ ትላለህ?” አለና የላምብሩን የኮት ኮሌታ ጐተተ ። “እውነቱን ንገራቸው!”

ስፒሮስ ላምብሩ እጁን አስለቀቀው ። “እውነቱ እህቴ መሞቷና የገደልካትም አንተ መሆንህ ነው ።”

“ውሸታም!” ሲል ዴሚሪስ ጮኸ ። “ውሸታም!” ዘሎ ላምብሩን ለማነቅ ሲንደረደር ሁለት ፖሊሶች ጣልቃ ገቡ ።

“አንተ የውሻ ልጅ ። ንፁህ ሰው መሆኔን ታውቃለህ ።”

“ንፁህነትህን የሚያረጋግጥልህ እኔ ሳልሆን ዳኛው ነው ። ጥሩ ጠበቃ የሚያስፈልግህ ይመስለኛል ።”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከዚህ ሁሉ ጉድ ሊያተርፈው የሚችል አንድ ሰው ብቻ እንደነበር ተገነዘበ ።

ናፖሊዮን ቾታስ ።

# ምዕራፍ ሃያ ሰባት

## ምስጢራዊ ማኅደር

### ከካተሪን ዶግላስ ጋር የተካሄደው ውይይት ዶሴ

ካ = አንድ ሰው ክፉ እንደሚያደርስበት ሰውነቱ እንደሚነግረው ታምናለህ አላን?

አ = በሳይንሳዊ አመለካከት ተቀባይነት የለውም ። እውነት ለመናገር ግን እኔም አምንበታለሁ ። ክፉ ይደርስብኛል ብለሽ ሰግተሽ ታውቂያለሽ?

ካ = አዎ ። አንድ አደጋ ያጋጥመኛል የሚል ፍርሃት አድሮብኛል ።

አ = ድሮ በሕልምሽ ያየሽው ዓይነት

ካ = አይደለም ። እንደነገርኩህ ሚስተር ዴሚሪስ ከአቴንስ ሰዎችን ወዲህ ልኳል ።

አ = አዎ ።

ካ = ሰዎቹን እንድንከባከባቸው ባዘዘኝ መሠረት ከጥቂቶቹ ጋር ቅርበት ነበረኝ ።

አ = ያስፈራራሽ አለ?

ካ = የለም ። እንደዚያ አይደለም ። ለማስረዳት ያስቸግራል ። ምንም ያደረገኝ የለም ። ግን አንድ አሰቃቂ ድርጊት ሊፈጸም ይችላል የሚል ግምት አለኝ ። ይህ አባባሌ ትርጉም ይሰጥሃል?

አ = ስለ ሰዎቹ ንገሪኝ ።

ካ = ፈረንሣዊው ዪቬ ሬናድ ይባላል ። ወደ ሙዚዬም እንሂድ ብሎ ፈትሮ ይይዘኛል ። እተባለው ሥፍራ ስንደርስ ደግሞ ሙዚዬሞቹን ለመጎብኘት ምንም ደንታ የሌለው ሆኖ አገኘዋለሁ ። ለምሳሌ ባለፈው ቅዳሜ ወደስቴን ሄንግ አብሬው እንድሄድ ጠይቆኝ ነበር። ከልዑካኑ አባላት ሌላው ጄሪ ሃሌይ የሚባለው አሜሪካዊ ነው ። ሰውዬው ደስ የሚል ቢሆንም ግራ የሚያጋቡ ነገሮች አይበታለሁ።



ሦስተኛውም ሰው ዲኖ ማቱሲ ይባላል ። በሚስተር ዴሚሪስ ኩባንያ ውስጥ ከፍተኛ የኃላፊነት ሥፍራ ያለው ቢሆንም እራሱ የሚያውቀውን እንዳብራራለት ይጠይቀኛል ። አብሬው በመኪና ከከተማ ውጭ እንድሄድ ጋብዞኝ ነበር ። እኔም ዊም አብሮን እንዲመጣ አስቤ ··· እና ያ ለሌላ ምክንያት ሊሆን ይችላል ።

አ = እንዴት?

ካ = ዊም የተለየ ፀባይ ማሳየት ጀመረ ።

አ = እንዴት ዓይነት?

ካ = ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት ወደቢሮ ስመጣ ቀድሞ ይጠብቀኛል ። ከዚህ ቀደም እንደዚያ አድርጐ አያውቅም ። እና በሚያየኝም ወቅት በቢሮው ውስጥ መገኘቴ እንደሚያናድደው ከፊቱ ላይ አነባለሁ ። ይህ ሁሉ ግራ አጋብቶኛል ። አንተስ ምን ይመስልሃል?

አ = አንዴ መክፈቻ ቁልፉን ከጨበጥሽ ምስጢሩ ይገለፅልሻል ። ሌላ ተጨማሪ ሕልሞች አይተሽ ታውቂያለሽ?

ካ = ስለኮንስታንቲን ዴሚሪስ አልሜ ነበር ፣ ግን ፍቺው ግልጽ አልሆነልኝም ።

አ = ካየሽው ውስጥ የምታስታውሺውን ንገሪኝ ።

ካ = ለምን ይህን ያህል ደግ እንደሆነልኝ ፡ ስለምንስ በለንደን ሥራና መኖሪያ እንደለገሰኝ ፡ የወርቅ የደረት ጌጡን ለምን እንደሸለመኝ እንዲያስረዳኝ ጠይቄው ነበር ።

አ = ታዲያ እርሱስ ምን አለሽ?

ካ = አላስታውሰውም ፡ የማስታውሰው ከእንቅልፌ እየጮህኩ መነሳቴን ነው ።

ዶክተር አላን ሃሚልተን ማኅደሩን በጥንቃቄ ማጥናት ቀጠለ ። በውስጠ ኅሊናዋ ተደብቆ የቀረና ካተሪንን የሚረብሻት ነገር ካለ ለይቶ ለማወቅ ጥረት አደረገ ። ስጋቷ የመነጨው እንግዶች ከአቴንስ በመምጣታቸውና ያለፈው አሰቃቂ ሕይወቷ ከአቴንስ ጋር የተቆራኘ በመሆኑ እንደሆነ እርግጠኛ ነበር ። የዊምም ሁኔታ አላንን አስገርሞታል ። ሊሆን ይችላል ብላ ካተሪን በመገመቷ ነው? ወይንስ ዊም እንግዳ ባሕሪይ

ማሳየት ጀምሯል? 'ዊምን በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ማግኘት አለብኝ' አለ አላን በአሳቡ ። 'ምናልባት ቀጠሮውንም ወደዚህ ማቅረብ እችል ይሆናል ።'

አላን ወንበሩ ላይ እንደተቀመጠ ስለካተሪን ማሰብ ቀጠለ ። ከታካሚዎቹ ጋር ልዩ ግንኙነት አለመፍጠርን መመሪያው ቢያደርግም ካተሪን ግን የተለየች ሴት ሆናበታለች ። በጣም ቆንጆና የምታጓጓ … "ምን ማድረጌ ነው? እንዲህ ማሰብ የለብኝም ። በሌላ ነገር ላይ ባተኩር ይሻለኛል ።" ግን አእምሮው ተመልሶ ስለእርሷ ያስባል ።

ካተሪን ስለአላን ሃሚልተን ማሰቧን ከአእምሮዋ ለማስወገድ አልቻለችም ። 'ባልጃጀል ይሻላል ። ትዳር ያለው ሰው ነው ። ታካሚዎች ሁሉ ስለሀኪማቸው ተመሳሳይ ስሜት ይኖራቸው ይሆን ?' ስትል ለእራሷ የምታወራው ጥቅም የሚሰጣት አልሆነም ። 'ምናልባት ስለሐኪሜ ሌላ ሐኪም ማማከር ሳያስፈልገኝ አይቀርም ።'

ከሁለት ቀናተ በኋላ ተመልሳ አላንን ማነጋገር ነበረባት ። 'ብዙ ጣጣ ውስጥ ከመግባቴ በፊት ቀጠሮውን ብሰርዝ ይሻለኛል ። ግን ልቤ ብዙ ጉዳና ተራምዷል ።' አለች ካተሪን በአሳቧ ።

ከአላን ጋር ቀጠሮ በነበራት ቀን ጠዋት ካተሪን ሽክ ብላ ወደቁንጅና ሳሎን አመራች ። 'ከዛሬ በኋላ ዳግመኛ ስለማላየው ለአሁኑ ሽክ ብል ምንም ክፋት የለውም ።' አለች ካተሪን ለራሷ ።

ወደቢሮው ገና እንደገባች ውሳኔዋ እንደጨው ሟሟ ። 'ለምንድን ነው እንዲህ በጣም የሚስበኝ? ምነው ከማግባቱ በፊት ተገናኝተን በነበረ? አእምሮዬ ደህና ሳለ ብንተዋወቅ ምንኛ ደስ ይለኝ ነበር? ለካ አእምሮዬ ጤነኛ ቢሆን ወደ እርሱ ዘንድ አልመጣም ነበር?'

"ያልሺውን በደንብ አልሰማሁትም" አላት ።

ካተሪን ድምጿን ከፍ አድርጋ መናገሯንም የተረዳችው ይኼኔ ነበር። ይህ የመጨረሻ ጉብኝቷ መሆኑን አፍርጣ ለመንገር ጊዜው አሁን



ነው ።

በኃይል ወደ ውስጥ ተነፈሰች ። "አላን …" እንደገና ውሳኔዋ ተቀየረ ። በጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን ፎቶግራፍ ተመለከተች ።

"ካገባህስንት ጊዜ ይሆንሃል?"

"ካገባህ አልሺኝ?" አለና የካተሪንን ዓይን ተከተለ ። "ይህቺ የእህቴና ልጇ ፎቶግራፍ ነው ።"

ካተሪን ከፍተኛ ደስታ በመላ ሰውነቷ ሲሰራጭ ተሰማት ። "በጣም ጥሩ ነው ። ማለቴ እርሷ … እርሷ በጣም ደስ የምትል ናት ።"

"ካተሪን ፣ እመመሽ እንዴ?"

ኪርክ ሬኖልድስም እንዲህ ብሎ ይጠይቃት ነበር ። አሰበች ። 'ያኔማ ሲጠይቀኝ ያመኝ ነበር ፤ አሁን ግን ደህና ነኝ ።' አላን ላቀረበላት ጥያቄ "ደህና ነኝ" ስትል መለሰችና "አላገባህም ?" ብላ ጠየቀችው ።

"የለም ፣ አላገባሁም ።"

'አብረኸኝ እራት ልትበላ ትችላለህ? የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ቢኖረንስ? ታገባኛለህ? ብላ ከእነኚህ ሦስቱ ጥያቄዎች አንዱን እንኳ በይፋ ብትናገር የለየላት እብድ ነች እንደሚላት እርግጠኛ ነበረች ። 'ምናልባትም እብድ ሳልሆን አልቀርም ።'

ግንባሩን ቋጥሮ ዝም ብሎ ተመለከታት ። "ካተሪን ከእንግዲህ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውይይታችንን ለመቀጠል የምንችል አይመስለኝም ። የዛሬው የመጨረሻችን ይሆናል ።"

የካተሪን ልብ ሊቆም ደረሰ ። "ምነው ያስቀየምኩህ ነገር …?"

"አይደለም ። አስቀ…አስቀይመሽኝ አይደለም ። በዚህ ዓይነቱ የሙያ ግንኙነት ሳቢያ በተፈጠረው መተዋወቅ አስታኮ ከታካሚ ጋር ልዩ ግንኙነት መፍጠር ለአንድ ሐኪም የተከለከለ ነው ።"

ዓይኗ አፍጥጦ አትኩራ አየችው ።

"ስላንቺ ፍላጎት አድሮብኛል ነው የምትለኝ?"

"እዎ ስጋቴ …"

"ሙሉ በሙሉ ትክክል ነህ" አለች ካተሪን በደስታ ። "ስለዚሁ ጉዳይ ዛሬ ማታ በእራት ላይ በዝርዝር እንወያይ ።"

በሶሆ እምብርት ላይ በምትገኝ አንዲት አነስተኛ የኢጣሊያን ሆቴል ውስጥ እራታቸውን በሉ ። ምግቡ መጥፎ ይሁን ጣፋጭ ለሁለቱ ምኑም አልታወቃቸውም ። አንዱ ስለሌላው በተመስጦ ሲያስላስል ነበር ያመሹት ።

"አላን ፣ ልክ አይደለህም ። መቼም ስለእኔ ሁሉንም ነገር ታውቃለህ። ስለእራስህ ደግሞ ንገረኝ ። ከዚህ ቀደም አግብተህ አታውቅም ?" ስትል ካተሪን ጠየቀችው ።

"አላገባሁም ግን አጭቼ ነበር።"

"ታዲያ ምን ሆነ ?"

"በጦርነቱ ወቅት አንዲት አነስተኛ አፓርታማ ውስጥ አብረን እንኖር ነበር ። በቦንብ ድብደባው ሰሞን እያከምቡ ሆስፒታል አምሽቼ ወደቤቴ ስመጣ ..."

ሁኔታው ምን ያህል እየዘገነነው እንደሆን ካተሪን ከድምጹ ተረዳች።

"...ሕንጻው ወድሟል ። የቀረ ምንም ነገር አልነበረም ።"

እጇን ከእጁ ላይ አኖረች ። "በጣም አዝናለሁ ።"

"ይህንን ለመርሳት ብዙ ጊዜ ፈጅቶብኛል ፤ ከዚያ በኋላ ለጋብቻ የምመኛት ሴት አላጋጠመችኝም ። ከዓይኖቹም ውስጥ 'አሁንም ቢሆን' የሚሉ ቃላት ይነበባሉ ።

የባጡን የቆጡን እያነሱ ሲያወጉ በሆቴሉ ውስጥ ለአራት ሰዓታት ያህል ተቀመጡ ። ስለትያትር ፣ ስለሕክምና ፣ ስለዓለም ሁኔታ ሲያወጉ ፣ ዋናውን ነጥብ እስካሁን አላነሱም ። በመካከላቸው አንድ የኤሌክትሪክ ኃይል የተፈጠረ ይመስላል ። ሁለቱንም ይህ ስሜት ተሰምቷቸዋል ። በጉጉትና በምኞት የተወጠረ የወሲብ ፍላጎትም ክፉኛ ተቀስቅሶባቸዋል።

በመጨረሻ አላን ጉዳዩን አፍረጠረጠው ። "ካተሪን ዛሬ ጠዋት ስለሐኪምና ታካሚ ግንኙነት የተናገርኩት ነገር..."

"ስለዚሁ ሁኔታ በመኖሪያ ቤትህ ውስጥ አጫውተኝ ።"

በፍጥነትና በጉጉት ሁለቱም ልብሶቻቸውን አወላለቁ ። ካተሪን በምታወልቅበት ወቅት ከኪርክ ሬኖልድስ ጋር የነበራትን ስሜት አስታወሰች ። የአሁኑ ከዚያን ጊዜው የተለየ ነው ። 'ልዩነቱ በፍቅር በመያዜ ነው' ስትል ካተሪን አሰበች ። 'ከዚህኛው ሰውዬ ፍቅር ይዞኛል።'



አልጋው ላይ ተንጋላ ስትጠብቀው መጥቶ እቅፍ ካደረጋት በኋላ ከእንግዲህ ወደወንድ ልጠጋ አልችልም የሚለው ስጋትና ፍርሃቷ ተነነ ። አንዱ የሌላውን ገላ መጀመሪያ በቀስታ ከዚያም በኃይል እየዳሰሰና እየጨበጠ ከሰውነት ወጥተው የአውሬ ዓይነት ባሕሪይ ወደማሳየት ደረሱ ። አንዱ በሌላው ውስጥ ሰመጠ ። ከፍተኛ ደስታና እርካታ የተሰማትም ካተሪን ድምጿን ከፍ አድርጋ ጮኸች ። 'እንደገና ሙሉ ሰው ሆኛለሁ ።' አለች በአሳቧ ። 'አመሰግናለሁ ።'

አልጋው ላይ ተኝተው ለረዥም ጊዜ ቆዩ ። ዳግመኛ እንዳይለያት ካተሪን ጥብቅ አድርጋ አቀፈችው ።

ለመናገር ትንፋሿ እንደተመለሰ በሚንቀጠቀጥ ድምጿ "በሽተኛን ማከሙን በደንብ ታውቅበታለህ ዶክተር" አለችው ።

# ምዕራፍ ሃያ ስምንት

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ሚስቱን በመግደሉ የተነሳ መታሰሩን ካትሪን በጋዜጣ ላይ እንዳነበበች በጣም ተደናግጣ ነበር ። ከቢሮዋ ስትደርስ ሁሉም ሰው ተክዞ አገኘች ።

"ዜናውን ሰማሽ ?" ስትል ኤቪሊን ጠየቀቻት ።" አሁን ምን እናድርግ ?"

"ከዚህ ቀደም በሰጠን መመሪያ መሠረት ሥራው እንዲካሄድ ማድረግ ። እርግጠኛ ነኝ በስሕተት ነው ያሰሩት ። አሁን በስልክ ላገኘው እሞክራለሁ ።"

ኮንስታንቲን ዴሚሪስን ለማግኘት ግን ከቶ አልተቻለም ።

የአቴንስ ማዕከላዊ እሥር ቤት እስካሁን በቁጥጥር ሥር ካዋላቸው እሥረኞች መካከል በጣም ታዋቂው ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነው ። ለዴሚሪስ ከሌሎች የተለየ እንክብካቤ እንዳይደረግለት የሚያዝ መመሪያ ከሕግ አስከባሪው ተሰጥቷል ። ዴሚሪስ የቴሌፎን ፣ የቴሌክስና ሌሎች መልእክት መለዋወጫ አገልግሎቶች ለማግኘት ጥያቄ ቢያቀርብም ተቀባይነትን አላገኘም ።

ዴሚሪስ ቀንም ሆነ ሌሊት አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው ሜሊናን ማን ገድሏት ይሆን እያለ ሲያሰላስል ነው ።

በመጀመሪያ ላይ ፣ ሌባ የባሕር ዳርቻ ቤቱን ለመመዝበር መጥቶ ሜሊና በድንገት ስለደረሰችበት ገድሏት ይሆናል ብሎ ሲያስብ ነበር ። ፖሊሶች መረጃውን አሰባስበውበት ካፋጠጡት በኋላ ግን ሆን ተብሎ እሱን በወንጀለኛነት ለማጥመድ የተጠነሰሰበት ሤራ መሰለው ። ግን ማን እንዲህ ሊያደርግ ይችላል ? ሊያደርግ የሚችለው ስፒሮስ ላምብሩ ፣ እህቱን ከማንም በላይ ስለሚወዳት ዴሚሪስን ለመወንጀል ብሎ አይገድላትም ከሚል መደምደሚያ ደረሰ ።



የዴሚሪስ ሌላው ጥርጣሬ ከቶኒ ሪዞሊ ጋር ተሰልፈው ባሉት ወሮበሎች ላይ ነው ። ምናልባት በሪዞሊ ላይ የፈፀመውን ነገር ተረድተው በዚህ ዓይነት መንገድ የበቀል እርምጃ መውሰዳቸው ይሆናል ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ይህንንም ግምት አልተቀበለውም ። ማፊያዎቹ የበቀል ርምጃ ቢወስዱ ኖሮ ፍላጻቸው የሚያተኩረው በቀጥታ በኮንስታንቲን ዴሚሪስ ላይ ነው ።

እና በጠባብ የእሥር ክፍሉ ውስጥ ተቀምጦ አእምሮውን እያንከራተተ ለእንቆቅልሹ መፍቻ ለማግኘት ይጥር ነበር ። ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የታሰቡ ጥርጣሬዎች ሁሉ መቋሚ የሌላቸው መሆኑን ሲረዳ መጨረሻ ላይ አንድ አማራጭ ብቻ መኖሩን ተገነዘበ ። የሜሊና ሕይወት ያለፈው በእራሷ እጅ ነው ። ራሷን ገድላ እሱ እንደገዳይ እንዲወነጀል ብላ ነው ። ዴሚሪስ ፣ በኖኤሌ ፓጂና በላሪ ዶግላስ ላይ የፈጸማቸውን ተግባሮች አስታወሰ ። የሚያስገርመው ግን በእነርሱ ላይ የደረሰው በእርሱም ላይ መፈጸሙ ነው ። እንደነሱ ባልፈጸመው የግድያ ወንጀል ክስ ተመስርቶበታል ።

የእሥር ቤቱ ጠባቂ ከዴሚሪስ ክፍል በር ላይ ቆሟል ። "ጠበቃህ ሊያነጋግርህ መጥቷል ።"

ዴሚሪስ ተነስቶ ዘበኛውን ተከተለና ወደአንዲት አዳራሽ አመራ ። ፃሲ ሉኪ የተባለው የሕግ ባለሙያ ይጠብቀው ነበር ። ዕድሜው በሃምሳው አካባቢ ሲሆን የፊልም ኮከብ ተዋናይ አቋም ያለው ሸበቶ ነው። በግድያ ወንጀል ጥብቅና ጥሩ ውጤት ማስገኘቱ ቢነገርለትም ፣ አሁን ጥሩ ውጤት ሊያስገኝ ይችል ይሆን ?

የእሥር ቤቱ ዘበኛ "አሥራ አምስት ደቂቃ ብቻ ነው ያላችሁ" አለና ሁለቱንም በአዳራሹ ውስጥ ትቶ ወጣ ።

"መልካም" ሲል ዴሚሪስ ንግግሩን ጀመረ ። "ከዚህ ሥፍራ መቼ ነው የምታስወጣኝ ? የማታስወጣኝ ከሆነ ለምንስ እከፍልሃለሁ ?"

"ሚስተር ዴሚሪስ ፣ ጉዳዩ ያንን ያህል ቀላል አይመስለኝም ዋናው ሕግ አስከባሪ እምቢ ስላለ ..."

"ዋናው ሕግ አስከባሪ ጅል ነው ። እዚህ ሥፍራ ሊያቆዩኝ አይችሉም ። ገንዘብ በዋስትና ማስያዝስ እንዴት ይመስልሃል ? የጠየቁኝን ያህል ገንዘብ ማስያዝ እችላለሁ ።"

ፃሰ ሉኪ በንዴት ከንፈሮቹን በምላሱ አረጠበ ። "የገንዘብ ዋስትና

ተቀባይነት አላገኝም ። ሚስተር ዴሚሪስ ፖሊሶች በአንተ ላይ ያቀረቡአቸውን ማስረጃዎች መርምሬአለሁ ። ማስረጃዎቹ በጣም ሊጐዱን የሚችሉ ናቸው ።”

“ጐዱንም አልጐዱንም –እኔ ሜሊናን አልገደልኩም ። ከደሟ ንጹህ ነኝ ።”

ጠበቃው ምራቁን ዋጠ ። “አዎ ፣ ትክክል ነህ ፣ ትክክል ። ባለቤትህን ማን ገደላት ብለህ ታስባለህ ?”

“ማንም ። ባለቤቴ ራሷን በራሷ ነው የገደለችው ።”

ጠበቃው ትኩር ብሎ አየው ። “ይቅርታ አድርግልኝና ሚስተር ዴሚሪስ ይህ አባባልህ ጥሩ መከላከያ ሊሆንልን አይችልም ። ከዚህ የተሻለና የሚያዋጣን ጥሩ የመከላከያ አሳብ ማግኘት ይኖርብሃል ።”

ልቦናው የተሰበረው ዴሚሪስ ጠበቃው የተናገረው ነገር ትክክል መሆኑን ተረዳ ። በዓለም ላይ በየትኛውም ፍርድ ቤት በሚሰየሙ የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎች ዘንድ ይህ አባባል ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም ።

በሚቀጥለው ቀን ማለዳ ጠበቃው ወደ ዴሚሪስ ተመልሶ መጣ ።

“መጥፎ ዜና ነው ይዤልህ የመጣሁት ።”

ዴሚሪስ ከት ብሎ ሳቀ ። በጠባብ የእሥር ክፍሉ ውስጥ ተቀምጦ የሞት ቅጣት ፍርድ ሲጠባበቅ ይህ ሞኛሞኝ ደግሞ መጥፎ ዜና ይዤልህ መጣሁ ይለዋል ። አሁን ካለበት ሁኔታ የከፋ ምን ነገር ሊገጥመው ይችላል ?

“እሺ?”

“የዋርሳህ ጉዳይ ነው ።”

“ስፒሮስ ? ምን ሆነ ?”

“ወደፖሊሶች ዘንድ ሄዶ ካተሪን ዶግላስ የተባለችው ሴት በሕይወት ትገኛለች ብሎ እንደነገራቸው የሚገልጽ መረጃ አግኝቻለሁ።”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ እያዳመጠ አልነበረም ። ከየአቅጣጫው በመወጠሩ ካተሪንን ረስቷት ነበር ። ሴትዮዋ ወደአደባባይ ወጥታ የምታውቀውን ምስጢር ካወጣች በኖኤሌ ፓጂና በላሪ ዶግላስ ግድያ ወንጀል እንደገና ሊጠየቅ ነው ። ቀደም ሲል በእርሷ ላይ ርምጃ የሚወስድ ሰው ወደለንደን ቢልክም ተልእኮው አሁን በአጣዳፊ ሁኔታ መፈፀም እንዳለበት ተረድቷል ።



ወደፊት ቀና ብሎ ተቀመጠና የጠበቃውን ክንድ መታ መታ አደረገ። “በአስቸኳይ ወደለንደን መልእክት እንድታስተላልፍልኝ እፈልጋለሁ ።”

መልእክቱን ሁለት ጊዜ እንዳነበበ ዘወትር የኮንትራት ውል ከመፈራረሙ በፊት የወሲብ ፍላጐቱ ለንደሚቀሰቀስበት ሁሉ አሁንም ተቀሰቀሰበት ። የፈጣሪን ሚና እንደመውሰድ ያህል ነው ። ማን እንደሚኖርና ማን እንደሚሞት ወስኗል ። ባለው ኃይሉና ጉልበቱ ተኩራርቷል ። ግን አንድ ችግር አለ ። ይህን ያቀደውን በአስቸኳይ የሚፈፅም ከሆነ ሌላውን ሃሣቡን ተግባራዊ ለማድረግ ጊዜ ሊያጥረው ነው ። ዘዴ መፍጠር ይኖርበታል ። በድንገት የደረሰ አደጋ እንደሚመስል ማድረግ አለበት ። ዛሬ ማታ ።

# ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

## ምስጢራዊ ሰነድ

### ከዊም ቫንዲን ጋር የተካሄደ ውይይት ዶሴ

አላን = ዛሬ ምን ይሰማሃል?

ዊም = ደህና ነኝ ። እዚህ የመጣሁት በታክሲ ነው። የሾፌሩ ስም ፎናልድ ክሪስቲ ይባላል ። የታክሲው ታርጋ ቁጥር 30271 ሆኖ የሊብሬውም ቁጥር 3070 ነው ። ወደዚህ በምንመጣበት ወቅት በአጠገባችን ሰላሳ ሰባት ሮቨሮች ፣ አንድ ቤንትሌይ ፣ አሥር ጃጓሮች ፣ ስድስት አውስቲኖች ፣ አንድ ሮልስ ሮይስ መኪና ሃያ ሰባት ሞተር ብስክሌቶችና ስድስት ብስክሌቶች አልፈዋል ።

አ= ዊም ፣ የቢሮ ሥራህ አሁን እንዴት ነው ?

ዊ= ታውቃለህ ።

አ= ንገረኝ ።

ዊ= እዚያ ያሉትን ሰዎች ጠልቻቸዋለሁ ።

አ = ካተሪን አሌክሳንደርስ? … ዊም ፣ ካተሪን አሌክሳንደርንስ? … ዊም?

ዊ= እርሷማ ፣ ከእንግዲህ እዚያ አትሠራም ።

አ= ምን ማለትህ ነው ?

ዊ= እሷ ልትገደል ነው ።

አ= ምን? ለምን እንደዚያ አልክ ?

ዊ= እርሷ ነገረችኝ ።

አ= ካተሪን ናት እንደምትገደል የነገረችህ ?

ዊ= የለም ሌላ ።

አ= ሌላ ማን ?

ዊ= ሚስቱ ።

አ= የማን ሚስት ዊም ?



ዊ= የኮንስታንቲን ዴሚሪስ

አ= ካተሪን አሌክሳንደር ልትገደል መሆኗን እርሱ ነገረህ ?

ዊ= ሚስስ ዴሚሪስ ፣ ሚስቱ ናት ። የደወለችልኝ ከግሪክ ነው ።

አ= ካተሪንን ማን ሊገድላት ?

ዊ= ከሰዎቹ አንዱ ።

አ= ከአቴንስ ከመጡት ሰዎች መካከል አንዱ ማለትህ ነው ?

ዊ= አዎ ።

አ= ዊም ውይይታችንን እዚህ ላይ እናብቃ ፤ መሄድ አለብኝ ።

ዊ= እሺ ።

# ምዕራፍ ሠላሳ

የሄሌኒክ የንግድ ኮርፖሬሽን ቢሮዎች የሚዘጉት በአሥራ ሁለት ሰዓት ነው ። አሥራ ሁለት ሰዓት ከመሆኑ ጥቂት ደቂቃዎች በፊት ኤቬሊንና ሌሎች ሠራተኞች ከቢሮ ወጥተው ለመሄድ ዝግጅት ያደርጉ ነበር ።

ኤቬሊን ወደ ካተሪን ቢሮ ገባች ። "ሚራክል ኦን ሰርቲፎርዝ ስትሪት" የተባለ ድራማ በክራቴሪያን ይታያል ። በጋዜጣና በሬዲዮ ተደንቋል ። ዛሬ ማታ ልታይው ትፈልጊያለሽ ?"

"አልችልም ። አመሰግናለሁ ኤቬሊን ። ወደትያትር ቤት አብሬው ለመሄድ ለጂሪ ሃሌይ ቃል ገብቼለታለሁ ።"

"ሥራ አበዙብሽ አይደል ? መልካም ጥሩ የመዝናኛ ጊዜ እንዲኖርሽ እመኛለሁ ።"

ሌሎች ሠራተኞች ከቢሮ ወጥተው ሲሄዱ ካተሪን ትሰማ ነበር ። በመጨረሻም ፀጥታ ሰፈነ ። ጠረጴዛዋን ለመጨረሻ ጊዜ አየችውና ሁሉም ነገር በሥርዓት መቀመጡን ካረጋገጠች በኋላ ለብሳ ፣ ቦርሳዋን ይዛ ከቢሮ ወጣች ። ደረጃውን ወርዳ ከዋናው በር አጠገብ እንደደረሰች የስልኩን ድምፅ ሰማች ። ካተሪን ተመልሼ ስልኩን ላንሳ ብላ አመነታች። ሰዓቷን ተመለከተች ። ከቀጠሮዋ የሚያዘገያት ሊሆን ነው ። ስልኩ ጥሪውን ቀጠለ ። ሮጣ ወደ ቢሮዋ ተመለሰችና ስልኩን አነሳች ። "ሃሎ" አለች ።

"ካተሪን" የደወለው አላን ሃሚልተን ነው ። ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ይላል ። "ስላገኘሁሽ ለፈጣሪ ክብር ምስጋና ይግባው ።"

"ችግር አለ ?"



"ሕይወትሽ አደጋ ላይ ነው ። ሰው ሊገድልሽ ነው ።"

እንደማጉመትመት አለች ። አሰቃቂው ቅዠቷ እውን እየሆነ መጥቷል ። ሰውነቷ ደነዘዘ ። "ማን ?" ።

"እኔ አላውቅም ማን ካለሽበት ሥፍራ እንድትቆይ እፈልጋለሁ ። ከቢሮው አትውጪ ። ማንንም እንዳታነጋግሪ ። አሁኑኑ መጥቼ እወስድሻለሁ ።"

"አላን ፣ እኔ …"

"አታስቢ መንገድ ጀምሬአለሁ ። ቆልፈሽ ተቀመጪ ምንም አትሆኚም ።"

ስልኩ ተዘጋ ።

ካተሪን ቀስ ብላ የስልኩን እጀታ አስቀመጠች ። "አቤት አምላኬ !"

አታናስ ከቢሮዋ ፊት ለፊት ቆሟል ። የገረጣውን የካተሪንን ፊት አንዴ ገረመመና ወደቆመችበት ተራመደ ። "ችግር አለ ሚስ አሌክሳንደር ?"

ወደ እርሱ ዞር አለች ። "የሆነ ሰው … አንድ ሰው ሊገድለኝ ነው ።"

ቁና ቁና እየተነፈሰ "ለምን ! ማን … ማን ነው ይህንን ለማድረግ ያሰበው ?"

"እርግጠኛ አይደለሁም ።"

የውጪው በር ሲንኳኳ ሰሙ ።

አታናስ ካተሪንን ተመለከተ ። "ልክፈት … ?"

"የለም" አለች በፍጥነት ። "ማንንም እንዳታስገባ ። ዶክተር ሃሚልተን እየመጣ ነው ።"

የፊትለፊቱ በር ደጋግሞ በኃይል ተንኳኳ ።

"ምድር ቤቱ ውስጥ ልትደበቂ ትችያለሽ" አለና አታናስ በሹክሹክታ ነገራት ። "እዚያ ማንም አይነካሽም ።"

በድንጋጤ መንፈስ በአዎንታ ጭንቅላቷን ነቀነቀች ። "ልክ ነህ ።"

በጓሮ በኩል ዞረው ወደ ምድር ቤቱ አመሩ ።

"ዶክተር ሃሚልተን ሲመጣ የት እንደሆንኩ ንገረው ።"

"እዚያ ለብቻሽ ስትሆኚ አትፈሪም ?"

"አልፈራም" አለች ካተሪን ።

አታናስ መብራቱን አብርቶ ወደ ምድር ቤቱ በሚወስደው መው

ረድ ጀመረ ።

"እዚህ ማንም ሰው ሊያገኝሽ አይችልም ። ሊገድልሽ ስለሚፈልገው ሰውዬ ምንም አታውቂም ?" ሲል አታናስ ጠየቃት ።

ከኮንስታንቲን ዴሚሪስ ጋር ስለ ሕልሞቿ ያደረጉትን ውይይት አስታወሰች ። 'ሊገድልሽማ ነው ። ግን ቅዠት ነበር ያየሽው ።'

"እርግጠኛ አይደለሁም ።"

አታናስ ወደእርሷ ተመለከተና በሹክሹክታ "እኔ የማውቅ ይመስለኛል" አላት ። ካተሪን ትኩር ብላ አየችው ። "ማን ነው ?"

"እኔ ነኝ ።" ከመቅጽበት ትልቅ አውቶማቲክ ሰንጢ አወጣና ጉሮሮዋ ላይ ደገነ ።

"አታናስ ይህ የጨዋታ ጊዜ አይደለም ..."

ሰንጢው ጉሮሮዋን በኃይል ሲጫነው ይሰማት ነበር ።

"ካተሪን አፖይንትመንት ኢን ሳማራ የሚል መጽሐፍ አንብበሽ ፣ ታውቂያለሽ አታውቂም ? መልካም ፣ አሁን ሁሉም ነገር መዳረሻ አግኝቷል ። ያንቺም ያሁኑ ሁኔታ ከሞት ሊያመልጥ ወደሳማራ ሲሄድ እዚያም ሞት እንደጠበቀው ሰው ነው ። ይህ ሥፍራ ላንቺ ሳማራ መሆኑ ነው ። ካተሪን" ። የዋህ ይመስል ከነበረው ልጅ አንደበት እንደዚህ ዓይነት አስፈሪ ቃላት ሲወጡ መስማት በጣም አድርጎ ይዘገንናል ።

"አታናስ እባክህ እንዴት እንዲህ ታደርጋለህ ... "

ፊቷን በጥፊ በኃይል መታት ። "ልጅ በመሆኔ ነው እንዲህ ማድረጌ ያስደነቀሽ ? አትገረሚ ብልሃተኛ ተዋናይ ስለሆንኩ ነው ። ካተሪን ልጅ አልምሰልሽ ፡ ሰላሳ ዓመቴ ነው ። ለምን ልጅ እንደምመስል ታውቂያለሽ? በሕፃንነቴ በቂ ምግብ አላገኝም ነበር ። ማታ ማታ ከቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ የሚበላ ነገር እየሰረቅኩ ነበር ያደግሁት ።" ግድግዳ አስደግፎት ሰንጢውን ጉሮሮዋ ላይ ደግኗል ። "ልጅ በነበርኩበት ወቅት ወታደሮች እናትና አባቴን ገርፈው ሲገድሏቸው በዓይኔ አይቻለሁ ። እኔንም ደብድበው በሞት አፋፍ ላይ ጥለውኝ ነበር ።"

በኃይል እየገፈተራት ወደ ምድር ቤቱ ወሰዳት ።

"አታናስ ፣ እኔ — እኔ አንተን የሚጎዳ ነገር አድርጌ አላውቅም ። እኔ ..."



የጨቅላ ፈገግታ አሳያት ። "ይህን የማደርገው ጠልቼሽ ሳይሆን ሥራ ስለሆነ ነው ። አንቺን ብገድል ሃምሣ ሺህ ዶላር አገኛለሁ ።"

ካተሪን ልክ መጋረጃ ከፊት ለፊቷ የተጣለ ይመስል አይኖቿ በቀይ ብዥታ ተጋርደው ማየት ተሳናት ። ከፊል ሰውነቷ ደግሞ ከግርዶሹ ወጣ ብሎ እየተፈፀመባት ያለውን ድርጊት ያያል ።

"በጣም ግሩም እቅድ ነድፌልሽ ነበር ። ግን አለቃችን በጣም በመቻኮሉ ቶሎ ለፍጻሜ የሚያደርሰኝን ሌላ ዘዴ እንደምንም መፈለግ አለብን ። አይመስልሽም?"

የሰንጢው ጫፍ ስለት ጉሮሮዋን እያሳመመው መጣ ። ስለቱን ወደታች አወረደውና ከፊት ለፊት ያለውን ልብሷን ሸረከተባት ።

"ቆንጆ ነሽ" አላት ። "በጣም ደስ ትያለሽ ። ፓርቲ ልደግስ አስቤ ነበር፤ ግን ዶክተሩ ጓደኛሽ ስለሚመጣ ለዚህ ጊዜ አይኖረንም ። አይመስልሽም? መጥፎ እድል ነው ያለሽ ። እንዴት ያለ ፍቅረኛ ይወጣኝ ነበር መሰለሽ!"

ካተሪን በቆመችበት መተንፈስ አቃታት ።

አታናስ እጁን ወደኪሱ ከተተና ጠርሙስ አወጣ ። በደብዛዛው ጠርሙስ ውስጥ ቀይ ሐምራዊ ቀለም ያለው ፈሳሽ ነበረ ። "ስሊቮቪክ ጠጥተሽ ታውቂያለሽ ? ስለሚደርስብሽ አደጋ ፅዋ እናነሳለን ።" በሰንጢው ጠርሙሱን ለመክፈት ሲሞክር ካተሪን ሮጣ ለማምለጥ ቃጣት።

"በይ ቀጥይ" አለ አታናስ ተዝናንቶ ። "እስቲ ሞክሪው !"

ካተሪን ከንፈሯን መጠጠች ። "ይኸውልህ ፣ እኔ ... ገንዘቡን እሰጥሃለሁ ። እኔ ..."

ትንፋሽሽን ብተቆጥቢ አይሻልም ? አታናስ ጉንጩን ሙሉ ተጎነጨና ጠርሙሱን አቀበላት "ጠጪው ።"

"የለም እኔ አልጠጣም ..."

"ጠጪ !"

ካተሪን ተቀበለችና ትንሽ ተጎነጨች ። ጠንካራው ብራንዲ ጉሮሮዋን አቃጠላት ። አታናስ ጠርሙሱን መልሶ ተቀበላትና በኃይል ተጎነጨ ።

"ሰው ሊገድልሽ መሆኑን ለዶክተሩ ጓደኛሽ የነገረው ማነው ?"

"እኔ—እኔ አላውቅም ።"

"ግድ የለም ። ይህን ያህል አስፈላጊ አይደለም !" አታናስ ጣራውን ደግፎ ወደያዘው የእንጨት ምሰሶ አመለከተ ። "ወደዚያ ሂጂ ።"

ካተሪን ወደበሩ አየች ። በሰንጢው እንደገና አንገቷን ነካ ። "ደግሜ እንድነግርሽ አትፈልጊ ።"

ካተሪን ወደ እንጨቱ ምሰሶ ሄደች ።

"አሁን ገና ጥሩ ልጅ ሆንሽ ። ተቀመጭ" አለ አታናስ ። "ወደኋላው ዞሮ ሲያይ ካተሪን ያቺን አጋጣሚ ተጠቀመች ።

ልቧ በኃይል እየመታ ወደደረጃው አቅጣጫ እግሬ አውጭኝ አለች። ሕይወቷን ለማትረፍ ነው ሩጫው ። ካሰበችበት ደርሳ ገና አንድ ደረጃ ወደ ላይ መውጣት ስትጀምር በጣም የጠነከረ እጅ እግሯን ይዞ ወደ ኋላ ጐተታት ።

"ውሻ !"

ፀጉሯን ጨምድዶ ፊቷን ወደ እራሱ ፊት አስጠጋ ።

"እንዲህ ዓይነቱን ነገር ሁለተኛ ብትሞክሪው ሁለቱንም እግሮችሽን እሰብራቸዋለሁ ።"

ሰንጢው አሁን ብብቷ ላይ አርፏል ።

"ተንቀሳቀሺ"

አታናስ መልሶ ወደእንጨቱ ምሰሶ ወሰዳትና ከመሬት ወረወራት ።

"እዚያው ቆዪ ።"

አታናስ የካርቶን ቁልል በሲባጎ ታስሮ ወደ ተቀመጠበት አቅጣጫ ሲሄድ ካተሪን ትመለከት ነበር ። ከሲባጐው ላይ ርዝመት ያላቸው ሁለት ሲባጐዎችን ቆርጦ ወደ እርሷ ተመለሰ ።

"እጆችሽን ወደኋላሽ ምሰሶው ላይ አስደግፊ"

"አይሆንም አታናስ ። እኔ ..."

ፊቷ ላይ በቡጢ ሲመታት ዞረባት ። አታናስ ወደ እርሷ ጠጋ አለና "ሁለተኛ እምቢ እንዳትይኝ ። ጭንቅላትሽን እንዳልበረቅሰው ያልኩሽን ብትፈጽሚ ይሻልሻል ።"

ካተሪን እንደታዘዘችው እጇን ወደ ኋላ ከምሰሶው ላይ ስታስደግፍ አታናስ ክንዶቿ እስኪከረከሩ ድረስ ጠፈራት ። የደም ሥሮቿ ደም እንደልብ ማስተላለፍ ማቆማቸው ተሰማት ።



"እባክህ" አለች ። "በጣም ወጥረህ ነው ያሰርከኝ ።"

"ጥሩ ነው" አለ እየሳቀ ። ሁለተኛውን ሲባጐ አነሳና ቁርጭምጭሚቶቿን አስሮ ተነስቶ ቆመ ። "የሚፈለገውም ይኸው ነው" አለ ። "በተሳካና በጥሩ ሁኔታ ተከናውኗል ።"

ከጠርሙሱ ውስጥ ለሦስተኛ ጊዜ ተጎነጨ ። "ተጨማሪ መጠጥ ትፈልጊያለሽ ?"

ካተሪን ጭንቅላቷን ነቀነቀች ።

ትከሻውን ነቀነቀ ። "እሺ ።"

ጠርሙሱን እንደገና ወደ አፉ ሲወስድ 'ምናልባት ተሳክቶ እንቅልፍ ይይዘው ይሆናል ?' አለች ካተሪን በአሳቧ ተስፋ በቆረጠ መንፈስ ።

"በቀን አንድ ሊትር ያህል እጠጣለሁ" ሲል አታናስ ጉራውን ነዛ። ባዶውን ጠርሙስ ከሲሚንቶው ወለል ላይ አስቀመጠው ። "መልካም ፣ አሁን ዋናውን ሥራ የምንጀምርበት ጊዜ ደርሷል ።"

"ምን—ምን ልታደርግ ነው ?"

"አንድ ትንሽ አደጋ ልፈጥር ነው ። ይህ ደግሞ በደንብ ታቅዶ የሚፈጸም ተግባር ነው ። ለዚህ ተግባር ዴሚሪስ ከተዋዋልነው በላይ እጥፍ እንዲከፍል እጠይቀዋለሁ ።"

'ዴሚሪስ! እና ነገሩ ሕልም አይደለም ፣ ይህንን ሁሉ የሚያስደርገው እርሱ ነው ማለት ነው ? ግን ለምን ?'

አታናስ ማሞቂያው ወደሚገኝበት ሥፍራ ሲጓዝ ካተሪን ዝም ብላ ከመመልከት በቀር ሌላ አማራጭ አልነበራትም ። የማሞቂያውን ክዳን አነሳና ከውስጥ ያለውን የሙቀት ማመልከቻ እንዲሁም ማሞቂያው እንዲግል የሚያደርጉትን ስምንቱን ምጣዶች ተመለከተ ። የአደጋ መከላከያው ቁልፍ በቀላሉ እንዳይነካካ ከብረት በተሰራ ሽፋን ውስጥ ተደርጓል ። አታናስ አንድ ትንሽ እንጨት አነሳና በመከላከያው ቁልፍ ውስጥ በመሸንቆር ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆን አደረገው ። ማሞቂያው በ150 ዲግሪ ሙቀት ላይ ተደርጎ ቆይቷል ። ካተሪን እያየችው አታናስ ማሞቂያው የመጨረሻ ደረጃ ሙቀት ወደሚሰጥበት ዘወረው ። በፈጸመው ተግባር በመርካት ዞር ብሎ ካተሪን ወዳለችበት አካባቢ መጣ።

"ይህን ማሞቂያ ለማሠራት ምን ያህል ሲያስቸግረን እንደከረመ ታስታውሺያለሽ ?" ሲል አታናስ ጠየቃት ። "መልካም ፣ ከእንግዲህ ስለሱ ብዙ ላንጨነቅ ነው ። አሁን ከናካቴው ሊፈነዳ አይደል ?" አለና

ወደ ካተሪን ተጠጋ ። "ያ የሙቀት መጠን ጠቋሚ ከአራት መቶ ዲግሪ ላይ ሲደርስ ማሞቂያው ይፈነዳል ። ከዚያ በኋላ ምን እንደሚሆን ታውቂያለሽ? የጋዝ ቧንቧዎቹ ይፈነዱና እሳት ይያያዛል ። ከዚያም ሕንጻው በምብ የፈነዳ ይመስል እንዳልነበረ ይሆናል ።"

"አንተ እብድ ነህ ። እዚህ ውስጥ እኮ ሌሎች ንጹሐን ሰዎች አሉ ። ..."

"ንጹህ የሚባል ሰው የለም ። እናንተ አሜሪካኖች በአስደሳች ፍጻሜ ታምናላችሁ ። ሞኞች ናችሁ ። አስደሳች ፍጻሜ ከቶ ሊኖር አይችልም ።" የካተሪንን እጆች ከምሰሶው የጠፈረው ሲባጐ መጥበቅ አለመጥበቁን ለማረጋገጥ ጐንበስ ብሎ ተመለከተ ። የደም አበላ ከእጆቿ ላይ ይታያል ። ገመዱ በጣም ከመጥበቁ የተነሳ አካሏን ሠርስሮታል ። አታናስ በተቀደደው ልብስ በኩል ሾልከው አፍጠው የሚታዩትን የካተሪንን ጡቶች በእጁ ደባበሰና ጐንበስ ብሎ ሳማቸው ። "በጣም አሳዛኝ ነው ፤ በቂ ጊዜ አጣን ። እንደዚት ያለ ነገር እንዳመለጠኝ ባወቅሽ ።"

ፀጉሯን ጨምድዶ ያዘና ከንፈሯን ሳማት ። ትንፋሹ ብራንዲ ብራንዲ ይላል ። "ደህና ሁኚ ካተሪን" አለና ተነስቶ ቆመ ።

"እባክህ ጥለኸኝ አትሂድ" ስትል ለመነች ። "እስቲ እንወያይና ..."

"ወደአቴንስ የሚመልሰኝ አውሮፕላን መነሻ ሰዓት ተዳርሷል ።" ደረጃውን ሲወርድ ዝም ብላ ተመለከተችው ። "ፍጻሜሽን በደንብ ለማየት እንድትችዪ መብራቱን አብርቼ እተውልሻለሁ ።" ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ካተሪን የምድር ቤቱ በር ተከፍቶ ተመልሶ ከውጭ ሲቀረቀር ሰማች ። ከዚያ በኋላ ፀጥታ ሰፈነ ። ለብቻዋ ናት ። ቀና አለችና የማሞቂያውን ቆጣሪ ተመለከተች ። ሙቀቱ በፍጥነት ወደላይ ይገሰግሳል። ከ160 ዲግሪ ወደ 170 ድግሪና ከዚያም በላይ እያሻቀበ ሄደ ። እጇን ከገመዱ ለማስለቀቅ ታገለች ። ስትታገል ገመዱ የበለጠ እየጠበቀ ሄደ ። እንደገና ቀና ብላ እየች የሙቀቱ ቆጣሪ 180 ዲግሪ ደርሶ ከዚያም በላይ እየወጣ ነው ። ምንም ማምለጫ መንገድ አልነበራትም ።

ጨርሶ ምንም ።

አላን ሃሚልተን በዊምፖል ጐዳና በኩል ቁልቁለቱን በመኪናዎች መካከል እየተሽሎከለከ ፤ የሌሎችን አሽከርካሪዎች ግልምጫና የብስጭት



ጡሩንባ እየሰማ እንደእብድ ያሽከረክራል ። ከፊት ለፊቱ ያለው መንገድ ስለተዘጋ ወደግራ ታጠፈና በፖርትላንድ በኩል ወደ አክስፎርድ ሰርከስ ገሰገሰ ። እዚህ ደግሞ የባሰ መኪናዎች በመጨናነቃቸው እንደልብ በፍጥነት መንዳት ተሳነው ።

በ217 ቦንድ ጐዳና ላይ በሚገኘው ምድር ቤት ውስጥ ያለው የማሞቂያው ቆጣሪ ከ200 ዲግሪ ላይ ደርሷል ። ምድር ቤቱ እየጋለ ነው ።

የመኪኖቹ ሁኔታ ጨርሶ አላንቀሳቅሰው አለ ። ሰዎች ወደቤታቸው ይመለሳሉ ፤ ወደ አራትና ትያትር ቤቶች ይገሰግሳሉ ። አላን ሃሚልተን ተስፋ እንደቆረጠ ከመኪናው ውስጥ ተቀምጦ ቀረ ። 'ለፖሊስ መደወል ነበረብኝ! ግን ምን ጥቅም ሊኖረው! አንድ የአእምሮ በሽተኛዬ ሊገድል መሆኑን ሰው ነገረኝ ብል ማን ያምነኛል? ፖሊሶቹ ሊስቁብኝ ይችላሉ። የለም—የለም ፤ ቶሎ ብዬ እርሷው ዘንድ መድረስ አለብኝ ።' መኪኖቹ ትንሽ እየተቃለሉና መንገዱም እየተከፈተ መጣ ።

በምድር ቤቱ ውስጥ የማሞቂያው ቆጣሪ ከ300 ላይ ደርሷል ። ከፍሉ ሊቋቋሙት በማይቻል ከፍተኛ ሙቀት ተውጧል ። እጇን ከገመዱ ለማስለቀቅ እንደገና ስትሞክር የበለጠ ከንዱ ተወጠረ ።

በአክስፎርድ ጐዳና ላይ ባለው የእግረኞች መንገድ ለይ መኪናውን በፍጥነት ማሽከርከር ቀጠለ ። ሁለት አሮጊቶች አቋረጡት ። ከኋላው የትራፊክ ፖሊስ የፊሽካ ድምፅ እንዳሰማ መኪናውን አቁሞ ዕርዳታ ሊጠይቅ አስቦ ነበር ። ግን ስለጉዳዩ ለማስረዳት ጊዜ የለውም ። መንዳቱን ቀጠለ ።

ማቋረጫ ላይ አንድ ከባድ መኪና መንገድ ዘጋበት ። ሃሚልተን ትዕግሥቱ አልቆ ተነጫነጨ ። ጭንቅላቱን በመኪናዋ መስተዋት በኩል ወጣ አደረገና "ተንቀሳቀስ !" አለ ።

የከባድ መኪናው አሽከርካሪ ዞር ብሎ አየው ። "ምን ነካህ ጓዴ ፤ እሳት ውስጥ ልትገባ ነው ?"

መኪኖቹ እንደገና ተጨናንቁ ። መንገዱ ለቀቅ ሲልለት ደግሞ ወደቦንድ ጐዳና በረረ ። ከአሥር ደቂቃ በላይ የማይወስደው መንገድ ግማሽ ሰዓት ያህል ፈጀበት ።

ምድር ቤቱ ውስጥ ያለው መቁጠሪያ 400 ዲግሪ ላይ ደርሷል ።

በመጨረሻ እግዜር አድሎት ሕንፃውን ከፊትለፊት ከሚያይበት ደረጃ ደረሰ ። አላን ሃሚልተን መኪናውን ወደ አንድ ኩርባ አስጠግቶ አቆመና በሩን ቶሎ ከፍቶ ወረደ ። ወደ ሕንፃው አቅጣጫ መሮጥ እንደጀመረ ደነገጠና ቀጥ ብሎ ቆመ ። ሕንፃው እንደ ትልቅ ቦምብ ሲፈነዳ መሬቱ በኃይል ተንቃነቀ ። አካባቢው በእሳት ወላፈንና በጢስ ተሞላ ።

ከዚያ በኋላ ሞት ።



# ምዕራፍ ሠላሳ አንድ

አታናስ ስታቪችን የወሲብ ፍላጐቱ በጣም ተቀስቅሶበታል ። የተፈራረመውን ኮንትራት በተግባር ሲፈፅም ሁልጊዜ እንዲህ ዓይነት ውስጣዊ ስሜት ያድርበታል ። ሊገድላት የተላከባትን ሴት ሲጥ ከማድረጉ በፊት ከሷ ጋር ወሲብ መፈጸምን እንደመመሪያ አድርጐ ይዞታል ። አሁን ግን ተበሳጭቷል ፤ ምክንያቱም ካተሪንን ለማሰቃየትም ሆነ አብሯት ወሲብ ለመፈጸም የሚያስችለው በቂ ጊዜ አላገኘም ። አታናስ ሰዓቱን ተመለከተ ። አሁንም ጊዜው ገና ነው ። አውሮፕላኑ የሚነሳው ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ ነው ። ወደሼፐርድ የገበያ ሥፍራ በታክሲ ተጓዘና ከታክሲው ወርዶ በጐዳናዎቹ ላይ መራመድ ጀመረ ። በጐዳናዎቹ ላይ በሺህ የሚቆጠሩ ሴቶች ግራና ቀኝ ተሰልፈው ቆመው በዚያ የሚያልፈውን ወንድ ሁሉ ይለክፉሉ ።

‘ሰላም ፣ የእኔ ፍቅር ፣ ዛሬ ማታ ከኔ ጋር አብረህ ለማምሸት ትፈልጋለህ?’

‘ትንሽ ፓርቲ ብናደርግስ ምን ይመስልሃል?’

‘የግሪክ ዓይነቱን ትሻለህ?’

ሆኖም አንዲት ሴት እንኳ አታናስን እንዲህ አላለችውም ። አጭር የቆዳ ቀሚስ ለብሳ ረዥም ታኮ ወደተጫማችው ባለወርቅማ ፀጉር ረዥም ሴት ተጠጋ ።

“እንደምን አመሸሽ?” አለ አታናስ በትህትና ።

በሁኔታው ተገረመችና አቆልቁላ እየችው ። “ሰላም አንተ ትንሽ ልጅ ። እዚህ መምጣትህን እናትህ ታውቃለች?”

አታናስ በሐፍረት ፈገግ አለ ። “አዎ እመቤቴ ። ሥራ የማይበዛብሽ ከሆነ …” ሴተኛ አዳሪዋ ሳቀች ። “ከሆነ ምን ልታደርግ? ሥራ የማይበዛብኝ ከሆነ ምን ልታደርግ? ከዚህ በፊት ከሴት ጋር ተገናኝተህ ታውቃለህ?”

“እንዴ ፣” አለ አታናስ በለሆሳስ ። “በጣም ወድጀው ነበር ።”

“አንተኮ ጨጨ ነህ” አለችና ሳቀች ። “ብዙውን ጊዜ እንዳንተ ያሉትን ጨጨዎች እመልሳቸዋለሁ ፤ ግን ዛሬ ሥራ የለም ለመሆኑ አሥር ይዘሃል?”

“አዎ እመቤቴ ።”

“እሺ የእኔ ፍቅር እንግዲያውስ ወደፎቅ እንውጣ ።”

አታናስን መርታ ወደፎቅ አወጣችውና ከአንድ ክፍል ደረሱ ።

አታናስ ገንዘቡን ሰጣትና የሄደበትን ጉዳይ ጨርሶ ዓይኑን ሲገልጥ አብራው የነበረችው ካተሪን አለመሆኗን ተረዳ ። በአንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ ከአንዲት አስቀያሚ ሴተኛ አዳሪ ጋር ነው ተኝቶ ያለው ። ልብሱን ለበሰና በታክሲ ተሳፍሮ ወደሆቴሉ በመሄድ ሻንጣውን ይዞ ወጣ ።

ወደአውሮፕላን ማረፊያ ጉዞ ሲጀምር ሰዓቱ ከምሽቱ ሦስት ተኩል ነበረ ። ከአውሮፕላኑ ለመድረስ በቂ ጊዜ አለው ።

ተሰልፈው ያሉ የኦሎምፒክ አየር መንገድ ተሳፋሪዎች ጥቂት ናቸው አታናስ ተሰልፎ ተራው ሲደርስ ለሠራተኛው ቲኬቱን አሳየ ። “አውሮፕላኑ በሰዓቱ ነው የሚነሳው?”

“አዎ” አለና ሠራተኛው ቲኬቱ ላይ የሠፈረውን ስም ተመከተ ። ‘አታናስ ስታቪች’ ይላል ። እንደገና ቀና ብሎ ወደ አታናስ ተመለከተና ዞር ብሎ አጠገቡ ቆሞ ወዳለው ሰው አይቶ ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። ሰውዬው ወደ ቲኬት ማፅደቂያው ጠረጴዛ ተጠጋ ።

“እስቲ ትኬትህን ልየው?”

አታናስ ቲኬቱን ሰጠውና “ችግር አለ?” ሲል ጠየቀ ። ሰውዬው መለሰና “ለዚህ በረራ የተመዘገቡ ሰዎች ቁጥር የበዛ ይመስለኛል ።

አታናስ ትከሻውን ነቀነቀ ። “እሺ” አለና በልበ ሙሉነት ሰውዬውን ተከትሎ ወደቢሮ ሄደ ። ይሄኔ ዴሚሬስ ከእሥር ተለቆ ሊሆን ይችላል ። ሰውዬው ሕግ የማይገዛው ዝነኛ ሰው ነው ። ሁሉም ነገር እንደታቀደው ተከናውኗል ። የሚቀበለውን ሃምሣ ሺህ ዶላር በስዊስ ባንክ ውስጥ ከከፈታቸው የተለያዩ ደብተሮች በአንደኛው ሊያስቀምጥ ይችላል ። ከዚህ በኋላ ለዕረፍት ወደሪቪኢራ ወይም ሪኦ ይሄዳል ። በተለይ በሪኦ የሚወደው ነገር አለ ።



አታናስ ወደቢሮው ውስጥ ገባና ቆም ብሎ አፈጠጠ ። ፊቱ ገረጣ ። “ሞተሻል! ሞተሽ የለ እንዴ! ገድዬሻለሁ!” እያለ ጩኸቱን ለቀቀ ።

ከክፍሉ አውጥተው ወደተዘጋጀው የፖሊስ መኪና ሲወስዱትም አታናስ ጩኸቱን አላቆመም ነበር ። መኪናው ውስጥ ገብቶ ሲሄድ እነ አላን ሃሚልተን ያዩታል ። አላን ወደ ካተሪን ዞር አለና “እዚህ ላይ አበቃ ፍቅሬ ፣ ከእንግዲህ ተገላግለናል” ሲል ተናገረ ።

# ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት

ከጥቂት ሰዓታት በፊት ካተሪን እጆቿን ከገመዱ እሥራት ለማላቀቅ በምድር ቤቱ ውስጥ ብዙ ታግላለች ። በተወራጨችና በታገለች ቁጥር ገመዱም ይበልጥ ጠብቆባታል ። ጣቶቿ ደንዝዘዋል ። በማሞቂያው ላይ ያለውን ቆጣሪ አሁንም አሁንም ታይ ነበር ። ቆጣሪው ከ250 ዲግሪ ላይ ደርሷል ። 'ያ ቆጣሪ ከ400 ዲግሪ ላይ ሲደርስ ማሞቂያው ይፈነዳል ። ከዚህ ለማምለጥ አንድ ዘዴ መገኘት ይኖርበታል' አለች ካተሪን በአሳቧ ።

'ዘዴ መገኘት ይኖርበታል ።' የካተሪን ዓይን በወለሉ ላይ በተጣለው የብራንዲ ጠርሙስ ላይ አረፈ ። አተኩራ ስታየው ልቧ በኃይል መምታት ጀመረ ። 'አንድ ዕድል አለኝ' አለች በአሳቧ 'የምችል ከሆነ ።' … ካተሪን ከታሰረችበት ምሰሶ እራሷን ለማላቀቅ ወደፊት ተንጠራራችና በእግሯ ጠርሙሱን ለመንካት ሞከረች ። ልትደርስበት አልቻለችም ። የበለጠ ስትንጠራራ የምሰሶው ስንጥር ጀርባዋን ወጋጋው ። ጠርሙሱ ከእግሯ አንድ ኢንች ያህል ርቆ ይገኛል ። የካተሪን ዓይኖች እንባ አቀረሩ። 'አንድ ጊዜ ልሞክር' አለች በአሳቧ ። 'አንዴ ብቻ ።' እንደገና ባለ በሌለ ኃይሏ ወደፊት ስትንጠራራ ፤ ስንጥሮቹ የበለጠ ጀርባዋን ወጋጉት ። አንዱ እግሯ ጠርሙሱን ነካው ። 'ጥንቃቄ ፤ ገፍቼ እንዳላርቀው' የሚል አሳብ በአእምሮዋ ብልጭ አለ ። ቀስ በቀስ የጠርሙሱን አንገት እግሯን ባሰረው ገመድ ውስጥ ከተተች ። ጥንቃቄ በተመላበት ሁኔታ እግሯን አጠፈችና ጠርሙሱን አስጠጋች ። አሁን ጠርሙሱ ከእጠገቧ ነው ።

ቀና ብላ የማሞቂያውን ቆጣሪ ተመለከተች ፤ አሁን ከ280 ዲግሪ ደርሷል ። ክፉኛ ተደናግጣለች ። ቀስ ብላ ጠርሙሱን በእግሯ ወደኋላጥ ገፋች ። ጣቶቿ ወደ ጠርሙሱ ቢደርሱም ደንዝዘው ስለነበረ እንደምትፈልገው ሊጨብጡላት አልቻሉም ። ከእጅ ጡንቻዎቿም የሚንጠባጠበው የደም እበላ እጆቿን አርሶ እንዲያሙለጨልጩ አድርጓቸዋል ።

ምድር ቤቱ በጣም እየሞቀ መጥቷል ። እንደገና ሞከረች ፤ ግን



ጠርሙሱ ተሙለጭልጮ ወደቀ ። ካተሪን ቆጣሪውን ስታየው ከ300 ዲግሪ የደረሰ ሲሆን በፍጥነት ማሻቀቡን ቀጥሏል ። ከማሞቂያው ውስጥ እንፋሎት መውጣት ጀምሯል ። እንደገና ጠርሙሱን ለመጨበጥ ሞከረች።

አዎ አሁን ጠርሙሱን በእጇ ጨበጠች ። ጠበቅ አድርጋ ያዘችውና ምሰሶው ላይ ልትሰብረው ሞከረች ። አልተሰበረም ። ተስፋ በመቁረጥ ድምጿን ከፍ አድርጋ ጮኸች ። እንደገና ሞከረችው ፤ አሁንም ምንም ለውጥ አልተገኘም ። ቆጣሪው አሁን ከ350 ዲግሪ ላይ ደርሷል ። ካተሪን በኃይል ወደውስጥ ተነፈሰችና ባለ በሌለ ጉልበቷ እንደገና ልትሰብረው ሞከረች ። የመሰበር ድምፅ ሰማች ። 'እግዚአብሔር ይመስገን' አለችና በፍጥነት አንዱን ስባሪ አንስታ ገመዱን መገዝገዝ ጀመረች ። ጡንቻዋን ቢቆርጠውም ሕመሙን ተቋቁማ ገመዱን መበጣጠስ ቀጠለች ። ወዲያው አንዱ እጇ ተለቀቀ ። ሌላውን እጇንም እንዲሁ በመጨረሻ ፈታች ። ይኼኔ ቆጣሪው ከ380 ዲግሪ ደርሷል ። ከማሞቂያው ውስጥ እንፋሎት በኃይል ቡልቅ ቡልቅ ይላል ። ካተሪን ዘላ ተነስታ ቆመች ። አታናስ የምድር ቤቱን በር ከውጭ ዘግቶታል ። ። ከፍንዳታው በፊት ከሕንፃው ውስጥ ለማምለጥ የሚቻልበት በቂ ጊዜ የለም ።

ካተሪን ወደማሞቂያው ሮጣ የአደጋ መከላከያው እንዳይሠራ የተሸነቀረበትን እንጨት መዝዛ ስታወጣ ቆጣሪው ከ400 ዲግሪ ደርሷል።

ከውሳኔ ላይ ለመድረስ በጣም አጭር ጊዜ ነበራት ። ወደፍንዳታ መከላከያው ክፍል ሮጣ በሩን ከፍታ ዘው አለችና በኃይል ወረወራ ዘጋችው ። ቁና ቁና እየተነፈሰች ወለሉ ላይ እንደተዘረረች ከአምስት ደቂቃ በኋላ ከፍተኛ ፍንዳታ ደረሰና ክፍሉ ክፉኛ ተንቃነቀ ። በጨለማው ውስጥ ወለሉ ላይ ተኝታ ከውጭ የሚንቀለቀለውን የእሳት ወላፈን ድምፅ ትሰማ ነበር ። ምንም ጉዳት አልደረሰባትም ፤ ፍንዳታውም አልቋል ። 'የለም ። አሁንም ገና ነው' አለች ካተሪን በአሳቧ ። 'አሁንም ማድረግ ያለብኝ ነገር አለ ።'

የእሳት አደጋ መከላከያ ሠራተኞች ከአንድ ሰዓት በኋላ ደርሰው ሲያወጧት አላን ሃሚልተንም እዚያው ነበር ። ካተሪን ሮጣ አቀፈችው ፤ እርሱም ጥብቅ አድርጎ ያዛት ።

"ካተሪን የእኔ ፍቅር ፤ በጣም ፈርቼ ነበር ፤ ለመሆኑ እንዴት …?"

"በኋላ" አለች ካተሪን ። "አታናስ ስታቪችን ማስያዝ አለብን ።"

# ምዕራፍ ሰላሳ ሦስት

በሱሴክስ በሚገኘው የአላን እህት የእርሻ ቦታ ማንንም ተጋባዥ ሳይጠሩ የጋብቻ ሥነ ሥርዓታቸውን ፈጸሙ ። ካተሪን በአላን ቢሮ ውስጥ እንዳየችው ፎቶግራፍ የአላን እህት ፍፁም ደስ የምትል ሆና አግኝታታለች ። ልጇ ወደ ትምህርት ቤት ሄዷል ። ካተሪንና አላን ቅዳሜና እሁድን እየተዝናኑ በእርሻው አካባቢ ካሳለፉ በኋላ ለጫጉላ ጊዜያቸው ወደቬነስ በረሩ ።

ቬነስ በመካከለኛው ዘመን ታሪኳ የታወቀች ናት ። ለመርከብና ለጀልባ መጓጓዣ በይ የተቆፈረላት ፣ 120 ደሴቶቿ በ400 ድልድዮች የተያያዙላት ውብ ከተማ ናት ። አላንና ካተሪን ሜስትሬ አጠገብ ከሚገኘው ማርኮፓሎ የቬነስ አውሮፕላን ማረፊያ እንደደረሱ በሞተር ጀልባ ተሳፍረው ወደፒአዛ ሳን ማርኮ አመሩ ። ከዚያም እንደደረሱ በዶጅስ ቤተመንግሥት አጠገብ ካለው የሮያል ዳኒኤሊ ሆቴል ውስጥ ክፍል ተከራዩ ።

ክፍላቸው ልዩና ውብ ሲሆን በጥንታዊ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች አጊጧል ። መኝታ ቤቱ ውስጥ ሆኖ ዋናውን ትልቅ ቦይ መመልከት ይቻላል ።

*"በመጀመሪያ ምን ለማድረግ ትፈልጊያለሽ?" ሲል አላን ጠየቃት።*
*ካተሪን ወደእርሱ ተጠጋችና እቅፍ አደረገችው ። "እስቲ ገምት።"*
*ዕቃቸውን ከሻንጣቸው ያወጡት በኋላ ነው ።*

ካተሪን ያለፈውን ቅዠቷንና አስፈሪ ነገሮችን እንድትረሳ ቬኒስ ፈዋሽ መድኃኒቷ ሆነች ።

ከአላን ጋር ብዙ ሥፍራ ጐበኙ ። የብዙ መቶ ዓመታት ዕድሜ ያለው የቅዱስ ማርቆስ አደባባይ ከሆቴላቸው 100 ያርድ ያህል ብቻ ርቆ ይገኛል ። የቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል ቤተክርስቲያንም ፣ የሥዕል ማሳያም ነው ። በግምቡና በጣሪያው ልዩ ልዩ አይነ–ግብ ሥዕሎች ተስለዋል።



ወደዶጅስ ቤተመንግሥት ገብተው በውስጡ ያሉትን ክፍሎች ጐበኙ ። ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ሞት የተፈረደባቸው እሥረኞች ሲገደሉ ሲወሰዱ ከሚያልፉበት የሳይስ ድልድይ ላይ ቆመው ተመለከቱ ።

የተለያዩ ሙዚየሞችን ፣ አብያተ ክርስቲያናትንና ደሴቶችን እየተዘዋወሩ አዩ ። በሙራኖም የመስተዋት ሥራን ፣ በቡራኖ የሴቶችን የጥልፍ ሥራ ተመለከቱ ። በሞተር ጀልባ ወደቶርሴሎ ተጉዘው በአበባ ተክል በተዋበችው በሉካንዳ ሲፕሪአኒ ሆቴል ምሣ ተመገቡ ።

ካተሪን የሴቶቹን ገዳም የአትክልት ሥፍራ አስታወሰችና ምን ያህል ጠፍታና ተበላሽታ እንደነበር ተገነዘበች ። ከፊት ለፊቷ የተቀመጠውን ፍቅረኛዋን አላንን እያየች በልቧ 'እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ' አለች ።

ሜርሴሪ ፣ ቆንጆ – ቆንጆ ፣ በርካታ መደብሮች ያሉባት አካባቢ ነች። ከሩቤሉ መደብር ልብሶችን ፣ ከካሳላ መደብር ጫማዎችን ፣ ከጂአኮንዶ ካሲኒ ሉቅ ብርቅዬ ዕቃዎችን ሸማመቱ ። በኳድሪና አል ግራስታ ዴሎአና እንዲሁም በሃሪ ባር ሆቴሎች ተመገቡ ። በትልቁ ጉንዶላና በትንሽ ሳንዶሊ ታንኳዎች ተንሸራሸሩ ።

መመለሻቸው ሲቃረብ ዓርብ ዕለት መጠነኛ ዝናብ ዘነበ ፤ አውሎ ነፋስም ተነሳ ።

ካተሪንና አላን ቶሎ ብለው ወደሆቴል ክፍላቸው ተመለሱ ። ከመኝታ ቤታቸው ሆነው በመስኮት በኩል እያዩ "በመዝነቡ በጣም አዝናለሁ ሚስስ ሃሚልተን" አለ አላን እየቀለደ ። "ስለአየር ጠባዩ የሚገልፀው ወረቀት ፀሐይ እንደሚኖር ነበር የጠቆመኝ ።"

ካተሪን ፈገግ አለች ። "የምን ዝናብ? ፍቅርዬ እኔን በጣም ደስ ብሎኛል ።"

በሰማዩ ላይ ብልጭታ ታይቶ የመብረቅ ድምፅ መሰማቱ ካተሪን የማሞቂያውን ፍንዳታ እንድታስታውስ አደረጋት ።

ወደአላን ዞር አለች ። "ዛሬ የፍርድ ውሳኔ ሰጭዎቹ ፍርድ የሚሰጡበት ቀን አይደለምን?" ስትል ጠየቀችው ።

ትንሽ አመነታ ። "አዎ ፣ ነገሩን ያላነሳሁብሽ ለምን መሰለሽ ..."
"መጥፎ ነገር የማስታውስ መስሎህ ነው? ደህና ነኝ ለማወቅ ነው።"
ትኩር ብሎ እያትና ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "እሺ ።"

አላን ሬድዮኑ ወደተቀመጠበት ሥፍራ ሄዶ ሬድዮኑን ሲከፍት ካተሪን ዝም ብላ ታይ ነበር ። ሬድዮኑን ጐራጐረና ከቢቢሲ ጣቢያ ላይ መሥመሩን አቆመ ።

" … ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዛሬ የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤያቸውን አቀረቡ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አዲስ መንግሥት ያቋቁማሉ ።" የራድዮው ድምፅ ብቅ እልም እያለ በደንብ አይሰማም ።

"ያ መብረቅ አዘል አውሎ ነፋስ ነው እክል የሚፈጥረው" አለ አላን።

የራድዮው ድምፅ እንደገና መሰማት ጀመረ ። "በአቴንስ የኮንስታንቲን ዴሚሪስ ክስ ከማጠቃለያ ላይ የደረሰ ሲሆን የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የቀድሞ ውሳኔያቸውን በማጠፍ ብዙ ሰዎችን ባስገረመው ሁኔታ ፈረዱ …"

የሬድዮው ድምፅ ጠፋ ።

ካተሪን ወደ አላን ዞር አለች ። "ምን … ፍርዱ ምን ይመስልሃል?"

እቅፍ አደረጋትና "በመልካም ፍፃሜ ማመንና አለማመንሽ ይህንን ይወስነዋል" አላት ።



# መደረሻ

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ፍርድ ቤት በመቅረቡ ከአምስት ቀናት በፊት ጠባቂው ዘበኛ የእሥር ቤቱን በር ከፈተለት ።

"ጠያቂ መጥቶልሃል ።"

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ቀና ብሎ አየው ። ከጠበቃው በስተቀር እስካሁን ድረስ ማንም ጎብኚ እንዲያየው አልተፈቀደም ነበር ። ፊቱ ላይ ምንም ዓይነት ጉጉት አላስነበበም ። አንኒያ ውላጆች እንደተራ ወንጀለኛ ነበር የቆጠሩት ። የውስጥ ስሜቱን አሳይቶ ደስ ሊያሰኛቸው አልፈቀደም ። የእሥር ቤቱን ዘብ ተከትሎ ወደ አንዲት የስብሰባ አዳራሽ አመራ ።

"እዚያ አለልህ ።"

ዴሚሪስ ከክፍሉ ውስጥ እንደገባ በተሽከርካሪው ወንበር ላይ ጎብጦ የተቀመጠ አካለ ስንኩል ሽማግሌ ተመለከተ ። ፀጉሩ እንደ በረዶ የነጣ ነው ። ፊቱ የተለበለበ ሳምባ ይመስላል ። የተቆለመመ ከንፈሮቹ ፈገግታ ለማሳየት ሲሉ ያስፈራሉ ። ዴሚሪስ ጎብኚው ማን እንደሆነ ለማወቅ ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም ። በድንጋጤ አመዱ ቡን አለ ።

"ያንተ ያለህ!"

"ጎዕረሞት አይደለሁም" አለ ናፖሊዮን ቾታስ በጐረነነ ድምጽ ። "ግባ በል ኮስታ!"

ዴሚሪስ በግድ መናገር ጀመረ ። "እሳቱ …"

"በመስኮት በኩል ዘልዩ ወጣሁና ወገቤ ተሰበረ ። የእሳት አደጋ ተከላካዮች ከመድረሳቸው በፊት የእልፍኝ አሽከሬ ደርሶ ገለል አደረገኝ ። በሕይወት መኖሬን እንድታውቅ አልፈለግኩም ነበር ። ከአንተ ጋር ግብግብ መግጠሙ ሰልችቶኛል ።"

"ማን … ያኔ የተገኘውስ አስከሬን?"

"የቤቱ ጠባቂ ነው ።"

ዴሚሪስ ወንበር ላይ ዘፍ አለ ። "ሕይወትህ በመትረፉ ደስ ብሎኛል" አለ በደከመ ድምፅ ።

"ደስ ሊልህ ይገባል ። ሕይወትህን ላተርፍ ነው ።"

ዴሚሪስ በጥርጣሬ አተኩሮ አየው ።

“አንተ ልታተርፈኝ?”

“አዎ ። እኔ ጥብቅና ልቆምልህ ነው ።”

ዴሚሪስ ከት ብሎ ሳቀ ። “የምርህን ነው … ሊዮን? ከዚህ ሁሉ ዓመት በኋላ አሁንም እንደምኝ ትቆጥረኛለህ? ለመሆኑ ሕይወቴን ባንተ መዳፍ ውስጥ የምጥል እንዴት ሊመስልህ ቻለ?”

“ምክንያቱም ኮስታ ፣ ሕይወትህን ለማትረፍ የምችለው እኔ ብቻ ስለሆንኩ ነው ።”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ተነሳና “አልፈልግም ለማንኛውም አመሰግ ናለሁ” በማለት ወደበሩ አመራ ።

“ስፒሮስ ላምብሩን አነጋግሬዋለሁ ። እህቱ በተገደለችበት ሰዓት ከአንተ ጋር እንደቆየ ምስክርነቱን እንዲሰጥ አግባብቼዋለሁ ።”

ዴሚሪስ ቆም ብሎ ወደኋላው ዞረና “ለምን ብሎ ይመሰክርል ኛል?” ሲል ጠየቀው።

ቾታስ ወንበሩ ውስጥ እንዳለ ወደፊት አዘመመ ። “ሕይወትክን ከማጥፋቱ ይልቅ በቁምህ ሀብትህን በሙሉ በመንጠቅ መበቀሉ የበለጠ እንደሚያረካው ስላሳመንኩት ።”

“በጇ ።”

“እሚመሰክርልህ ከሆነ መላ ሀብትህንና ንብረትህን እንደምታስረ ክበው አረጋገጥኩለት ። ኩባንያዎችህን ፣ መርከቦችህን ፣ ማንኛውንም ቅርስህን …”

“አብደሀል መሰለኝ?”

“እመስልሃለሁ? ኮስታ እስቲ አስብበት ።”

“የእርሱ ምስክርነት ሕይወትህን ሊያተርፍ ይችላል ። ሀብትህ ከሕይወትህ ይበልጥብሀል እንዴ?”

ለረዥም ጊዜ ፀጥታ ሰፈነ ። ዴሚሪስ ተመልሶ ተቀመጠ ። “ሜሊና በተገደለችበት ወቅት ከእርሱ ጋር እንደነበርኩ ላምብሩ ሊመሰክርልኝ ፈቃደኛ ነው?”

“አዎን ።”

“በምላሹ ከኔ የሚፈልገው …”

“ያፈራኸውን ሁሉ እንድትሰጠው ።”

ዴሚሪስ ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። “አንድ ነገር ለራሴ ማስቀረት …”



“አትችልም ። ሙልጭህን ሊያስቀርህ ፈልጓል ። እንደበቀል የሚቆጥረውም ይህንን ነው ።”

ዴሚሪስን ያስገረመው ሌላም ነገር አለ ። “ይህን ሁሉ በማድረግ አንተስ የምታገኘው ምንድርነው ሊዮን?” ሲል ቾታስን በጭንቀት ጠየቀው ።

የቾታስ ክንፈሮች ፈገግታ ሊያሳዩ ሞከሩ ፤ ያልተሳካ ጥረት ። “ሁሉንም” ብሎ መለሰለት ።

“እ … አልገባኝም ።”

“የሄሌኒክ ንግድ ኩባንያን ወደላምብሩ ይዞታ ከማዛወርህ በፊት የኩባንያውን ንብረት ሁሉ የእኔ ንብረት ወደሆነው ወደ አዲስ ኩባንያ ታዛውራለህ ።”

ዴሚሪስ ትኩር ብሎ አየው ። “እና ላምብሩ ምንም አያገኝም ማለት ነዋ!”

ቾታስ ትከሻውን ነቀነቀ ። “አሸናፊዎች እንዳሉ ሁሉ ተሸናፊዎ ችም አሉ ።”

“ላምብሩ ጥርጣሬ አያድርበትም?”

“አሠራሬ ጥርጣሬ አያሳድርም ።”

“ላምብሩን በዚህ ዓይነት የምታታልለው ከሆነ እኔንም ላለማታለ ልህ ምን ማረጋገጫ አለኝ?”

“ቀላል ነው ውድ ኮስታ ፡ ሥጋት አይግባህ ። ኩባንያው የኔ የሚሆነው አንተ በነፃ ስትለቀቅ ብቻ መሆኑን ጠቅሰን እንፈራረማለን ። ወንጀለኛ ሆነህ ከተገኘህ እኔም ምንም አላገኝም ።”

ለመጀመሪያ ጊዜ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በጉዳዩ ተመስጦ ከተቀመጠበት ሆኖ አካለ ስንኩሉን የሕግ ባለሙያ በጥሞና ተመለከተ ። ‘እኔን ሊበቀልስ ሲል ከፍርድ ቤቱ ሊያገኝ የሚቻለውን በብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ካሳ ለማጣት ይፈልጋል? በፍጹም ያን ያህልስ ጅል አይደለም ።’ “መልካም” አለ ዴሚሪስ ። “ተስማምቻለሁ ።”

ቾታስ “ጥሩ ፣ ኮስታ አሁን ገና ሕይወትህን አተረፍክ” አለው ።

‘መች ሕይወቴን ብቻ’ አለ ዴሚሪስ በአሸናፊነት መንፈስ በልቡ ። ‘ማንም ሰው ሊያገኘው በማይችል ሥፍራ አንድ መቶ ሚሊዮን ዶላር ያህል ደብቄአለሁ ።’

ቾታስ ከስፒሮስ ላምብሩ ጋር ያደረገው ውይይት በቀላሉ ከመግባባት ላይ የተደረሰበት አይደለም ።

"መስክረህ የዚያን አረመኔ ሕይወት አትርፍለት ነው የምትለኝ? በል ከዚህ ውጣልኝ ።"

"ልትበቀለው ትፈልግ የለ?" ሲል ቾታስ ጠየቀው ።

"እየተበቀልኩትማ ነው ።"

"ነው እንዴ? ኮስታን ታውቀዋለህ! ሀብቱ ከሕይወቱ ይበልጥበታል። ብትገድለው ጣሩ ለቅጽበት ብቻ ተሰምቶው ወዲያው ያልፋል ። ያለውን ሁሉ ወስደህበት በባዶ ኪሱ ከኑሮ ጋር ካጋፈጥከው ግን ከሞት በባሰ ቅጣት ቀጣኸው ማለት ነው ። አይገባህም?"

የሕግ ባለሙያው ያለው እውነትነት አለው ። እስካሁን ካጋጠሙት ሰዎች መካከል እንደዴሚሪስ ስስታም ሰው አላየም ። "ያለውን ሀብት በሙሉ አሳልፎ ሊሰጠኝ ተስማምቷል ነው የምትለው?"

"ሳንቲም ሳትቀር ስልህ! በየብስ ፣ በአየርና በባሕር ያሉ ይዞታዎቹንም ሆኑ ኩባንያዎቹን ሁሉ ።"

አባባሉ በጣም የሚያጓጓ ነው ። "እስቲ ላስብበት" ካለ በኋላ የሕግ ባለሙያው ተሽከርካሪ ወንበሩን እያሽከረከረ ከቢሮው ሲወጣ ላምብሩ ዝም ብሎ ተመለከተው ። 'እስቲ እንዲህ ሆኖ መኖር ያስመኛል?' አለ በልቡ ።

እኩለ ሌሊት ላይ ስፒሮስ ላምብሩ ለናፖሊዮን ቾታስ ስልክ ደወለለት ። "ከውሳኔ ደርሻለሁ በሃሳብህ እስማማለሁ ።"

የዜና ማሰራጫዎች የሚያሯሯጡት ትኩስ ዜና ሆነ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ባለቤቱን በመግደሉ የወንጀል ክስ የተመሠረተበት መሆኑ ብቻ ሳይሆን በእሳት አደጋ ሞቷል ተብሎ የነበረ ዝነኛ ጠበቃ በሕይወት ተገኝቶ ጥብቅና የቆመለት መሆኑ ጭምር ጉዳዩን የበለጠ አስገራሚ አድርጎታል ።

ችሎቱ የተሰየመበት ክፍል ያኔ ኖኤሌ ፓጂና የላሪ ዶግላስ ክስ የታየበት ያው ክፍል ነው ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ብድንብ ሊታይ ከማይችልበት የተከሳሽ መቀመጫ ሥር ተቀምጧል ። ክሱ ቀጥሎ ናፖሊዮን ቾታስ በተሽከርካሪ ወንበሩ ላይ ተኮፍሷል ። የሕግ ተወካይ ሆነ



በከሳሽ ወገን የቆመው ልዩ አቃቤ ሕግ ዴልማ ነው ።

ዴልማ ለፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ የሚከተለውን ቃል አሰማ ፦

"ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በዓለም ውስጥ በጣም ታዋቂ ከሆኑትና ተደማጭነትን ካላቸው ሰዎች መካከል አንዱ ነው ። ወደርየለሽ የሆነው ሀብቱ ያሻውን ብዙ ነገር ለማድረግ አስችሎታል ። ቢሆንም አረመኔያዊ ግድያ የመፈፀምን መብት ሊያስከብርለት አልቻለም ። ማንም ቢሆን እንዲህ ዓይነት መብት አይኖረውም ።" ዞር ብሎ ወደ ዴሚሪስ ተመለከተ። "ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ታፈቅረው የነበረችውን ሚስቱን በአሰቃቂ ሁኔታ ለመግደሉ በቂ ማስረጃ በሕግ አስከባሪው በኩል ሊቀርብ ይችላል ። ይህ ማስረጃ ቀርቦላችሁ ስትሰሙ ልትሰጡት የምትችሉት ውሳኔ አንድ ብቻ ለመሆን እርግጠኛ ነኝ ። ይኸውም ተከሳሹ ለተከሰሰበት ወንጀል በአንደኛ ደረጃ ጥፋተኛ መሆኑን ነው ።" ተመልሶ ወደመቀመጫው ሄደና ተቀመጠ ።

ሰብሳቢ ዳኛው ወደናፖሊዮን ቾታስ ዞር አለ ። "ተከሳሾች የመከላከያ አሳብ ለማቅረብ ተዘጋጅታችኋል?"

"አዎ ጌታዬ" አለና ቾታስ በተሽከርካሪ ወንበሩ ወደፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ ተጠጋ ። አስፈሪ ፊቱንና ሽባ አካሉን ለማየት ቢጠየፉም በፊታቸው ገፅታ ላይ አዘኔታ እንደሚነበብ ተገንዝቧል ።

"ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የተከሰሰበት ጉዳይ ሀብታምና ኃያል ስለሆነ አይደለም ። ምናልባት ወደዚህ ፍርድ ቤት ተጐትቶ የመጣው በዚያ ሰበብ ሊሆን ይችላል ። ደካሞች ምን ጊዜም ጠንካሮችን ለማንበር ከክ መከጀላቸው አይቀርም ። ሚስተር ዴሚሪስ ኃያል ባለፀጋ በመሆኑ እንደጥፋተኛ ሊታይ ይችል ይሆናል ። ግን ባለቤቱን ከመግደል ወንጀል ንፁህ መሆኑን ለማረጋገጥ እወዳለሁ ።"

ችሎቱ የተጀመረው በዚህ ሁኔታ ነበር ።

አቃቤ ሕጉ ዴልማ ለፖሊስ የመቶ አለቃ ቲዮፊሎስ በዳኞቹ ፊት ጥያቄ አቀረበ ።

"የመቶ አለቃ ፣ ወደዴሚሪስ የባሕር ዳርቻ ቤት ስትገባ ምን እንዳየህ ትገልጥልናለህ?"

"ወንበሮቹና ጠረጴዛዎቹ ተገለባብጠውና ቤቱ ተመሰቃቅሎ ነበር።"

"በከባድ ልፊያና ትንቅንቅ ምክንያት ይመስልሃል?"

"አዎ ጌታዬ ። ቤት የተዘረፈ ነበር የሚመስለው ።"

"ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ሥፍራ በደም የተጨማለቀ ጩቤ አግኝተህ ነበር አይደል?"

"አዎ ጌታዬ ።"

"በጩቤው ላይ የጣት አሻራ ነበረ?"

"ትክክል ።"

"የማን የጣት አሻራ ነው?"

"የኮንስታንቲን ዴሚሪስ ።"

የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ ዓይን ዴሚሪስ ላይ አረፈ ።

"ቤቱን በምትፈትሽበት ወቅት ሌላ ምን አገኘህ?"

"ከቁም ሣጥኑ በስተጀርባ የዴሚሪስ አህፅሮተ ስም ያለበትን በደም የተጨማለቀ የዋና ሙታንታ ።"

"የዋና ልብሱ በቤቱ ውስጥ ለብዙ ጊዜ ቆይቶ ነበር ለማለት አይቻልም?"

"አይደለም ጌታዬ ያኔ በባሕሩ ውሀ እንደረጠበ ነበር ።"

"አመሰግናለሁ ።"

ተራው የናፖሊዮን ቾታስ ነበረ ። "መርማሪ ቲዮፊሉስ ፣ ተከሳሹን በግል የማነጋገር ዕድል አግኝተህ ነበር?"

"አዎ ጌታዬ"

"ስለእርሱ ሥዕላዊ መግለጫ እስቲ ስጠን ።"

"መልካም ..." አለና መርማሪው ዴሚሪስ ወደተቀመጠበት ተንጠራርቶ እያየ "ግዙፍ ሰው ነበር ለማለት እችላለሁ ።"

"ጠንካራ ይመስል ነበር? ማለት በሰውነት አቋሙ ።"

"አዎ ።"

"ማለቴ ሚስቱን ለመግደል ያን ያህል ቤቱን የሚያመሰቃቅል አይደለማ?"

ዴልማ ተስፈንጥሮ ቆመ ። "ተቃውሞ ።"

"ተቃውሞው ይጸናል ። የተከሳሹ ጠበቃ ጠቋሚ ጥያቄዎችን ባያቀርብ ጥሩ ነው ።"

"ይቅርታ ክቡር ጌታዬ ።" ቾታስ ወደመርማሪው ተመልሶ ዞረ ። "ከሚስተር ዴሚሪስ ጋር ካደረግከው ውይይት በወሰድከው ግምት ብልህ ሰው አድርገህ ትቆጥረዋለህ?"



"አዎ ጌታዬ ። በጣም ብልህና ጉበዝ ካልሆነ በቀር ማንም ሰው እንደርሱ ሀብታም ሊሆን አይችልም ።"

"ትክክል ብለሃል የመቶ አለቃ ፣ ይሁንና ይህ ሀቅ ወደሌላ ጥያቄ ይመራናል ። ታዲያ እንደ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ያለ ብልህ ሰው ግድያ የፈጸመበትን ጩቤ ከእነአሻራው እንዲሁም በደም የተጨማለቀ ሙታንታም ለማስረጃነት ትቶ ይሄዳል? ... ይህ ሞኝ የሚያከናውነው አይመስልህም?"

"አዎ ፣ አንዳንዴ ሰዎች ወንጀል በሚፈጽሙበት ወቅት እንግዳ ነገር መስራታቸው አዲስ አይደለም ።"

"ፖሊሶች ዴሚሪስ ከሚለብሰው ጃኬት ላይ የተበጠሰ የወርቅ አዝራር አግኝተዋል ይባላል ፤ ይህ ልክ ነው?"

"አዎ ጌታዬ ።"

"እና ለሚስተር ዴሚሪስ ወንጀለኛነት ዋነኛው ማስረጃ አዝራሩ ነው ። በፖሊሶቹ ግምት ሚችቱ ነፍሷን ለማዳን ስትታገለው የበጠሰችው መሆኑ ነው?"

"ትክክል ።"

"ታዲያ አዘውትሮ ላለባበሱ የሚጨነቅ የሚስተር ዴሚሪስ ዓይነት ሰው የጃኬቱ ቁልፍ መጉደል ፊት ለፊት እየታየው ሳያስተውል ቀረ? እቤቱ ውስጥ እየለበሰውም ልብ ሳይለው ቀረ? አውልቆት ቁም ሳጥኑ ውስጥ ሲሰቅለው እንዴት መበጠሱን አያይም? የመቶ አለቃ ፣ ይህማ ተከሳሹ ጅል ብቻ ሳይሆን ዓይነስውርም ነበር ማለት ነው?"

ተከታዩ ምስክር ሚስተር ካቴላኖስ ነበር ። የግል የወንጀል መከላከያና ምርመራ ድርጅት ባለቤት የሆነው ካቴላኖስ በአለባበሱ በጣሙን ደምቋል ።

ዴልማ "የግል የምርመራ ድርጅት ባለቤት ነህ?" ሲል ጥያቄ አቀረበለት ።

"አዎ ጌታዬ ።"

"እና ሚስስ ዴሚሪስ ከመገደሏ ከጥቂት ቀናት በፊት ልታነጋግርህ መጥታ ነበር?"

"ትክክል ነው ።"

"ምን ፍለጋ ነበር?"

"ጥበቃ ። ባለቤቷን ለመፍታት በመፈለጓ ሊገድላት እንደዛተባትና በዚህም የተነሳ የኛን ጥበቃ እንደምትሻ ገልጣለች ።"

ተመልካቹ ማጉረምረም ጀመረ ።

"እና ሚስስ ዴሚሪስ ተሸብራ ነበር?"

"አዎ ተረብሻ ነበር ።"

"ድርጅትህ ከባለቤቷ እንዲጠብቃት ነዋ የቀጠረችህ "

"አዎ ጌታዬ ።"

"ይበቃኛል ፤ አመሰግናለሁ ። " ዴልማ ወደ ቾታስ ዞር አለ ። "ምስክሩ ይኸውልህ ።"

ቾታስ ወንበሩን እያሽከረከረ ወደ ምስክሩ ተጠጋና "ሚስተር ካቱላኖስ በዚህ የምርምራ ሥራ ላይ ለስንት ዓመት አገልግሎት ሰጥተ ሃል?" አለው ።

"ለአሥራ አምስት ዓመታት ያህል ።"

ቾታስ ተገረመ ። "በጣም ረዥም ጊዜ ነው በሥራህ የተካንክ ሳትሆን አልቀረህም ።"

"ይመስለኛል" አለ ካቱላኖስ ጉራ እንዳይመስልበት እየሰጋ ።

"እና ችግር የገጠማቸው ሰዎችን በመርዳት በኩል ሰፊ ዕድል አለህ ማለት ነዋ!"

"ለዚህ አይደል ወደእኔ ዘንድ የሚመጡት!" አለ ካቱላኖስ ።

"እና ሚስስ ዴሚሪስ ወደአንተ ዘንድ ስትመጣ የተረበሸች ትመስል ነበር ፤ ወይንስ …?"

"አዎ በጣም የተረበሸች ትመስል ነበር ። ደንግጣ ነበር ለማለት ይቻላል ።"

"እሃ ምክንያቱም ባለቤቴ ይገድለኛል ብላ ፈርታ ስለነበር?"

"ትክክል ።"

"ታዲያ ከቢሮህ እንደወጣች ስንት ሠራተኞችህን እንዲከተሏት አደረግህ? አንድ? ሁለት?"

"የለም ፣ የሚከተላት እንኳ አልመደብኩላትም ።"

ቾታስ ተኰሳተረ ። "ለምን ያኔውኑ እንዳልመደብክላት ሊገባኝ ግን አልቻለም ።"

"ምክንያቱም እስከሰኞ ድረስ ጥበቃችንን እንድንጀምር አልፈለገ



ችም ነበር ።"

ቾታስ ግራ ተጋብቶ ወደእርሱ ተመለከተ ። "ሚስተር ካቱላኖስ ነገሮችን እያምታታህብኝ ነው ። ባለቤቱ ሊገድለኝ ስለሆነ በጣም ፈርቻለሁ ያለች ሴት እንዴት እስከመጪው ሰኞ ድረስ ጥበቃ እንዲደረግ ልኝ አልሻም ትላለች?"

"ይኸው ነው እንግዲህ እንዲሁ ነበር ያለችኝ ።"

ናፖሊዮን ቾታስ ለእራሱ እንደሚናገር ቀስ ባለ ድምፅ "የሚስስ ዴሚሪስ ፍራቻ ምን ያህል እንደነበር መቼም እግዜር ይወቀው ።"

የዴሚሪስ የቤት አገልጋይ ለምስክርነት ቀረበች ። "በሚስስ ዴሚሪስና በባለቤቷ መካከል በስልክ የተደረገውን ውይይት በትክክል ሰምተሻል?"

"አዎ ጌታዬ ።"

"ውይይቱ ምን እንደነበር ልትነግሪን ትችያለሽ?"

"ሚስስ ዴሚሪስ ባለቤቷን ልትፈታው እንደምትፈልግ ገልጻለት እርሱም ይህንኑ አሳቧን እንደማይቀበል ነግሯታል ።"

ዴልማ የፍርድ አሳብ ሰጪዎቹን ቃኘ ። "ገባኝ" ተመልሶ ወደምስክሯ አየ ። "ሌላስ የሰማሽው ነገር አለ?"

"በባሕር ዳርቻ ቤቱ በዘጠኝ ሰዓት ብቻዋን መጥታ እንድታገኘው ቀጠሮ ሰጧት ነበር ።"

"ብቻሽን መምጣት አለብሽ ነው ያላት?"

"አዎ ። እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት ባትመለስ ለፖሊስ እንዳመለክትም አዛኝ ነበር ።"

የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ አስተያየት ሲለወጥ በግልጽ ይታይ ነበር ። ሁሉም ዞር አሉና ዴሚሪስን በትኩረት ተመለከቱት ።

"ጥያቄዬን ጨርሻለሁ ።" ዴልማ ወደ ቾታስ ዞር አለና "የተከሳሽ ጠበቃ ልትጠይቃት ትችላለህ" ሲል ተናገረ ።

ናፖሊዮን ቾታስ ወንበሩን እያሽከረከረ ምስክሯ ወደ ቆመችበት ሥፍራ ተጠጋ ።

"ስምሽ አንድሪያ ነው አይደል?"

"አዎ ጌታዬ" አስቀያሚና አስፈሪ ወደሆነው ፊት ላለመመልከት ሞከረች ።

"አንድሪያ ፣ ሚስስ ዴሚሪስ ባሏን ልፈታህ እፈልጋለሁ ብላ ስትነግረውና ሚስተር ዴሚሪስም ለዚሁ ጥያቄዋ ምላሽ ለማግኘት በዘጠኝ ሰዓት ብቻዋን ወደባሕር ዳርቻው ቤት እንድትመጣ ሲጠይቃት መስማትሽን ተናግረሻል ፣ ይህ ልክ ነው?"

"አዎ ጌታዬ ።"

"አንድሪያ ፣ መሐላ መፈፀምሽን አትርሺ አንድሪያ አንቺ የሰማሺው ይህንን አይደለም ።"

"አዎ ይህ ነው ጌታዬ ።"

"በክፍሉ ውስጥ ስንት ስልክ ነበር?"

"አንድ ።"

ናፖሊዮን ቾታስ ወንበሩን እያሽከረከረ ወደምስክሯ ተጠጋ ። "ሌላ ስልክ አንስተሽ ሙሉ ንግግራቸውን አላዳመጥሽም ማለት ነው ።"

"እንዴት እንደዚያ አደርጋለሁ ጌታዬ?"

"እንግዲያውስ አንቺ የሰማሺው ሚስስ ዴሚሪስ የተናገረችውን ብቻ ነው ። የባሏን ንግግር ማዳመጥ ግን አይቻልሽም ነበር ።"

"እኔ ግን ስገምተው ..."

"በሌላ አነጋገር ሚስተር ዴሚሪስ ሚስቱን ሲያስፈራራ ወይም ወደባሕር ዳርቻው ቤት እንድትመጣ ሲጠይቃት አሊያም ሌላ ነገር ሲናገር በጆሮሽ አልሰማሽም ማለት ነው ። ይህንን የተናገርሺው ሚስስ ዴሚሪስ ስትናገር ስለሰማሽ ከሚስተር ዴሚሪስ ጋር ሳይሆን አይቀርም በሚል ግምት ነው ።"

አንድሪያ ግራ ተጋባች ። "መልካም ፣ ነገሩ እንዳልከውም ሊሆን ይችላል ።"

"እንዳልኩት ሊሆን ይችላል ። ለመሆኑ ሚስስ ዴሚሪስ ስልክ ስታነጋግር አንቺ ክፍሉ ውስጥ የነበርሽው ለምንድን ነው?"

"ሻይ እንዳቀርብላት ጠይቃኝ ነው ።"

"እና ሻይውን አመጣሽላት?"

"አዎ ጌታዬ ።"



"ጠረጴዛ ላይ ነው ያስቀመጥሺው?"

"አዎ ጌታዬ ።"

"ታዲያ ለምን ከክፍሉ አልወጣሽም?"

"ሚስስ ዴሚሪስ እንድቆይ በእጇ ምልክት ስለሰጠችኝ ።"

"አንቺ እርግጠኛ ውይይቱን እንድታዳምጪ ነው? ወይንስ ውይይት መስሎ እንዲሰማሽ ለማድረግ አስባ ነው?"

"መሰለኝ ።"

ድምፁ እየጠነከረና እየቀጠነ መጣ ። "ስለዚህ በስልኩ ባለቤቷን ታናግር ፣ ወይንም ለይስሙላ ብቻዋን ትለፍልፍ የምታውቂው ነገር የለም ማለት ነዋ!" ቾታስ ወንበሩን ይበልጥ ወደ እርሷ አስጠጋ ። "ወደክፍሉ ስትገቢ ስልኩን አቋርጣ ሚስስ ዴሚሪስ አንቺን ቆዪ ማለቷን እንደእንግዳ ነገር አትቆጥሪውም? እኔ እንደማውቀው እቤቴ ውስጥ የግል ውይይት በማድረግ ላይ ያለን ከሆነ ማንም የቤቱ ሠራተኛ ወዳለንበት ክፍል ውስጥ እንዲገባ አንፈቅድለትም ። ግልጽ ለማድረግ ያህል ያ ውይይት ጨርሶ አልተካሄደም ። ሚስስ ዴሚሪስ ማንንም አላነጋገረችም ። ሆን ብላ ከባለቤቷ ጋር እንደምታወራ በማስመሰል በዚህች ዕለት በዚህ ፍርድ ቤት ውስጥ በመረጃነት የሚያደናግር ወጥመድ አዘጋጀች ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ባለቤቱን አልገደለም ። በእርሱ ላይ የቀረቡት በጥንቃቄ የተወጠኑ ማስረጃዎች ሁሉ ሆን ብለው የተሸረቡ ናቸው ። ማንም ብልህ ሰው ወንጀል ፈጽሞ እንዲያ ዓይነት ማስረጃ ከኋላው ሊተው አይችልም ። የሚተው ይኖራል ቢባል እንኳ እንደ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ያለ ብልህ እንዲህ አያደርግም ።"

በፍርድ ቤቱ ለአሥር ቀናት ክርክር ሲካሄድ መከላከያ ሲሰማ እንዲሁም የልዩ ወንጀል ተከታታዮች ማረጋገጫ ሲቀርብና የፖሊስ ማስረጃ ሲታይ ቆየ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ወንጀለኛ ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት በአብዛኛው ሰው ዘንድ አደረ ።

ናፖሊዮን ቾታስ ቦንቡን ለማፈንዳት መዘግየቱን መረጠ ። ስፒሮስ ላምብሩን በምስክር ቃል መስጫ ሳጥን ውስጥ አቆመው ። የዕለቱ ችሎት ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የሄሊኒክ ንግድ ኮርፖሬሽኑና ሌሎችም

ንብረቶቹ ሁሉ ወደስፒሮስ ላምብሩ ይዞታ እንዲዛወሩ ዴሚሪስ ውል ፈርሟል ። አንድ ቀን ቀደም ብሎም እነኚህ ንብረቶቹ በምስጢር ወደናፖሊዮን ቾታስ ይዞታ ተዛውረዋል ። ይህ የንብረት ዝውውር ውል የሚፀናው ግን ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከተመሠረተበት ክስ በነፃ የተለቀቀ እንደሆነ ብቻ ነው ።

"ሚስተር ላምብሩ ፤ በአንተና በእህትህ ባለቤት በኮንስታንቲን ዴሚሪስ መሃከል አለመግባባት ነበር ይባላል ፤ እውነት ነው?"

"አዎ ፣ ስምምነት አልነበረም ።"

"በሁለታችሁ መካከል መቃቃር ነበር ለማለት ይቻላል?"

ላምብሩ ወደኮንስታንቲን ዴሚሪስ ተመለከተ ። "ይቻላል ። ከመቃቃርም በላይ ነበር ።"

"እህትህ በጠፋች ቀን ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በባሕር ዳርቻው ቤት አካባቢ እንዳልነበረ ለፖሊሶች ተናግረህ ነበር ። እንዲያውም በዘጠኝ ሰዓት ማለትም እህትህ ተገደለችበት በተባለው ሰዓት ዴሚሪስ በአክሮ ኮሪንዝ ካንተ ጋር እንደቆየ ነበር የገለፀው ። ፖሊሶች የአንተን ማረጋገጫ በጠየቁበት ወቅት ግን በሰዓቱ ካንተ ጋር መቆየቱን ክደህ ነበር ።"

"አዎ ክጂአለሁ ።"

"ለምን?"

ላምብሩ ለረዥም ጊዜ ዝም ብሎ ተቀምጦ ቀረ ። ከዚያም በንዴት "ዴሚሪስ እህቴን በየጊዜው እየሰደበ ፣ እያዋላና ሌላም ውርደት እያስከተለባት ስላበሳጫት እንዲቀጣ ፈልጌ ነበር ያቀድኩት ። ወንጀል ተፈጸመ በተባለበት ሥፍራ እንዳልነበረ እንድመሰክርለት ይፈልግ ነበር። እኔ ደግሞ ልመሰክርለት አልፈለግሁም ።"

"አሁንስ?"

"በዋሾነት ልቆይ አልፈልግም ። እውነት መናገር እንዳለብኝ ተሰምቶኛል ።"

"ያን ዕለት ከሰዓት በኋላ አንተና ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በአክሮ ኮሪንዝ አንድ ላይ ነበራችሁ?"

"አዎ እርግጠኛ ነኝ አንድ ላይ ነበርን ።"

በፍርድ ቤቱ ውስጥ ሁካታ ተሰማ ። ዴልማ ፊቱ በርበሬ እንደመሰለ ከተቀመጠበት ተነሳ ። "ክቡር ጌታዬ ፣ ተቃውሞ አለኝ ...."

"ተቃውሞህ ተቀባይነት የለውም ።"



ዴልማ ተመልሶ ወንበሩ ላይ ዘፍ አለ ። ዓይኑ የፈካው ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ወደፊት አዘንብሎ ተቀመጠ ።

"እስቲ እንዴት እንደተገናኛችሁ አጫውተን ። እንድትገናኙ አሳብ ያቀረብከው አንተ ነህ?"

"አይደለም አሳቡ የሜሊና ነበር ። ሁለታችንንም አታልላን ነው።"

"እንዴት አድርጋ ነው ያታለለቻችሁ?"

"ሜሊና በስልክ ደወለችልኝና ባልዋ በግል መዝናኛ ክበቤ ውስጥ ለንግድ ሥራ ጉዳይ ሊያነጋግረኝ እንደሚሻ ገለጠችልኝ ። እንደገና ደግሞ ለዴሚሪስ ደውላ እኔ ላገኘው እንደምፈልግ ነገረችው ። በተባለው ሥፍራ እንደተገናኘን ሁለታችንንም የሚያወያየን ነገር አልነበረም ።"

"እና ሁለታችሁ የተገናኛችሁት ሚስስ ዴሚሪስ ሞተች በተባለው ሰዓት ነው?"

"ትክክል ።"

"እኔ ሰዓት አስይዤ እንዳስጠናሁት በመኪና ከአክሮ ኮሪንዝ እስከ ባሕር ዳርቻ ቤቱ አራት ሰዓት ይፈጃል ።" ናፖሊዮን ቾታስ ወደፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ ዞር ብሎ ተመለከተ ። "ስለዚህ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በዘጠኝ ሰዓት በአክሮ ኮሪንዝ ታይቶ ተመልሶ ደግሞ ከምሽቱ በአንድ ሰዓት አቴንስ ውስጥ ሊገኝ በፍፁም አይችልም ። "ቾታስ ወደስፒሮስ ላምብሩ ዞር ብሎ ተመለከተ ። ቃለመሐላ ፈፅመሃል ላምብሩ ። ለዚህ ፍርድ ቤት የሰጠኸው ቃል እውነተኛ ነው?"

"አዎ ነው ። እግዚአብሔር ምስክሬ ነው ።"

የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ ለአራት ሰዓታት ለምክክር ቆይታ አድርገው ተመልሰው ወደፍርድ ቤቱ ሲገቡ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በጥሞና ይመለከት ነበር ። ፊቱ ገርጥቶ በጉጉት ውሳኔውን ይጠባበቃል ። ቾታስ ግን ወደሰዎቹ እንደማየት አተኩሮ የሚያየው የኮንስታንቲን ዴሚሪስን ፊት ነው ። ያ ሁሉ የዴሚሪስ ትዕቢትና ኩራት አሁን አይታይም ። ከሞት ፊት ለፊት የቆመ ሰው ነው ።

የመሐል ዳኛው "የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎች ከውሳኔ ላይ ደረሱ?" ሲሉ ጠየቁ ።

"አዎ ደርሰናል ፤ ክቡር ጌታዬ ።" የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ ሰብሳቢ

ወረቀት ይዞ ተነሳ ።

"እባክህ ውሳኔውን ለአስተናባሪው ትሰጥልኝ?"

አስተናባሪው የውሳኔውን ወረቀት ተቀበለና ለመሐል ዳኛው ሰጣቸው ። የመሐል ዳኛው ወረቀቱን አዩና ቀና ብለው "የፍርድ ውሳኔ ሰጪዎቹ ተከሳሹን ጥፋተኛ ሆኖ አላገኙትም" ሲሉ ገለፁ ።

በፍርድ ቤቱ ውስጥ ጫጫታ በረከተ ። ግማሹ ተነስቶ ሲያጨበ ጭብ ሌላው ደግሞ ያጉረመርማል ።

የዴሚሪስ ፊት ፈካ ። በኃይል ወደውስጥ ተነፈሰና ተነስቶ ቾታስ ወዳለበት ሥፍራ ሄዶ "እንዳልከው አደረግክ! ትልቅ ባለውለታዬ ነህ ።" አለው ።

ቾታስ ትኩር ብሎ ዓይን ዓይኑን እያየ "እዚህ ላይ አበቃን ። እንግዲህ እኔ ስከብር አንተ ደግሞ ደህይተሃል ። በል አሁን የደስ ደስ ልበልህ ።"

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የቾታስን ተሽከርካሪ ወንበር እየገፋ በሕዝቡና በጋዜጠኞች መካከል አልፎ ወደመኪና ማቆሚያው አመራ ። ቾታስም ከፍርድ ቤቱ መግቢያ አጠገብ ወደ ቆመችው ሲዳን መኪና አመለከተ ። "መኪናዬ ያችትና ።"

ዴሚሪስ ወንበሩን እየገፋ ወደ መኪናዋ ተጓዘ ። "ምነው ሾፌር የለህም?"

"አያስፈልገኝም ፡ እኔ ራሴ እንድነዳት ሆና በልዩ ትዕዛዝ የተሠራች ልኝ ናት ። ወደውስጥ አስገባኝ ።"

ዴሚሪስ የመኪናዋን በር ከፈተና ቾታስን ተሸክሞ ከመሪው አጠገብ አስቀመጠው ። ተሽከርካሪ ወንበሩንም አጣጥፎለት ከኋላ ኮፈን ውስጥ ከከተተው በኋላ እራሱም መኪናው ውስጥ ገብቶ ከቾታስ ጐን ተቀመጠ ።

"አሁንም በዓለም ውስጥ ያሉት ጠበቃዎች ቁንጮ ነህ" ሲል ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ፈገግ አለ ።

"አዎ" አለና ናፖሊዮን ቾታስ መኪናውን አስነስቶ ማሽከርከሩን ቀጠለ ። "አሁን ምን ልትሠራ አስበሃል ኮስታ?"

ዴሚሪስ በጥንቃቄ "ምን ታደርገዋለህ እንደምንም ብዬ እራሴን ለማቋቋም እሞክራለሁ" ብሎ መለሰ ። በልቡ ግን 'በመቶ ሚሊዮን ዶላር እንደገና የእራሴን ሰፊ ድርጅት አቋቁማለሁ' አለ ።



ዴሚሪስ እየሳቀ "ስፒሮስ ፣ እንዴት እንዳታለልከው ሲረዳ በጣም መበሳጨቱ ነው ።"

"ከእንግዲህ ምን ሊያደርግ ይችላል ብለህ ነው?" ሲል ማረጋገጫ ሰጠው ። "ባዶ ኩባንያ የሚያሳቅፈው ውል ነው የተፈራረመው ።"

ወደተራራው ተጓዙ ። ቾታስ የፍሬን መያዣና የቤንዚን መስጫውን እንዲሁም ማርሽ መቀየሪያውን እየተቆጣጠረ መኪናውን ሲያሽከረክር ዴሚሪስ ይመለከት ነበር ። "ደህና አድርገህ ነው የምትነዳው ።"

"የግድ ሲሆንብህ ትማራዋለህ" አለ ቾታስ ። በጠባቧ መንገድ ወደተራራው ጫፍ አሽከረከረ ።

"ወዴት ነው የምንሄደው?"

"እዚህ ጫፉ ላይ ትንሽ ቤት አለችኝ ። አንዳንድ ብርጭቆ ሻምፓኝ እንጠጣና በታክሲ ወደ ከተማ እልክሃለሁ ። ታውቃለህ ኮስታ ፣ ከዚህ ቀደም ስለተፈጸሙት ነገሮች አስብ እንደነበረ? … ስለ ኖኤሌ ሞት ፣ ስለላሪ ዶግላስ ሞት ፣ እንዲሁም ስለዚያ ምስኪን ስታቭሮስ ። ግን መቼም የሦስቱም አሟሟት ከገንዘብ ጋር በተገናኘ ምክንያት ነው አትለኝም ።" ዞር ብሎ ዴሚሪስን ተመለከተው ። "ሁሉም በጥላቻ ምክንያት ነው ። በጥላቻና በፍቅር ። ኖኤሌን ትወዳት ነበር?"

"አዎ" አለ ዴሚሪስ ። "ኖኤሌን እወዳት ነበር ።"

"እኔምኮ እወዳት ነበር ግን እንደምወዳት አታውቅም ነበር አይደል?" አለ ቾታስ ። ዴሚሪስ በመገረም ተመለከተው ። "አላውቅም ።"

"እንደዚያ ሆኖ እርሷን እንድትገድል ረዳሁህ ። ለዚያ ኃጢአቴ ምንጊዜም ከፀፀት አላመልጥም ። አንተስ ኮስታ?"

"ዋጋዋን ነው ያገኘችው ።"

"እኛም መጨረሻ ላይ ዋጋችንን እናገኛለን ። አንድ ያልነገርኩህ ነገር አለ ኮስታ ። የእሳቱ ጉዳይ የእሳት አደጋ ከደረሰብኝ ከዚያ ሌሊት ጀምሮ ልቋቋመው የማልችለው ሕመም ይሰማኛል ። ዶክተሮች መልሰው እንደነበርኩ ሊያደርጉኝ ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም ። በመጥፎ ሁኔታ ነው ሰውነቴ ሽባ የሆነው ።" መኪናውን ለማፍጠን ማርሽ ቀየረ ። በጣም ጠባብ በሆነው ጠመዝማዛው መንገድ እየበረሩ ከተራራው ላይ ሲወጡ የኤጊአን ባሕር ከበታቻቸው ርቆ ወለል ብሎ ታየ ።

"እንደእውነቱ ከሆነ" አለ ቾታስ በጐረነነ ድምፅ ። "በአሁኑ ወቅት የሚያሰቃየኝ ሕመም በሕይወት ኑር ፣ ኑር አያሰኘኝም ።" ማርሽ

ቀይሮ መኪናዋን የበለጠ አበረረ ።

"ቀስ በል" አለ ዴሚሪስ ። "ልትገለ…"

"እኔና አንተ አንድ ላይ እንዲያከትምልን ለማድረግ ወስኛለሁ ።"

በድንጋጤ የተዋጠው ዴሚሪስ ዞር ብሎ አየው ። "ምንድነው የምታወራው? ፍጥነት ቀንስ ነው የምልህ ሰውዬ ። ሁለታችንም እንዳናልቅ ።"

"ልክ ነህ" አለ ቾታስ ማርሹን እንደገና ሲለውጥ መኪናዋ ወደፊት ዘለለች ።

"እብድነህ ልበል? ሀብታም ሆነህ ሳለ ለምን ለመሞት ትፈልጋለህ?" አለ ዴሚሪስ ።

የተጠባበሱት የቾታስ ከንፈሮች ፈገግ ለማለት ሲሉ እጅግ አስፈሪ ሆኑ ።

"የለም እኔ ሀብታም አይደለሁም ። ማን ሀብታም እንደሆነ ታውቃለህ? ወዳጅህ ሲስተር ተሬዛ ። ገንዘብህን ሁሉ ኢአኒና ለሚገኘው የሴቶች ገዳም ሰጥቻለሁ ።"

መኪናዋ ወደኩርባው አቅጣጫ ሸመጠጠች ።

"መኪናውን አቁመው" ሲል ዴሚሪስ ጮኸ ። መሪውን ከቾታስ ለመንጠቅ ቢታገል አልተቻለውም ።

"የምትፈልገውን ሁሉ እሰጥሃለሁ" አለ ዴሚሪስ በጭንቀት ። "አቁም!"

"የምፈልገውን አግኝቻለሁ" አለ ቾታስ ።

ወዲያው የተሳፈሩባት መኪና ከገደሉ ላይ ተንሳፍፋ እየተላተመች በፊትና በኋላ እየተገለባበጠች ረጅሙን የተራራ ቁልቁለት ጨርሳ ከባሕሩ ላይ ወደቀች ። የከባድ ፍንዳታ ድምፅ ተሰማ ። ከዚያም ረጭ ያለ ፀጥታ ።

ፍፃሜም ሆነ ።